ላይ ያደርጋል፤ እንደ ክብር እንግዳ ሁሉ ኢየሱስ ከስምዖን በስተ ጀርባ በኩል ሊሆን ይችላል::

በሰፈሩ ጥሩ ስም ያልነበራት ሴት ወደ ቤት ገባች::[115] ለመሆኑ ኃጢአትዋ ምን ነበር? በእርግጥ ማወቅ ባንችልም ሴተኛ አዳሪነት ሊሆን እንደሚችል ይታሰባል::[116] (1) በሰፈሩ ሁሉ የታወቀች መሆኗ፣ (2) ፀጉርዋን መሸፈን ሲኖርባት እንደዚያ አለማድረጓ፣ (3) ኢየሱስን በመንካትዋ ስምዖን ቅር መሰኘቱ ይህንኑ ሐሳብ ያጠናክራል::

በመጀመሪያ ደረጃ እንዲህ ያለችዋ ሴት እንዴት ወደ ስምዖን ቤት መግባት ቻለች? እንዲህ ያለ ግብዣ በሚደረግበት ጊዜ ሰዎች የግብዣ ሥርዓቱን እንዲያዩ፣ አንዳንዴም ከተጋባዦቹ ጋር እንዲነጋገሩ ይፈቀድ ነበር፤ ሌላው ቀርቶ ከተራረፈው ይወስዱ ነበር:: ይህች ሴት ወደ ኢየሱስ ለመጠጋት በተገኘው አጋጣሚ ተጠቅማለች፤ ሌላው አማራጭ ደግሞ ከዚያ በፊት በተለየ ምክንያት እዚያ ቤት መጥታ ሊሆን መቻሉ ነው:: አሁንም ቢሆን ትክክል ባለሆነ ሁኔታ የስምዖንን ስም ማንሣት አንፈልግም፤ የሃይማኖት መሪ እንዲህ ሊያደርግ እንደሚችል ይህ የመጀመሪያውም የመጨረሻውም አይደለም::

የአልባሳጥሮስ ሽቱ ብልቃጥ ይዛ ነበር:: እንዲህ ያለው ብልቃጥ በክር ወይም በሐብል ሴቶች አንገት ላይ ይታሰርና ልብሳቸው ውስጥ እንዲወሸቅ ይደረግ ነበር:: እንዲህ ላለው ውድ ዕቃ ከዚህ የተሻለ ዋስትና ያለው ቦታ ሊኖር አይችልም:: አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜም ሽቱውን ለመጠቀም ወይም የሰውነት ጠረንን ለማደስ ምቹ ቦታ ነበር:: (በተለይ ደግሞ እንደ እርሷ ላለች ሴት ሁለቱም የሚስማማ ነበር):: አልባስጥሮስ የከበረ ድንጋይ ሲሆን እንዲህ ያለው ጥሩ ሽቱ

[115] በሚቀጥለው ምዕራፍ (ሉቃ 8÷2) ላይ ሰሚ በመነሣቱ አንዳንዶች ይህች ሴት ሰባት አጋንንት የወጡላት (ማር 16÷9) ማርያም መግደላዊት ለትሆን እንደምትችል አስበዋል:: ሆኖም እርግጠኛ መሆን አይቻልም::

[116] T. Cavalcanti, "Jesus, the Penitent Woman and the Pharisee," *JHLT* 2/1(1994): 28-40.



የሚቀመጥበት እንደሆነ በብልቃጥ መልክ ይቀረጽ ነበር፤ በጣም ውድና የከበረ ስጦታ ይዛ ነበር የመጣችው:: ይህን የሚያህል ዋጋ ያለው ነገር የአንድ ዓመት ደመወዝ ሊጠይቅ ይችላል (ዮሐ 12÷5)::

ሁኔታው የሚያጓጓና ልብ የሚያንጠለጥል ነበር:: ኢየሱስን ሽቱ ለመቀባት ስትል እርሱ ወደ ነበረበት ቦታ መጣች:: ለእርሱ የነበራትን አክብሮት በአራት የተለያዩ መንገዶች ገልጻለች፤

1. በእንባዋ እግሩን አጠበች፤ «አራሰች» የሚለው ግሥ በሌሎች ቦታዎች፣ «ዝናብ» በሚል ተተርጉሟል:: ከዐይኖቿ የሚወርደው እንባ እግሮቹ ላይ ፈሰሱ:: በእርግጥም እግሮቹን ማራስ የሚችል በቂ እንባ ፈስሷታል::
2. በጠጉርዋ እግሮቹን አበሰች:: በእግሮቹ ሥር ክብርዋን ጣለች (ከ1ቆሮ 11÷15 ጋር ያነ):: በእንዲህ ዓይነት ትሕትና ጌታን አገለገለች::
3. እግሮቹን ሳመች:: «እየሳመች» የሚለው «ሳመች» የሚለውን ግሥ ለማጠናከር የቀረበ ነው:: በሌላ አነጋገር ደጋግማ ትስም ነበር::
4. እግሮቹን ሽቱ ቀባች:: ይህም ከዘይት ይልቅ ውድ ነው:: «ቀባች» ለማለት እዚህ ላይ የተጠቀመበት ግሥ በተለመደው ሃይማኖታዊ ሥርዓት እንደሚደረገው («ማፍሰስ») ማለት ሳይሆን፣ «አበሰች» ተብሎ የሚተረጐም ነው::

ሉቃ 7÷39-43

[39]የጋበዘውም ፈሪሳዊ ይህን ባየ ጊዜ፣ «ይህ ሰው ነቢይ ቢሆን ኖሮ፣ የነካችው ሴት ማን እንደ ሆነች፣ ደግሞም ምን ዐይነት ሰው እንደሆነች ባወቀ ነበር፤ ኃጢአተኛ ናትና» ብሎ በልቡ አሰበ:: [40]ኢየሱስም፣ «ስምዖን ሆይ፤ የምነግርህ ነገር አለኝ» አለው:: እርሱም፣ «መምህር ሆይ፤ ንገረኝ» አለው:: [41]ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ «ለአንድ አበዳሪ ገንዘብ የተበደሩ ሁለት ሰዎች ነበሩ፤ አንደኛው አምስት መቶ

ዲናር፣ ሁለተኛው ደግሞ አምሳ ዲናር ነበረበት:: 42የሚከፍሉትም ቢያጡ ዕዳቸውን
ለሁለቱም ተወላቸው:: እንግዲህ ከሁለቱ አበዳሪውን አብልጦ የሚወደው የትኛው ነው?
43ስምዖንም፣ «ብዙው ዕዳ የተተወለት ይመስለኛል» ሲል መለሰ:: ኢየሱስም፣ «ትክክል
ፈርደሃል» አለው::

የስምዖንን አስተሳሰብ በሚከተለው ምክንያታዊ ሁኔታ በአጭሩ ማስቀመጥ ይቻላል፤

*ሀ. ኢየሱስ ነቢይ ቢሆን ኖሮ፣ ምን ዐይነት ሴት እንደሆነች ያውቅ ነበር::[117]*

*ለ. ምን ዓይነት ሴት እንደሆነች ኢየሱስ ቢያውቅ ኖሮ ስትነካው ዝም አይልም ነበር::[118]*

*ሐ. ኢየሱስ ግን ስትነካው ዝም ብሏል::*

*ስለዚህ ኢየሱስ ነቢይ አይደለም ማለት ነው::*

የዚህ አስተሳሰብ ወይም ምክንያታዊ ድምዳሜ ችግር በ «ለ» የተቀመጠው ነው፤ ፈሪሳዊው የራሱን ባሕላዊ አስተሳሰብ መሠረት በማድረግ መሲሑ አመንዝራ ሴት ስትነካው ዝም ብሎ አያይም የሚል መደምደሚያ ላይ ደርሷል:: ስሕተቱ እዚህ ላይ ነው::

ኢየሱስ ግን ሴትየዋ ማን እንደ ሆነች ማወቅ ብቻ ሳይሆን ስምዖን እያሰበ የነበረውን እንኳ እንደሚያውቅ ግልጽ አደረገለት፤ ስምዖን ሆይ፣ የምነግርህ ነገር አለኝ» አለው:: እርሱም ኢየሱስ እያሰበ የነበረውን እንዳወቀ ሳይጠረጥር በአክብሮት፣ «መምህር ሆይ፣ ንገረኝ» አለው:: ምንኛ ግብዝ ነበር! በልቡ እየተብላላ የነበረውና አንደበቱ የሚናገረው በፍጹም የተለያየ ነበር::

---

117 ነቢይ የሰዎችን ሐሳብና አኗኗር መለየት እንደሚችል ይታሰብ ነበር (ኢሳ 11÷2-4፤ 1ነገ 14÷6፤ 2ነገ 1÷1-3፤ 5÷26 ጋር ያነ)::

118 አይሁድ ኀጢአተኛ ሴት፣ እንድትነካቸው ቀርቶ በጣም ከተከበረች ሴት እንኳ ፊት አይነጋገሩም:: በዚህ ላይ ደግሞ ከሥራዋ ባሕርይ የተነሣ እንደ ርኩስ ትቆጠራለች::



ኢየሱስ ስለ አንድ ገንዘብ አበዳሪ ቀለል ያለ ምሳሌ ነገረው፤ ይህ ሰው የባንክ ሠራተኛ ወይም ከሰዎች ትርፍ የሚያጋብስ አራጣ አበዳሪ ሊሆን ይችላል:: በሌላ አነጋገር ይህን ያህል ቸር እንዲሆን የሚጠበቅበት አልነበረም:: ይሁን እንጂ፣ ይህን ያደረገው እነዚህ ሁለት ሰዎችን ከዕዳ ነጻ ለማድረግ ነበር::

አንድ ዲናር የአብዛኛው ሰው የአንድ ቀን ደመወዝ ነበር፤ ስለዚህ አንደኛው ሰው የአንድ ወር ተኩል ደመወዝ ሲኖርበት፣ ሌላው ግን ዐሥር እጥፍ፣ ያም የሁለት ዓመት ደመወዝ የሚሆን ዕዳ ነበረበት::

ስለዚህ ገንዘብ አበዳሪውን ይበልጥ የሚወድ ማነው? «ይመስለኛል» የሚለው ለጉዳዩ ይህን ያህል ትኩረት እንዳልሰጠ የሚያመለክት ሊሆን ይችላል:: ምናልባትም አንድ ዓይነት ወጥመድ እየተዘጋጀለት እንደ ሆነ ጠርጥሮ ሊሆን ይችላል፤ እንዴት ሊሆን እንደሚችል ግን እርግጠኛ አልነበረም::

ሉቃ 7÷44-47

44ወደ ሴቲቱም ዘወር ብሎ ስምዖንን እንዲህ
አለው፤ «ይህቺን ሴት ታያታለህን? እኔ ወደ ቤትህ ገባሁ፤
አንተ ለእግሬ ውሃ እንኳ አላቀረብህልኝም፤ እርሷ ግን እግሬን በእንባዋ እያራሰች
በጠጉርዋ አበሰች 45አንተ ከቶ አልሳምኸኝም፤ እርሷ ግን ከገባሁ ጀምራ እግሬን
ከመሳም አላቋረጠችም:: 46አንተ ራሴን ዘይት አልቀባህም፤ እርሷ ግን እግሬን ሽቶ
ቀባች:: 47ስለዚህ እልሃለሁ፤ እጅግ ወዳለችና ብዙው ኀጢአቷ ተሰርዮላታል፤ በትንሹ
የተሰረየለት ግን የሚወደው በትንሹ ነው::

ሁኔታው ዋጋ የመተመን ያህል ነበር:: ኢየሱስ ወደ ሴትየዋ እየተመለከተ ለስምዖን ተናገረ:: ሁለቱ ሰዎች ለእርሱ የነበራቸውን አቀራረብ በሚከተለው ሁኔታ በንጽጽር አቅርቦታል::

1. እግር ማጠብ፤ ይህ እንግዳ መቀበልን አስመልክቶ አንድ የሚደረግ ዋና ጉዳይ ነበር:: በነጠላ ጫማ በአቧራማው መንገድ ከተጓዙ በኋላ እግር መቆሸሹ የማይቀር ነው:: ስለሆነም

አገልጋዮች የእንግዶችን እግር ማጠባቸው ተገቢ ነበር:: እግሩ ከታጠበ እንግዳው የቤቱን ምንጣፍ አያቆሽሽም:: ስምዖን ይህን ለማድረግ ሲደክም አይታይም:: ሴትየዋ ግንእግሩን ማጠቧ ብቻ ሳይሆን በእንባዋ ጭምር በማራስ በጠጉርዋ አብሳለች::

2. የሰላምታ አሳሳም፤ እንዲህ ያለው አሳሳም የወንድና የሴት መሳሳምን አይደለም የሚያመለክተው:: ወንዶችም ቢሆኑ ጉንጭ ለጉንጭ በመሳሳም ሰላም ይባባላሉ:: ስምዖን ግን ኢየሱስን በመሳም ፍቅሩን አላሳየም:: ይህች ሴት ግን መሳም ብቻ ሳይሆን፣ ዝቅ ብላ እግሮቹን ደጋግማ ስማለች::
3. መቀባት፤ ይህ የተለየ ዓይነት አክብሮት ምልክት ነው:: ብዙውን ጊዜም ወይራ ዘይት በመቀባት ነበር የሚደረገው:: የወይራ ዘይት ለቤት ውስጥ አገልግለት የተለመደ ነበር:: ስምዖን በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ለኢየሱስ የሚገባውን አክብሮት አላሳየም:: ይህች ሴት ግን መቀባት ብቻ ሳይሆን ተራ ከሆነው ዘይት ይልቅ በጣም ውድ በሆነ ሽቱ ቀብታዋለች:: የኢየሱስን ራሱን ብቻ ሳይሆን እግሩንም ጭምር አክብራለች:: እንዲህ ማድረጓ ግን እንደ ቅንጦት ነበር የተቆጠረባት (Pliny, H.N. 13:4)::

ቁጥር 47 በስምዖንና በዚህች አመንዝራ ሴት መካከል ንጽጽር ማድረጉን ቀጥሏል:: ብዙ ይቅር የምትባለው ኀጢአት ስለ ነበራት ብዙ ወዳለች:: ስምዖን ግን ይቅር የሚባለው በጥቂቱ ስለ ነበር በጥቂቱ ወዷል:: ሐቁ ግን እንደ አመንዝራዋ ሴት ሁሉ ስምዖንም የነበረበትን ዕዳ መክፈል አለመቻሉ ነበር:: ኢየሱስ ከስምዖን ጋር አብሮ ለመብላት ወደ ቤቱ ሲገባ ከሆነው ይልቅ ይህች ሴት እንድትነካው ለማድረግ ያን ያህል ራሱን አላመቻቸም:: መሠረታዊው ጉዳይ ኢየሱስ ለሁላችንም የሚያስፈልገን መሆኑ ነው::



**ሉቃ 7÷48-50**

48ኢየሱስም ሴቲቱን፣ «ኀጢአትሽ ተሰርዮልሻል»
አላት:: 49አብረውት በማእድ ተቀምጠው የነበሩ
እንግዶችም፣ «ይህ ኀጢአትን እንኳ የሚያስተሰርይ እርሱ
ማን ነው?» ብለው በልባቸው አሰቡ:: 50ኢየሱስም
ሴቲቱን፣ «እምነትሽ አድኖሻል፤ በሰላም ሂጂ» አላት::

በዚያ ማእድ ላይ እያለ ኢየሱስ ለሁለተኛ ጊዜ የሰዎች መከራከሪያ ርዕስ ሆነ:: ከጥቂት ወሮች በፊት አራት ሰዎች ሽባ የነበረ ወዳጃቸውን በቃሬዛ በቤቱ ጣራ ባወረዱ ጊዜ በቅፍርናሆም የዚህ ዐይነት ክርክር ተነሥቶ ነበር:: ኢየሱስ የሰውየውን ኀጢአት ይቅር አለ፤ እንደዚያ ማድረግ እንደሚችል ሰውየውን በመፈወስ አሳየ (ሉቃ 5÷17-26):: በዚህ ጊዜ ግን ምንም ዐይነት ማረጋገጫ ወይም ማስረጃ አላሳየም:: እንዲያውም በቤቱ ውስጥ ለነበረው ሽኩሽኩታ ይህን ያህል ትኩረት የሰጠ አይመስልም:: ትኩረቱን ሁሉ ያደረገው በዚያች ለሐሜት በተጋለጠች ሴት ላይ ነበር::

«እምነትሽ አድኖሻል::» ይህ አጭር ዐረፍተ ነገር በተለያዩ ፍሬ ሐሳቦች ታጭቆአል:: በመጀመሪያ ደረጃ፣ ያዳናት እምነቷ አልነበረም:: ያዳናት ኢየሱስ ነበር፤ ምክንያቱም ማዳን የሚችል እርሱ ብቻ ነው:: ሆኖም፣ የሚያድነው በእምነት ወደ እርሱ የሚመጡትን ብቻ ነው:: በተጨማሪም እምነቷን ያሳየችው በተግባር በሚገለጥ አምልኮ እንጂ በአንደበት አልነበረም:: እምነታችን የሚለካው በምንፈጽመው ተግባር ነው::

ኢየሱስ፣ «ድነሻል» አለ (ግሪክ ኃላፊ ጊዜ)፤ ስለዚህም በሰላም መሄድ ትችላለች:: በፊት ከነበረው የተለየች አልሆነችም፤ ሆኖም ድናለችና ተለውጣለች፤ ገና ብዙ የምታስተካክለውም ይኖራታል:: ፈተናዎችን ማሸነፍ፣ ማኅበረሰቡ የሚያደርስባትን ማግለልና ሥራዋን

ስታቋርጥ የሚደርስባትን ድህነትም መቋቋም ይኖርባታል:: ከእንግዲህ ሰላም የሚመጣው ከውስጥ ነው:: ኢየሱስ ኀጢአትዋን ይቅር በማለቱ፣ በእርግጥም ሰላሟ የተጠበቀ ይሆናል::

**§ 60**
**የኢየሱስ አገልግሎት የሚረዱ ሴቶች**
**(ሉቃ 8÷1-3)**

[1]ከዚህ በኋላ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት የምሥራች ቃል እየሰበከ በየከተማውና በየመንደሩ አለፈ:: ዐሥራ ሁለቱም ከእርሱ ጋር ነበሩ፤ [2]እንዲሁም ከርኩሳን መናፍስትና ከደዌ የተፈወሱ አንዳንድ ሴቶች አብረውት ነበሩ፤ እነርሱም ሰባት አጋንንት የወጡላት መግደላዊት የተባለችው ማርያም፣ [3]የሄሮድስ ቤት ኀላፊ የነበረው የኩዛ ሚስት ዮሐና፣ ሶስና ደግሞም ሌሎች ብዙዎች ነበሩ፤ እነዚህም በገዛ ንብረታቸው የሚያገለግሉት ነበሩ::

ይህ ክፍል አጭር ከመሆኑም በላይ ትኩረት የሚስብ ነው:: ለሁለተኛው የኢየሱስ የገሊላ አገልገሎት በር የተከፈተው በዚህ ጊዜ ነበር:: ዐሥራ ሁለቱ፣ «ከእርሱ ጋር ነበሩ» (ቁ 1):: ከጌታ ጋር አብረው ማገልገል ሳይጀምሩ አልቀረም:: አብረውት የነበሩት እነርሱ ብቻ አልነበሩም:: በሚገርም ሁኔታ የኢየሱስን አገልግሎት በገንዘባቸው የሚረዱ ታዋቂ ሴቶችም ነበሩ:: ከባሕሉ ውጪ ቢሆንም እንኳ፣ እስከ መጨረሻው ድረስ ከኢየሱስ ደቀመዛሙርት ጋር ነበሩ (ሉቃ 23÷55)::[119] እንደ ኢየሱስ ሁሉ ሉቃስ ለሴቶች ያለው አክብሮት ታይቷል::

119 ዊዘሪንግተን እንደሚለው፣ ምንም እንኳ እነዚህ ሴቶች ባሕላዊ በሆነ መልኩ የሐዋርያቱን ቡድን እየረዱ ቢሆንም አንድን የሃይማኖት መምህር በደቀ መዛሙርነት መከተላቸው በዘመኑ በጣም ያልተለመደ ጉዳይ ነበር:: ሲም ደግሞ ከዚህም ርቆ ይሄዳል:: እርሱ እንደሚለው፣ (1) እነዚህ ሴቶች አብዛኞቹ ያላገቡ፣ ባል የሞተባቸው፣ ጥቂቶችም ሴተኛ አዳሪ የነበሩ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ተራ አገልጋዮች ብቻ ሳይሆኑ ሙሉ በሙሉ የተሰጡ ደቀ መዛሙርት ነበሩ፤ (2) ሀብታም የነበሩ ደቀ መዛሙርት ገንዘብ የሚያገኙበትን ሥራ እንደ መተዋቸው መጠን እነዚህ ሴቶች የበጐ ፈቃድ ልግስና ከማድረግ ያለፈ ሥራ ነበረባቸው፤ ከሐዋርያት ሥራ እንደምናነበው የኢየሱስ ተከታዮች ጋርዮሻዊ የአኗኗር መንገድ እየተለማመዱ ነበር::



መግደላዊት ማርያም ምንጊዜም ከኢየሱስ ጋር ነበረች:: ከሰባት አጋንንት ነጻ ያወጣት ሲሆን፣ ከመጀመሪያው የትንሣኤው ምስክሮችም አንዷ ነበረች (ማር 16÷9)::

ዮሐና የሄሮድስ ቤት አስተዳዳሪ የነበረው የኩዛ ሚስት ነበረች:: ሁሉም ነገር በትክክል መከፋፈሉን ማረጋገጥ የእርሱ ኀላፊነት ነበር:: ይህ ቀላል ሥልጣን አልነበረም:: ሚስቱ ለኢየሱስ የበራትን ፍቅር ኩዛ መጋራቱን አናውቅም:: እንደዚያ ባይሆን ኖሮ ግን ከኢየሱስ ጋር የነበራትን ግንኙነት እንድታቆም ያደርግ ነበር:: የምታደርገው የገንዘብ ርዳታ በቀላል የሚታይ አልነበረም:: የኢየሱስ ተሰሚነትም «ከተራ ሰዎች» አልፎ ሄዷል::

እነዚህና ሌሎች ሴቶች እያደረጉ የነበረው የገንዘብ ርዳታ ለኢየሱስና ለሐዋርያቱ ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው:: ጴጥሮስ፣ እንድርያስ፣ ያዕቆብና ዮሐንስ በቅፍርናሆም ከነበረው ዓሣ ማጥመድ ሥራቸው የሚያገኙት መጠነኛ ድጐማ ሳይኖርም አይቀርም:: ከዚህና ከዚያ የሚገኘው ገንዘብ በአስቆሮቱ ይሁዳ ኀላፊነት ይቀመጥና ለምግብ፣ ለቀረጥ፣ ለአንዳንድ ነገሮች አቅርቦት፣ ለልብስና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለማረፊያ ቦታ ይከፈል ነበር::

**§ 61**
**መንፈስ ቅዱስን መስደብ**
**(ማቴ 12÷22-37፤ ማር 3÷20-30፤ ከሉቃ 11÷14-23 ጋር ያነ)**

[ማር3:][20]ከዚያም ኢየሱስ ወደ አንድ ቤት ገባ፤ እርሱና ደቀ መዛሙርቱ ምግብ መብላት እንኳ እስኪሳናቸው ድረስ ሕዝቡ እንደ ገና በብዛት ተሰበሰበ:: [21]ሁኔታውን የሰሙ ዘመዶቹም፣ «አእምሮውን ስቶአል» በማለት ይዘውት ለመሄድ ወደሰበት መጡ::

[ማቴ 12:][22]ከዚህ በኋላ በጋኔን ተይዞ ማየትና መናገር የማይችል ሰው ወደ እርሱ አመጡ፤ ኢየሱስም ፈወሰው፤ ሰውየውም ማየትና መናገር ቻለ:: [23]ሕዝቡም ሁሉ ተደንቀው፣ «ይህ ሰው የዳዊት ልጅ ይሆንን?» አሉ::

የኢየሱስ አገልግሎት አደገኛና አጣብቂኝ ሁኔታ ውስጥ ገብቶ ነበር:: ደቀ መዛሙርቱ እርሱ በትክክል ማን እንደ ሆነ ያውቁ ዘንድ እየጣረ ነበር:: በዚሁ ጊዜ ደግሞ እርሱን በመንካት ፈውስ ማግኘት በሚፈልጉ ሰዎች ተጨናንቋል:: እርሱን ባልተቀበሉና ከኢየሩሳሌም በመጡ ፈሪሳውያንም ለጥያቄ ተዳርጎ ነበር:: ቤተሰቦቹ[120] ስለ ነበረበት ሁኔታ በመስማታቸው ወደ ነበረበት ቦታ መምጣታቸውን እዚህ ላይ እናያለን:: ጤንነቱን ወይም ደኅንነቱን ሽፋን በማድረግ ደብቀው ሊወስዱትና ከነበረበት አጣብቂኝ ሊያወጡት ፈልገዋል::[121] ምግብ የሚበላበት ጊዜ እስኪያጣ ድረስ በሰዎች የሚፈለግ ሆኗል::[122]

በዚህ ጊዜ ወንድሞቹ እንኳ አላመኑበትም ነበር፤ ምናልባት ሳይቀኑበትም አልቀሩም (ዮሐ 7÷1-5):: ምናልባትም፣ «እስካሁን ድረስ ታግሠናል፤ ወዲያ ወዲህ ማለቱና ያገኘው ታዋቂነት ስለራሱ የተሳሳተ ግምት እንዲኖረው አድርጓል:: ወደ ልቦናው እስኪመለስ ድረስ ቤት ወስደን ጥቂት ጊዜ እንዲያርፍ ብናደርግ ሳይሻል አይቀርም» ብለው አስበው ይሆናል:: እንዲያውም ማርቆስ ታሪኩን የሚያቀርበው ኢየሱስ በብዔል ዜቡል ሥልጣን ተአምራት እንደሚያደርግ ፈሪሳውያን ባቀረቡበት ክስ ቤተሰቡም መወገናቸውን ነው:: የታሪኩ አወቃቀር ቤተ ሰቡ የፈሪሳውያንን አቋም መያዛቸውን የሚያመለክት ነው::


[120] ቃል በቃል፣ «የእርሱ የሆኑት::» «ቤተሰብ» (አመት)፣ «ዘመድ»፣ «ጓደኞች» ወይም «ወገኖች» ተብሎ ሊተረጐም ይችላል:: ቢያንስ ከሌሎች ይልቅ ለኢየሱስ ቅርብ የነበሩ ሰዎችን ያመለክታል::
[121] «መያዝ» የሚለው ግሥ፣ «ማሰር» እንደ ማለት ይሆናል (ማር 6÷17፤ 12÷12፤ 14÷1 ወዘተ):: እዚህ ላይ ኢየሱስን በኀይል ይዞ ለመውሰድ መፈለጋቸውን ነው የሚያመለክተው::
[122] ኢየሱስ አገልግሎቱ ስለበዛበት መመገብ አልቻለም፤ ኒውፌልድ ግን ሌላ አማራጭም አቅርቧል:: በሁለቱ ኪዳኖች መካከል የተጻፉ መጻሕፍት ጾም አጋንንት ለማስወጣት ከሚያስፈልጉ ዝግጅት አንዱ እንደ ነበር ያቀርባሉ:: ኢየሱስ በእርግጥም እየጾመ ከነበረ ከዐውዱ ጋር በጣም ይስማማል ማለት ነው:: አጋንንት የማውጣት ሥርዓት አንዳንድ እንግዳ ነገሮች የሚከሰቱበት ስለ ነበር ለቤተ ሰቡ መደንገጥ ምክንያቱ ይኸው ሳይሆን እንዳልቀረ ማሰብ ይቻላል::



የኢየሱስ ሥራ ስለ ማንነቱም ሆነ ጤነኛነቱ መከላከያ ሊሆን የሚችል ነበር (ከዮሐ 5÷36 ጋር ያነ):: ከሰውየው ጋኔን በማውጣት ዓይኑ እንዲበራና አንደበቱ እንዲፈታ ማድረጉ በኢየሱስ ላይ የተነሳውን ክስ ጸጥ ማሰኘት ይገባው ነበር:: ሕዝቡ ሁኔታውን ሁሉ በአንክሮ እያዩ ነበር:: «ይህ ሰው የዳዊት ልጅ ይሆንን?» በማለት ያቀረቡት ጥያቄ አሉታዊ መልስ እንደሚጠብቅ ዓይነት ቢሆንም ኢየሱስ መሲሕ መሆኑን በግልጽ የሚያመለክት ነው::[123] ይህ ሁኔታም በኢየሱስና በፈሪሳውያን መካከል ክርክር እንዲፈጠር መድረክ አመቻችቷል:: እነርሱም ሰዎች በኢየሱስ ማመናቸውን ማስቀምም ሆነ፣ ጩርሶ እንደሌለ በመቁጠር ከችግሩ ማምለጥ አይችሉም::

ማቴ 12÷24-28፤
ከማር 3÷22-23፤
ሉቃ 11÷20 ጋር





[24]ነገር ግን ፈሪሳውያን (ከኢየሩሳሌም የወጡ ጸሐፍትም[ማር]) ይህን በሰሙ ጊዜ፣ «ይህ ሰው አጋንንትን የሚያወጣው በአጋንንት አለቃ በብዔልዜቡል ብቻ መሆን አለበት» አሉ::

[25]ኢየሱስም ሐሳባቸውን ዐውቆ (በምሳሌ እንዲህ አላቸው[ማር]) እንዲህ አላቸው፤ «እርስ በርሱ የተከፋፈለ መንግሥት ሁሉ ይወድቃል፤ እርስ በርሱም የተከፋፈለ ከተማ ወይም ቤት አይጸናም:: [26]ሰይጣንም ሰይጣንን የሚያስወጣ ከሆነ፣ እርስ በርሱ ተለያይቷል ማለት ነው፤ እንዲህ ከሆነ ደግሞ መንግሥቱ እንዴት ጸንቶ ሊቆም ይችላል? [27]እኔ አጋንንትን የማስወጣው በብዔልዜቡል ከሆነ ልጆቻችሁ[124] በምን

[123] «የዳዊት ልጅ» የተሰኘው መጠሪያ በማቴዎስ ወንጌል ስለ ኢየሱስ ለመግለጽ ሰባት ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል:: የኢየሱስ የዘር ሐረግን ዝርዝር (1÷1) እና በድል ወደ ኢየሩሳሌም ከገባበት ሁኔታ ውጪ (21÷9) ሁሌም ከፈውስ ጋር በተያያዘ መንገድ ነበር ጥቅም ላይ የዋለው (9÷27፤ 12÷23፤ 15÷22 20÷30-31፤ 21÷15):: ስለሆነም «የዳዊት ልጅ» የሆነው መሲሕ እንደሚፈውስ ሕዝቡ ሲጠብቁ ነበር ማለት ነው:: D.C. Duling, "The Therapeutic Son of David: An Element in Matthew's Christological Apologetic," *NTS* 24 (1978): 392-410.
[124] «ልጆቻችሁ» የሚለው ቃል በቃል የማንነታችሁ ተከፋዮች ማለት ነው::

ሲያስወጧቸው ነው? ስለዚህ ልጆቻችሁ ይፈርዱባችኋል:: [28]ነገር ግን እኔ አጋንንትን የማስወጣው በእግዚአብሔር መንፈስ (ጣት[ሉቃ]) ከሆነ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ መጥታለች::

ብዔልዜቡል የከነዓናውያን ጣዖት ሲሆን፣ የስሙ ትርጉምም የቤቱ ወይም የመቅደሱ ጌታ ማለት ነው:: ምናልባትም የአጋንንት አለቃን የሚወክል ይሆናል (ከማቴ 10÷26፤ 12÷25፣26፤ ማር 3÷22፣27 ጋር ያነ) አይሁዳውያን ስሙን ጥቂት ለወጥ በማድረግ ለፌዝ ይጠቀሙበታል፤ በዚህ ሁኔታ ብዔልዜቡል የሚለው ስያሜ ትርጉም 'የዝንቦች ጌታ' የሚል ይሆናል (ከ2ነገ 1÷2-16 ጋር ያነ)::

በኢየሱስ ላይ የቀረበው ክስ ግልጽ ነበር:: ኢየሱስ አጋንንትን ሲያስወጣ የነበረው በእግዚአብሔር ኀይል ሳይሆን፣ በሰይጣን ኀይል ነው የሚል ነው:: ኢየሱስ ግን ክሱን በመቃወም ሁለት ምክንያታዊ ማረጋገጫዎች አቀረበ፤ በመጀመሪያ ደረጃ አጋንንቱ እንዲወጡ የሚፈቅደው ሰይጣን የራሱን ሥራ እያፈረሰ ነው:: ሰይጣን አጋንንት እንዳይወጡ እንጂ እንዲወጡ አይፈልግም:: ኢየሱስ የሰይጣን አገልጋይ ነው ማለት ፈጽሞ የማያስኬድ ነው::

በሁለተኛ ደረጃ ኢየሱስ ኀይል ያገኘው ከሰይጣን ከሆነ፣ ሌሎች አይሁዳውያን አጋንንት አውጪዎች ኀይል የሚቀበሉት ከማን ሊሆን ነው?[125] ስለሆነም ክሱ እነርሱንም ይመለከታል ማለት ነው:: ፈሪሳውያን «የልጆቻቸው» ማንነት ተከፋዮች እንደ መሆናቸው መጠን አይሁዳውያን አጋንንት አስወጪዎችን የሚከሱ ከሆነ ከሰይጣን ኀይል በመቀበላቸው ራሳቸውን እያወገዙ ነው ማለት ነው::

ያቀረቡት ክስ ትክክል ካልሆነስ? ኢየሱስ አጋንንትን የሚያስወጣው በእግዚአብሔር መንፈስ ከሆነስ? እንዲህ ከሆነ የሚመጣውን መንግሥትና የእግዚአብሔርን ኀይል እየተቃወሙ በመሆኑ ሰዎቹ ከፍ ያለ ችግር ውስጥ ሊወድቁ ነው::

*ማቴ 12÷29-32*
*ከሉቃ 11÷21-22፣*
*ማር 3÷29-30 ጋር*

[29]ወይስ አንድ ሰው ወደ ኀይለኛ ሰው ቤት ገብቶ ንብረቱን ለመዝረፍ ቢፈልግ፣ አስቀድሞ ያንን ኀይለኛ ሰው ሳያስር እንዴት አድርጎ ይሳካለታል? (ብርቱ ሰው በሚገባ ታጥቆ ቤቱን ከጠበቀ፣ ንብረቱ በሰላም ይቀመጣል:: ነገር ግን ይበልጥ ብርቱ የሆነ ሰው መጥቶ ካጠቃውና ካሸነፈው ታምኖበት የነበረውን ትጥቁን ያስፈታዋል፤ ምርኮውንም ወስዶ ለሌሎች ያካፍላል[ሉቃ])::

[30]ከእኔ ጋር ያልሆነ ሁሉ ይቃወመኛል፤ ከእኔም ጋር የማይሰበስብ ሁሉ ይበትናል:: [31]ስለዚህ እላችኋለሁ፤ ኀጢአት መሥራትና የስድብ ቃል ሁሉ መናገር ለሰዎች ይቅር ይባልላቸዋል፤ ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚነገር የስድብ ቃል (የዘላለም ኀጢአት ዕዳ ይሆንበታል እንጂ[ማር]) ይቅር አይባልም:: [32]ማንም ሰው በሰው ልጅ ላይ የሚናገረው ክፉ ቃል ይቅር ይባላል፣ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚናገረው ክፉ ቃል ግን በዚህም ሆነ በወዲያኛው ዓለም ይቅር አይባልም:: (ይህንንም ያለው፣ «ርኩስ መንፈስ አለበት» ስላሉት ነበር::[ማር])

ኢየሱስ አጋንንትን የሚያስወጣው በሰይጣን ኀይል አለመሆኑን ተናግሮአል:: ሰይጣንን ባዶ ለማስቀረት ከእርሱ የበለጠ ጉልበት አለው:: ሰይጣን «ኀይለኛ» የተባለው ሰው ነው፣ ኢየሱስ ግን ሰይጣንን ያሰረው

---

[125] R.Shirock, "Whose Exorcists Are They? The Referents of Hoi Huioi Humon at MT 12:27 & LK 11:19," *JSNT* 46 (1992): 41-51 ላይ እንደሚለው ኢየሱስ የተናገረው ስደቀ መዛሙርቱ እንጂ ለአይሁዳውያን አጋንንት አውጪዎች አልነበረም፤ (1) አዲስ ኪዳን በየትም ቦታ አይሁድ አጋንንት አውጪዎች እንዳሉ በመደገፍ አይናገርም:: (2) በኋላ ላይ ፍርድ ለዐሥራ ሁለቱ ይሰጣል (ማቴ 19÷28፤ ሉቃ 22÷30):: (3) ሐዋርያቱ አጋንንት ሲያስወጡ ከነበረበት የስብከትና ፈውስ አገልግሎት ገና መመለሳቸው ነበር:: ስለዚህም ኢየሱስ እነዚህ እኔ የማደርገውን የሚያደርጉ ደቀ መዛሙርቴ የእናንተው ዘሮች ናቸው፤ ታዲያ፣ ሁላችንም ሰይጣንን እያገለገልን እንደሆነ ነው የምትከሱን?» ማለቱ እንደ ነበር ማንም መረዳት ይችላል:: ዮሐንስ አፈወርቅም ሆነ የጥንት ቤተ ክርስቲያን አባቶች በዚህ አተረጓጎም ይስማማሉ::

ነው (ከይሁዳ 6፤ ራእ 20÷2 ጋር ያነ):: በተጨማሪም ከኢየሱስ ጋር አብረው ሰይጣንን የማይበዘብዙ ሁሉ ከእርሱ ጋር አይደሉም ማለት ነው:: የታሰረ ኀይለኛ ሰው ቢኖርና እርሱን ያሰረ ሌላ ኀይለኛ ሰውም ቢኖር ከየትኛው ጋር ትወግናላችሁ? ኢየሱስ፣ «ከእኔ ወይም ከእርሱ ጋር መወገን ትችላላችሁ? በማለት እየተናገረ ነበር፤ ምንም እንኳ ንግግሩ ጸሐፍትና ፈሪሳውያን ላይ ያነጣጠረ ቢሆንም፣ በዚያ ቦታ ለነበሩ ሁሉ ምርጫ ቀርቦላቸዋል:: ከሁለቱ አንዱ ጋር መወገን ነበረባቸው::

በተለያየ ምክንያት ኢየሱስን በመቃወም የጸኑ ፈሪሳውያን፣ መንፈስ ቅዱስን ከመስደብ ያላነሰ ኀጢአት ለመፈጸም ከአጋንንት ጋር ወግነው ነበር:: ሌላውን መቋወም ወይም መንቀፍ ስድብ ሊሆን ይችላል:: ኢየሱስ አጋንንትን ያስወጣው በእግዚአብሔር ኀይል ነበር:: ፈሪሳውያን ግን በቡዔልዜቡል (ሰይጣን) ኀይል ነው ብለዋል:: ስለሆነም ቅዱሱን መንፈስ፣ ርኩስ መንፈስ በማለት ጠርተዋል ማለት ነው:: መንፈስ ቅዱስ ላይ የሚሰነዘር ስድብ ይቅርታ የሌለው ኀጢአት ነው (ከኢሳ 5÷20 ጋር ያነ)::

ኢየሱስን መሳደብ ይቅር ሊባል ሲችል መንፈስ ቅዱስን መስደብ ግን ይቅር የማይባለው ለምንድነው? እግዚአብሔር በሥጋ (በኢየሱስ አካል በኩል) ተገለጠ የሚለውን ጽንሰ ሐሳብ ለመረዳት የሚከብድና ለትችት የተጋለጠ ሊሆን እንደሚችል ይታወቃል:: ኢየሱስ ስለ ራሱ የተናገረውን በተመለከተ በቂ ማስረጃ ካልቀረበ በቀር አንዳንዶች ሊጠራጠሩ እንደሚችሉ ግልጽ ነው:: ይሁን እንጂ መንፈስ ቅዱስን፣ በተለይም አጋንንት ሲያስወጣ እያየን፣ የምንሳደብበት ምክንያት መኖር የለበትም:: እንዲህ ያለው ስድብ ወይም አለማመን ሆን ብሎ እግዚአብሔር ያቀረበውን ማስረጃ አለመቀበል ነው:: ያለ እንዲህ ዓይነቱ ማረጋገጫ፣ ጽናት ያለው እምነት ሊኖር አይችልም:: ያለ እምነትም የኀጢአት ይቅርታ የለም::



ስለሆነም ይቅር የማይባለው አፍ አውጥቶ መሳደቡ ሳይሆን ሆን ተብሎ ላለማመን የሚኖረን የልባችን ዝንባሌ ነው:: አንድ ሰው ወደ ሞት የሚያመራው (ዮሐ 5÷16)፣ በንስሐ መመለስ የማይችልበት ደረጃ ላይ የሚደርሰው በእንዲህ ያለው ኀጢአት ምክንያት ነው (ዕብ 6÷4-6):: አንዳንዶች መንፈስ ቅዱስን የተሳደቡ ስለሚመስላቸው ይጨነቃሉ:: ይሁን እንጂ ጉዳዩ ይህን ያህል ካሳሰባቸው ሆን ብለው ያንን ኀጢአት እንዳልፈጸሙ ማረጋገጫ ሊሆናቸው ይችላል:: ዋናው ችግር ሆን ብሎ የእግዚአብሔርን ዓላማ መቃወም እንጂ (ዘኍ 15÷30-31 ጋር ያነ) የተለየ ቃል ወይም የተለየ ድርጊት አይደለም::

መንፈስ ቅዱስ ላይ የሚፈጸሙ ጥቂት ኀጢአቶች:- ዓመፅ (ኢሳ 63÷10)፣ መዋሸት (ሐሥ 5÷3-9)፣ መቃወም (ሐሥ 7÷51)፣ ለራስ ወዳድ ዓላማ መጠቀሚያ ማድረግ፣ (ሐሥ 8÷18-22)፣ ማሳዘን (ኤፌ 4÷30) ማጥፋት (1ተሰ 5÷19) አለመታዘዝ (ዕብ 10÷29) ናቸው:: መሳደብ ይቅር የማይባል ብቸኛ ኀጢአት ነው (ማቴ 12÷31-32፤ ማር 3÷29፤ ሉቃ 12÷10)::

**ማቴ 12÷33-37**

33ዛፍ ሁሉ በፍሬው ስለሚታወቅ፣ መልካም ፍሬ እንድታገኙ መልካም ዛፍ ይኑራችሁ፤ መጥፎ ዛፍ ቢኖራችሁ ግን መጥፎ ፍሬ ታገኛላችሁ:: 34እናንተ የእፉኝት ልጆች፤ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ መልካም ነገር መናገር እንዴት ትችላላችሁ? በልብ ውስጥ የሞላውን ይናገራዋልና:: 35መልካም ሰው በልቡ ካከማቸው መልካም ነገር በጎ ነገር ያወጣል፤ ክፉ ሰውም በልቡ ካከማቸው ክፉ ነገር መጥፎ ነገር ያወጣል:: 36ነገር ግን እላችኋለሁ፤ ሰዎች ስለ ተናገሩት ከንቱ ቃል ሁሉ በፍርድ ቀን ይጠየቁበታል:: 37ምክንያቱም ከቃልህ የተነሣ ትጸድቃለህ፤ ከቃልህም የተነሣ ይፈረድብሃልና::

ከአንደበታችን የሚወጡ ቃላት ኀይል አላቸው! ፍሬ የዛፉን መልካምነት እንደሚሳይ ሁሉ፣ ከአንደበታችን የሚወጣ ቃልም እንዲሁ

የልባችንን መልካምነት ያሳያል:: ንግግሮቻችን ሐሳቦቻችንን ያመለክታሉ፤ ድርጊታችን ምን ሊሆን እንደሚችል ይጠቁማሉ፤ በምንናገረው መሠረት ይፈረድብናል::

**§ 62**
**ፈሪሳውያን ምልክት በመጠየቃቸው ተገሠጹ**
**(ማቴ 12÷38-45፤ ሉቃ 11÷24-36 ጋር ያነ)**

ኢየሱስ አጋንንት የሚያስወጣው በእግዚአብሔር ኀይል መሆኑን ተናግሮአል:: ስለዚህም ፈሪሳውያን ለዚህ ማረጋገጫ የሚሆን ከሰማይ አንድ ዐይነት ምልክት እንዲያሳያቸው መጠየቃቸው የሚጠበቅ ነበር ማለት ነው:: እንደዚህ ያለ ነገር ሲያነሡ የመጀመሪያ አይደለም:: በኢየሩሳሌም ፈሪሳውያን ምልክት እንዲያሳያቸው መጠየቃቸውን ቀደም ሲል አይተናል (ዮሐ 2÷18-23):: እነዚህ ሁለቱ በተለያየ ምክንያት ተጓዳኝ ናቸው ማለት ይቻላል፤ (1) የማያምኑ ምልክት እንዲያደርግ የጠየቁት ታላቅ፣ «ተአምር» ማድረጉን ተከትሎ ነበር (ዮሐ 2÷12-17 ኢየሱስ መቅደሱን አነጻ፤ እዚህ ላይ ግን ጋኔን የነበረበትን ዲዳና ዐይነ ስውር ሰው ፈወሰ)፤ (2) በሁለቱም ጊዜ ትንሣኤው የመጨረሻ ተአምር መሆኑን አመለከተ እንጂ ተአምር ማድረግ አልፈለገም:: (3) የማመን ዝንባሌ ለነበራቸው ሁሉ በቂ ማረጋገጫ የሚሆን ተአምር ኢየሱስ እያደረገ ነበር (ለተመሳሳይ ሆኖም አጭር ገለጻ ማቴ 16÷1-4 ይመ)::

**ማቴ 12÷38-42**
**ከሉቃ 11÷16፣29 ጋር**

38 ከዚያም አንዳንድ የአይሁድ ሃይማኖት መምህራንና ፈሪሳውያን፣ «መምህር ሆይ፤ ከአንተ (ከሰማይ[ሉቃ]) ታምራዊ ምልክት ማየት እንፈልጋለን» አሉት::

(ብዙ ሕዝብ እየተሰበሰበ በሄደ ጊዜ[ሉቃ]) 39 እርሱ ግን መልሶ እንዲህ አላቸው፤ «ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክትን ይጠይቃል፤ ነገር ግን ከነቢዩ ዮናስ ምልክት



በስተቀር ሌላ ምልክት አይሰጠውም:: 40 ዮናስ በዓሣ አንበሪ ሆድ ውስጥ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንደ ቈየ፣ እንዲሁ የሰው ልጅ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት በምድር ሆድ ውስጥ ይቆያል:: 41 የነነዌ ሰዎች በፍርድ ዕለት ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥተው ይፈርዱበታል፤ እነርሱ በዮናስ ስብከት ንስሐ ገብተዋልና:: እነሆ፤ ከዮናስ የሚበልጥ እዚህ አለ:: 42 በፍርድ ዕለት የደቡብ ንግሥት ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥታ ትፈርድበታለች፤ የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት ከምድር ዳርቻ መጥታለችና:: እነሆ ከሰሎሞን የሚበልጥ እዚህ አለ::

የሕዝቡ ቍጥር እየበዛ የሄደው ከተፈጠረው የጋለ ክርክር የተነሣ ነበር፤ ክርክሩ የጀመረው ማቴዎስ 12÷24 (እና ሉቃ 11÷14) ላይ ነበር:: የጭቅጭቁ ምክንያት ምን እንደ ነበር ለማወቅ ብዙ ሕዝብ ተሰብስቧል:: አንዳንዶች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ሲናገሩ ይሰማል፤ ኢየሱስም ጠንከር ባለ አነጋገር፣ «ክፉና አምንዝራ ትውልድ!» በማለት ተናግሮአል:: ጣዖት አምልኮንና አመንዝራነትን በተመለከተ የብሉይ ኪዳንን ንጽጽር ነበር የተጠቀመው:: ፈሪሳውያን እንደ ቀደሙት አባቶቻቸው ሁሉ ለሥልጣናቸውና ክብራቸው ሲሉ እንኳን የእግዚአብሔርን መልእክተኞች በሥጋ የተገለጠውን እግዚኦብሔር ሳይቀር ችላ ብለዋል::

ምልክትን መጠየቅ ክፋቱ ምን ላይ ነው? እግዚአብሔር በምልክቶች አማካይነት የመልእክተኞቹን ቃል ሲያጸና አልነበረም? አዎን:: ኢየሱስ ግን አምላክ መሆኑን በምልክቶቹ አማካይነት አሳይቶ ነበር:: ከጥቂት ጊዜ በፊት ከዲዳ ሰው ጋኔን ማውጣቱ ብቻ ሳይሆን፣ በገሊላም ሆነ በይሁዳ አያሌ ተአምራት አድርጐ ነበር፤ ውሃውን ወደ ወይን ጠጅ ለውጧል፤ የሰዎችን ሐሳብ ዐውቆአል፤ የተለያዩ ሕመሞችን ፈውሷል፤ አጋንንት አስወጥቷል፤ ለምጽ አንጽቶአል፤ ሽባና ዐይነ ስውር ፈውሷል፤ ሌላው ቀርቶ በናይን የሞተ ሰው እንኳ አስነሥቶአል:: እንግዲህ በዚህ ጊዜ ምልክት መጠየቅ ቀደም ሲል የተደረጉ ተአምራትን

አለማመን ነው የሚሆነው ማለት ነው:: ይፈልጋሉ፣ ያገኙትን ግን አክብረው አይዙም:: አለማመን ቀላል ኀጢአት ይመስላል፤ ሆኖም በጣም አደገኛ ነው::

ከሰማይ፣ ያም ከራሱ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሆነ ምልክት እንዲያሳያቸው ጠይቀዋል (ሉቃ 11÷16፤ ከዘፀ 19÷22-24፤ 16÷4፤ ኢያ 10÷12፤ 1ሳሙ 7÷9-10፤ 12÷16-18፤ 1ነገ 18÷36-38፤ 2ነገ 1÷10፤ ኢሳ 38÷8):: ምልክቶችን ማየት የሚጠየቀው በአራት ሁኔታዎች ነበር፤ (1) ትንቢትን ለማረጋገጥ፤ (2) ያልተለመደ ዐይነት ሁኔታን ለማጽናት (ከዮሐ 2÷18 ጋር ያነ)፤ (3) አስተምህሮአዊ ጉዳይን ለመደገፍ፣ (ለምሳሌ፣ ኀጢአትን ይቅር ማለት፤ ማር 2÷6) እና (4) መሲሕነትን ለማጽናት::[126] ምልክቱ በወቅቱ ከተነገረ ቃል ወይም ድርጊት ጋር የሚጣጣም መሆን አለበት:: ዓላማው ኀይልን ማሳየት ሳይሆን ተገቢ በሆነ መልኩ ነገርን ማጽናት ነው:: የተአምራቱ ዓላማ፣ «እነዚህ አሁን ከተናገርከው ጋር የሚጣጣሙ አይደሉም» የማለት ያህል ቀደም ሲል የተደረጉ የኢየሱስ ተአምራትን ችላ እንዲባሉ ማድረግ አይደለም:: ያም ሆኖ ማስረጃ እየጠየቁ የነበረው በኢየሱስ ማመን ስለ ፈለጉ አልነበረም:: እርሱን የሚነቅፉበትና ሕዝቡ እርሱን ከመከተል ወደ ኋላ እንዲል የሚያደርጉበትን ምክንያት ነበር የሚፈልጉት:: ይህን ካለፈው ክፍል በግልጽ ማየት ይቻላል::

የዮናስ ምልክት፣ ትንሣኤውን የሚመለከት መሆኑ ግልጽ ነው::[127] ዮናስ በጥቂቱና በቸልታ ቢሰብክም እንኳ የአረማዊቷ ከተማ

[126] O. Linten, “The Demand for a Sign from Heaven," *ST* 19 (1965):12-29.

[127] E.H. Merrill እንደሚለው የነነዌ ከተማ የተመሠረተችው በዓሣ አምላክ እንደ ሆነ ይታሰብ ነበር፤ ይኸው ጣዖት በዚያ ከተማ ይመለክ ነበር:: የዮናስም ከዓሣ ሆድ ውስጥ መተፋት ለነነዌ ሰዎች የተለየ ትርጉም ነበረው:: ("The Sign of Jonah" *JETS* 32/1 [Mar 1980]: 23-30.) J. Swetnam ግን የዮናስ ምልክት ነነዌ እንደምትገለበጥ የተናገረው ትንቢት በመሆኑ የኢየሩሳሌምን ውድቀት የሚያመለክት ትንቢት ነበር:: ያቺ በመጠኗ ከተማ በዚያ ተራ ስብከት አማካይነት ወደ ንስሐ ከመጣች፣ የኢየሱስን ስብከት ሰምታ ኢየሩሳሌም ወደ ንስሐ ባለመምጧቷ ይፈረድባታል ማለት ነው፤ ስለ ትንሣኤ አንስቶ የተናገረው በእያንዳንዱ ከተማ ላይ የተነገረውን ትንቢት በማነጻጸር ለሚሰጠው ገለጻ እንደ ማነጻጸሪያ እንዲሆን ነበር (*Biblica* 68 [1987]: 74-79).



ሰዎችን በሙሉ ወደ ንስሐ አምጥቷል:: ኢየሱስ ግን በአያሌ ተአምራት፣ አስደናቂ ስብከቶችና ከነቀፋ በጠራ ሕይወት ምርጥ ሕዝብ የተባሉትን ወደ ንስሐ ማምጣት አልቻለም:: ስለሆነም የነነዌ ሰዎች እምነትን ሲያሳዩ፣ አይሁዳውያን ግን አለማመንን ነበር ያንፀባረቁት::

ማቴዎስ 12÷40 የዮናስ ምልክት ሦስት ቀንና ሌሊት በዐሣ ዐንበሪ ሆድ ውስጥ ማሳለፉን እንደሚያካትት ያሳያል:: ኢየሱስም ሦስት ቀንና ሌሊት መቃብር ውስጥ ካሳለፈ በኋላ ከሞት መነሣቱ ታላቁ ምልክት ይሆናል::[128] ይሁን እንጂ፣ ሌላው ቀርቶ ትንሣኤው እንኳ፣ የእነዚያ ሰዎችን አለማመን ማስወገድ አልቻለም (ሉቃ 16÷31)::

ንግሥተ ሳባ (1ነገ 10÷1) በአይሁዳውያን አለማመን ላይ የምትመሰክር ሌላ ምስክር ናት: አረማዊቷ ሴት በሰብዓዊ ጥበብ ተማርካ ነበር:: የኢየሱስ መንፈሳዊ ጥበብ ግን ከሰሎሞን ዓለማዊ ጥበብ የበለጠ ነበር::[129] ንግሥተ ሳባ ከሰሎሞን ለመስማት ረጅም መንገድ ተጉዛለች:: ይህ ትውልድ ግን ኢየሱስ ወደ ደጃቸው ቢመጣ እንኳ መቀበል የፈለገ አይደለም:: በተመሳሳይ መልኩ፣ ዮናስ አርባ ቀን ያህል በቸልታ ሰበከ እንጂ ምንም ተአምር አላደረገም ነበር:: ኢየሱስና ሐዋርያቱ ግን የአርባ ዓመት ስብከታቸውን በታላላቅ ተአምራት ቢያረጋግጡም፣ ኢየሩሳሌም

[128] የግድ 24 ሰዓት ያላቸው ሦስት ቀኖች መሆን የለበትም፤ ይህ እንዲሁ በደፈናው ለመናገር ያህል እንደ ነበር ኢየሱስ ከተጠቀመበት አነጋገር ሁኔታ ማየት ይቻላል፤ «በሦስተኛው ቀን «ከሦስት ቀን በኋላ»፣ «ሦስት ቀን ሦስት ሌሊት»::

[129] በሁለቱ ኪዳኖች መካከል በተጻፉ ጽሑፎች መሠረት ሰሎሞን ከፍተኛ የአስማትና አጋንንት የማስወጣት ችሎታ እንደ ነበረው ተገልጿል፤ ኢየሱስ ግን አጋንንትን ያስወጣው በቃሉ ሥልጣን እንጂ በተለያየ ዓይነት ድግምት አልነበረም፤ ስለሆነም ሰሎሞንን አጋንንት ከማስወጣት ጋር በተያያዘ መልኩ በዚህ ክፍል መቅረቡ አግባብ ነው ማለት ይቻላል:: Larry Perkins "Greater Than Solomon (Mt 12:42), *TrinJ* 19/2 (1998): 207-217.

እስከ ተደመሰሰችበት ጊዜ ድረስ ተቀባይነት አላገኙም:: ስለሆነም እነዚህ አረማውያን ተነሥተው በአይሁድ አለማመን ላይ ይፈርዳሉ:: ዋናው ጉዳይ፣ ምንም እንኳ አይሁድ የበለጠ ዕድል ቢኖራቸውም፣ ይበልጥ ያሳዩት እምቢተኝነት ወደሚበልጥ ጥፋት እየሄዱ መሆናቸውን ማመልከቱ ነው (ከማቴ 10፥15፤ 11፥21-24 ጋር ያነ)::

43ርኩስ መንፈስ ከሰው ከወጣ በኋላ ዕረፍት ለማግኘት ውሃ በሌለበት ደረቅ ቦታ ይንከራተታል፤ የሚሻውን ዕረፍት ግን አያገኝም:: 44ከዚያም፣ 'ወደ ነበርሁበት ቤት ተመልሼ ልሂድ' ይላል፤ ሲመለስም ቤቱ ባዶ ሆኖ፣ ጸድቶና ተዘጋጅቶ ያገኘዋል:: 45ከዚያም ይሄድና ከራሱ የባሱ ሌሎች ሰባት ክፉ መናፍስት ይዞ ይመጣል፤ እነርሱም ሰውየው ውስጥ ገብተው ይኖራሉ:: የዚያም ሰው የኋለኛው ሁኔታ ከፊተኛው የከፋ ይሆናል:: በዚህ ክፉ ትውልድም ላይ እንዲሁ ይሆንበታል::

ማቴ 12፥43-45

በዘመኑ በነበረው የአይሁድ አፈ ታሪክ መሠረት አጋንንት በበረሓ (በሽንት ቤት፣ በረግረግ ቦታዎች፣ በባዶ ቤቶችና ከአንዳንድ ዛፎች ጥላ በታች) እንደሚኖሩ ይታሰብ ነበር:: አይሁድ አጋንንትን አስመልክቶ የተለያዩ ባሕላዊ እምነቶች ነበሯቸው:: ለምሳሌ ያህል፤ አጋንንት ረቂቅ ፍጥረቶች ቢሆኑ እንኳን አንድ ሰው ደጃፉ ላይ ዐመድ ካኖረ ሲነጋ የዶሮ የሚመስል የእግር ዱካቸውን ማየት እንደሚችል ያምኑ ነበር::

ኢየሱስ ከአጋንንት ጋር ወደ ተያያዘ ጉዳይ በመመለስ እየከፋ የመጣውን የአይሁድ ሕዝብ ዐመፅ ለማሳየት ተጠቅሞበታል:: አጋንንት የወጡለት ሰው በሕይወቱ የተፈጠረውን ባዶ ቦታ እንዲሞላ ያስፈልጋል፤ አለበለዚያ ግን ከበፊቱ የሚከፋ አጋንንት ባዶ ሆኖ፣ ጸድቶና ተዘጋጅቶ በሚያገኙት መኖሪያ ውስጥ መኖር ይጀምራሉ:: በተመሳሳይ መልኩ የአይሁድ ሕዝብ መንፈሳዊ ባዶነት በክርስቶስ



መሞላት ነበረበት:: በግብረ ገባዊ ሕይወት የፀዱ መሆን ብቻ በቂ አይደለም:: የፈሪሳውያን ዐይነት ንጽሕና አጋንንት መጥተው ውስጡ እንዲያደበቁ የሚጋብዝ ሽፋን ሊሆን ይችላል::

መግደላዊት ማርያም ሰባት አጋንንት ወጥቶላት ነበር (ሉቃ 8፥2):: በጌርጌሴኖን የነበረው ሰው የአጋንንት ጭፍራ ሰፍሮበት ነበር:: ይሁን እንጂ እዚህ ላይ ሰባት ቊጥር የሚያመለክተው እጅግ የከፋ ዐመፅን ሊሆን ይችላል:: ሆኖም እንዲህ ባለው ጉዳይ ከሚገባ በላይ ርቀን መሄድ የለብንም::

**§ 63**
**እውነተኛ የኢየሱስ ቤተ ሰቦች**
**(ማቴ 12፥46-50፤ ማር 3፥31-35፤ ሉቃ 8፥19-21)**

ማርቆስ ቀደም ሲል ስለ ኢየሱስ ቤተ ሰብ ተናግሮ ነበር (ማር 3፥20-21):: ስለ ቤተ ሰቡ እየተናገረ እያለ ኢየሱስ አጋንንትን ያስወጣ የነበረው በቡዔልዜቡል ነው የሚለውን ክስ በመካከሉ አስገብቶአል::[130] ስለሆነም ኢየሱስ ተቃውሞ የተነሣበት ከሁለት አቅጣጫ እንደ ነበር ማየት ይቻላል:: የሃይማኖት መሪዎቹም ሆነ ቤተ ሰቡ በተሳሳተ መንገድ ስለ ተረዱት የአእምሮ ችግር እንደ ነበረበት አስበዋል::

46ኢየሱስ ለሕዝቡ ሲናገር ሳለ፣ እናቱና ወንድሞቹ ሊያነጋግሩት ፈልገው በውጭ ቆመው ነበር (ከሕዝቡ ብዛት የተነሣ ወደ እርሱ ሊቀርቡ አልቻሉም[ሉቃ]) (በውጭ ቆመውም ሰው ልከውበት አስጠሩት[ማር]):: 47አንድ ሰውም፣ «እነሆ፣ እናትህና ወንድሞችህ ሊያነጋግሩህ ፈልገው በውጭ ቆመዋል» አለው:: 48ኢየሱስም፣ «እናቴ ማን ናት? ወንድሞቼስ እነማን ናቸው?» ሲል መለሰለት::

**ማቴ 12፥46-48 ከሉቃ 8፥19፤ ማር 3፥31 ጋር ያነ**

---

[130] ይህ ለጉዳዩ ጠንከር ያለ አጽንዖት ለመስጠት ማርቆስ የተጠቀመበት የተለመደ አሠራር ነው (ከማር 4፥1-20፤ 5፥21-43፤ 6፥7-29፤ 11፥12-25፤ 14፥1-11፤ 14፥53-72 ጋር ያነ)::

[34]በዙሪያው ወደ ተቀመጡትም በመመልከት ... ማር 3÷34

[49]በእጁም ወደ ደቀ መዛሙርቱ እያመለከተ ማቴ 12÷49
እንዲህ አለ፤ «እናቴና ወንድሞቼ እነዚህ ናቸው፤

[21]«እናቴና ወንድሞቼስ የእግዚአብሔርን ቃል ሉቃ 8÷21
ሰምተው የሚያደርጉት ናቸው» አላቸው::

ኢየሱስ ያዕቆብ፣ ዮሴፍ፣ ይሁዳና ስምዖን የሚባሉ አራት ወንድሞች ነበሩት (ማቴ 13÷55):: እኅቶችም ነበሩት:: ስለ ኢየሱስ እያሰቡ ነበር:: በጣም ሥራ ስለበዛበትና የሚያርፍበትና የሚመገብበት ጊዜ እንኳ በማጣቱ አእምሮው ሳይነካ እንዳልቀረ ገምተዋል (ማር 3÷20-21):: ገና በእርሱ ያላመኑ ወንደሞቹ (ዮሐ 7÷1-4፤ ከ1ቆሮ 15÷7 ጋር ያነ) ረጋ እንዲልና እየበረታ ስለሄደው የፈሪሳውያን ተቃውሞ ጥንቃቄ እንዲያደርግ ሊነግሩት እዚያ ተገኝተዋል:: የኢየሱስ አባት ግን በቦታው እንዳልተገኘ መረዳት ይቻላል:: ምናልባትም በዚያ ጊዜ ዮሴፍ ሳይሞት አልቀረም:: ይሁን እንጂ የኢየሱስ አባት እግዚአብሔር ብቻ ነው (ከማቴ 23÷9 ጋር ያነ):: የተቀሩት ቤተ ሰቡ ለእግዚአብሔር ቃል ታማኝ የሆኑት ናቸው::

ኢየሱስ ለቤተ ሰቡ ደንታ ቢስ መሆኑ አልነበረም:: አይሁድ ለወላጆቻቸው ከፍ ያለ አክብሮት ነበራቸው:: ይልቁንም የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው ለሚታዘዙ ያለውን ላቅ ያለ ደረጃ ማመልከቱ ነበር:: «በጥምቀት አማካይነት ከሚገኘው ከእግዚአብሔር ቤተ ሰብ ጋር ከሚደረገው ትስስር ይልቅ የቤተ ሰብ ትስስር እንደሚበልጥ ለማመልከት፣ 'ደም ከውሃ ይወፍራል' እየተባለ የሚጠቀሰው የቆየ ብሒል የተሳሳተ አባባል ነው!» (በትለር፣ ገጽ 140)::



§ 64
በምሳሌዎች የቀረበ ስብከት
(ማቴ 13÷1-3፤ ማር 4÷1-2፤ ሉቃ 8÷4)

[1]በዚያኑ ቀን ኢየሱስ ከቤት ወጥቶ በባሕሩ ዳር
ለመገብ ተቀመጠ:: [2]ብዙ ሕዝብም ስለ ከበበው በባሕሩ
ዳር ትቶአቸው ጀልባ ላይ ወጥቶ ተቀመጠ:: [3]ብዙ
ነገሮችን በምሳሌ እንዲህ ሲል ነገራቸው፤

ለኢየሱስ ሥራ የበዛበት ቀን ነበር፤[131] ጋኔን የነበረበት ዕይነ ስውርና ዲዳ የተፈወሰውና ይህንኑ ተከትሎ መንፈስ ቅዱስን ስለ መሳደብ የተነሣው ውይይት የተደረገው በዚሁ ቀን ነበር (§ 61)፤ ከሰማይ ምልክት እንዲያሳያቸው ፈሪሳውያን ያቀረቡትን ጥያቄ ያልተቀበለው (§ 62)፤ በኀይል ይዘው ሊወስዱት ባሰቡ ዘመደቹ እንኳ የተናቀው (§ 63) እና በገሊላ ባሕር ዳር በምሳሌዎች ያስተማረውም በዚሁ ቀን ነበር (§ 64):: በዚያው ምሽት ማዕበሉን ፀጥ አድርጓል (§ 65)፤ እኩለ ሌሊት ላይም በጌርጌሴኖን ብዙ አጋንንት የነበሩበትን ሰው ፈውሶአል (§ 66)::

ይህ የኢየሱስ የባሕር ዳርቻ ስብከት የተለመደ ነበር:: ቤቱም ሆነ ጀልባው የጴጥሮስ እንደ ሆነ ይታሰባል:: ቀደም ሲል እንደ ተመለከትነው ኢየሱስ ጀልባን እንደ መድረክ፣ የባሕሩን ዳርቻ ደግሞ ሕዝቡን እንደሚያስተምርበት አዳራሽ ይጠቀም ነበር:: በምሳሌዎች አማካይነት መስበክ ለኢየሱስ አዲስ ነገር አልነበረም:: ቀደም ሲልም በምሳሌዎች ተጠቅሞአል (ማቴ 7÷24-27፤ 9÷16-17፤ 11÷16-19፤ 12÷29):: በዚህ ጊዜ ግን ስብከቶቹ ሁሉ ተከታታይ ምሳሌዎች ነበሩ:: ከዚህ በኋላ ይህ በኢየሱስ የማስተማር ሥራ ውስጥ ሰፋ ያለውን ስፍራ እንደሚይዝ እንመለከታለን:: ምሳሌዎቹ በሰዎች መካከል የአመለካከት

[131] The NIV is interpretive at this point. It inserts the word "same" in "that same day." We agree with the interpretation but question its place in a translation.

ልዩነት እንዲኖር ያደርጋሉ፤ አንዳንዶች ግራ ሲጋቡ፣ ሌሎች ግን ደስ ተሰኝተዋል::

ዌንሀም ማቴዎስ በዚህ ስብከት ያሉ ምሳሌዎችን (ማቴ 13) በእንዴት ዐይነት ሁኔታ እንዳቀናጃቸው ጠቃሚ ዝርዝር አቅርቧል::[132]

ሀ. የዘሪው ምሳሌ - የመንግሥቱን ቃል የሚሰሙትን አስመልክቶ የቀረበ::



ለ. የምሳሌዎችን አስፈላጊነትና ቀደም ሲል የተናገረውን ምሳሌ ትርጉም እንዲገልጽላቸው ደቀ መዛሙርቱ ያቀረቡት ጥያቄና ኢየሱስ የሰጠው መልስ::

ሐ. የእንክርዳዶቹ ምሳሌ - ክፉና መልካምን አስመልክቶ የመንግሥቱ ምሳሌ::

መ. የሰናፍጭ ቅንጣትና እርሾ ምሳሌ - ስለ መንግሥቱ ተጓዳኝ ምሳሌዎች::

ሠ. ስለ ሕዝቡ የተናገረው መደምደሚያና የእንክርዳዱ ትርጉም::

መ. የተደበቀ ሀብትና የዕንቁው ምሳሌ - ስለ መንግሥቱ ተጓዳኝ ምሳሌዎች::

ሐ. የመረቡ ምሳሌ - ክፉና መልካምን አስመልክቶ የመንግሥቱ ምሳሌ::

ለ. ምሳሌዎቹን ተረድተው እንደ ሆነ ኢየሱስ ላቀረበው ጥያቄ ደቀ መዛሙርቱ የሰጡት መልስ::

ሀ. የኦሪት ሕግ መምህር - የመንግሥተ ሰማይን ምሥጢር የመረዳት ምሳሌ

---

[132] D. Wenham, "The Structure of Matthew XIII," *NTS* 25 (1979): 517-518.



እያንዳንዱን ምሳሌ ከመመርመራችን በፊት ኢየሱስ ምሳሌዎቹን የተጠቀመበትን ሁኔታና የሰጠውን ትርጉም መረዳት ይኖርብናል::[133]

1. ኢየሱስ የተጠቀመው የአይሁድ ሃይማኖት መምህራን «በደፈናዊ» ምሳሌዎቹን በሚረዱበት ሁኔታ ነበር:: ጌቶች አባቶችና ነገሥታት እግዚአብሔርን ይወክላሉ:: አገልጋዮችና ልጆች የእግዚአብሔርን ሕዝብ ወይም ረዳቶቹን ይወክላሉ:: መከር ፍርድን ይወክላል:: ግብዣ የመሲሑን ግብዣ ድግስ ይወክላል::
2. የኢየሱስ ምሳሌዎች ከሌሎቹ የሃይማኖት መሪዎች ምሳሌዎች የተለዩ ነበሩ፤ (ሀ) ያስተማረበት ፅንስ ሐሳብ በጣም የተለየ ነበር፣ (ለ) ምሳሌዎቹን አንዳንድ ነገሮችን ለመግለጽ፣ ሌሎቹን ግን ለመሰወር ተጠቅሞባቸዋል::
3. የግሪኩ ፓራቦሌ (*parabole*) እና የዕብራይስጡ ማሻል (*mashal*) ጥቅም ላይ የዋሉት አንዳንድ የአነጋገር ፈሊጦችን ለማመልከት ቢሆንም እንደ አማርኛው በጣም የተለያዩ አይደለም:: ስምሳሌ ያህል፣ ምሳሌዎችን፣ ተመሳስሎዎችን፣ ውስጠ ወይራ አነጋገሮችን፣ ተረቶችን፣ ዘይቤያዊ አነጋገሮችን፣ ዕንቆቅልሾችን፣ ትእምርቶችንና ሌሎችንም ወዘተ ይወክላሉ::
4. የኢየሱስ ምሳሌዎች አንድን ነገር ለማብራራት ብቻ ሳይሆን፣ የመልእክቱን ጭብጥ ሐሳብ ለማመልከትም ነበር የተነገሩት::
5. የኢየሱስ ምሳሌዎች መነሻ ዕለት በዕለት የሚገጥሙት ሰዎች ወይም ነገሮች ነበሩ:: እንዲያውም ኤደርሼይም እንደሚለው ከሆነ ኢየሱስ እያንዳንዱን ምሳሌ ሲናገር በምሳሌዎቹ ያነሳቸው ነገሮችን በጣቱ እያመለከተ ሳይሆን አይቀርም፤ ለምሳሌ - ሜዳ፣ እንጀራ የምትጋግር ሴት፣ የስንዴ ቡቃያ፣ የሰናፍጭ ተክልና መረብ::

---

[133] ምሳሌዎችን በተመለከተ ከC.L. Blomberg, *Interpreting the Parables* (Downers Grove: InterVarsity, 1990) ይመ::

6. በምሳሌው ለሚያነሳቸው ዋነኛ ገጸ ባሕርያት ወይም የገጸ ባሕርያት ስብስብ ብዙውን ጊዜ አንድ ዐቢይ ትርጉም ብቻ ተሰጥቷል።
7. እነዚህ ተከታታይ ወይም ተያያዥ ምሳሌዎች፣ ስለ «መንግሥቱ የተነገሩ» ናቸው። ሐሳባቸው ግልጽ ስለ ነበር ለጉዳዩ አዲስ የሆነ ሰው እንኳ በቀላሉ ሊረዳቸው ይችላል። የእግዚአብሔርን መንግሥት መንፈሳዊ ትርጉም መረዳት ለማይችሉ ግን ሐሳቡ ከመረዳት በላይ ይሆንባቸዋል።

ይህ ስብከት የተነገረው በገሊላ ባሕር ዳርቻ፣ ምናልባትም በቅፍርናሆም አጠገብ ሊሆን እንደሚችል ማቴዎስና ማርቆስ ያመለክታሉ። ኢየሱስ ከባሕሩ ዳርቻ ጥቂት ራቅ ብሎ ጀልባ ላይ ነበር። ብዙ ሕዝብ በባሕሩ ዳር ቆሞ ነበር። እነዚህ ሰዎች ሁሉ ከየት ነበር የመጡት? ኢየሱስ በተለያዩ ቦታዎች እያለፈ እንደ ነበር ይናገራል። ስለዚህም ባለፈባቸው ስፈሮችና መንደሮች የነበሩ ሰዎች ተከትለውት እንደ ገና ወደ ቅፍርናሆም መጥተዋል ማለት ነው። ይህ ሰው የሚናገረውን ይበልጥ ለመስማት በመጓጓት በባሕሩ ዳርቻ ቆመው ነበር።

**§ 64ለ**
**የአፈሩ ምሳሌ**
**(ማቴ 13፥3-23፤ ማር 4፥3-25፤ ሉቃ 8፥5-18**



ስለ ባለንብረቱ የተነገረው ምሳሌ (ማቴ 13፥51-52) የጠቅላላው ስብከት መደምደሚያ እንደ ሆነ ሁሉ፣ ይህ የመጀመሪያው ምሳሌ የጠቅላላው ስብከት መግቢያ ወይም ማስተዋወቂያ ነበር ማለት ይቻላል።[134] «የእግዚአብሔር መንግሥት ይህን ትመስላለች» የሚል ሐረግ የሌለበት በመሆኑ ከሌሎቹ የተለየ ነበር። ስለሆነም ይህ ምሳሌ ሌሎች የእግዚአብሔር መንግሥት ምሳሌዎችን ለማቅረብ የተዘጋጀ መድረክ ነበር። በዚያ ከነበሩት አንዳንዶቹ የመልካም አፈር ያህል ስለ ነበሩ በስብከቱ በጣም ይባረካሉ። ሌሎች ግን በተለያየ ምክንያት እነዚህን ምሳሌዎች አይቀበሉም። እንዲያውም ምሳሌዎቹ ግራ መጋባትን ያስከትሉባቸዋል።

**ማቴ 13፥3-9፤**
**ከሉቃ 8፥5-7 ጋር**

አንድ ገበሬ ዘር ሊዘራ ወጣ። [4]ሲዘሩም ሳለ፣ አንዳንዱ ዘር መንገድ ዳር ወደቀ፤ (በእግርም ተረጋገጠ[ሉቃ]) ወፎችም መጥተው ለቀሙው በሉት።
[5]አንዳንዱ ዘር ዐፈሩ ስስ በሆነ፣ ድንጋያማ መሬት ላይ ወደቀ፤ ዐፈሩ ስስ ስለ ሆነም ፈጥኖ በቀለ። [6]ነገር ግን ፀሐይ ሲወጣው (ርጥበት አልነበረውምና[ሉቃ]) ጠወለገ፤ ሥር ባለ መስደዱም ደረቀ። [7]አንዳንዱም ዘር በእሾኽ መካከል ወደቀ፤ እሾኹም አደገና (አብሮት አደገና[ሉቃ]) ቡቃያውን አንቆ አስቀረው (ፍሬ አላፈራም[ማር])። [8]ሌላው ዘር ደግሞ በጥሩ መሬት ላይ ወደቀ፤ ፍሬም አፈራ፤ አንዱ መቶ፣ አንዱ ሥልሳ፣ አንዱም ሠላሳ ፍሬ ሰጠ። (ይህን ብሎ ሲያበቃም ድምፁን ከፍ አድርጎ[ሉቃ]) [9]ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ።

ኢየሱስ በነበረበት አራሽ ማኅበረ ሰብ ገበሬዎች ዘር ያለበት ስልቻ ተሸክመው ወደ እርሻው በመሄድ በእጃቸው እየዘገኑ ዘሩን በታረሰው ማሳ ላይ ይበትኑ ነበር። በፓለስቲና ይህን ማየት የተለመደ ነበር። ምንም እንኳ የእኛ አእምሮ ይህን ለመቀበል ዝግጁ ባይሆንም፣ ገበሬው ዘሩ ምን ዐይነት መሬት ላይ እንደሚወድቅ ይህን ያህል አያሳስበውም። እኛ በለመድነው አስተራረስ መሠረት ከመዝራታችን በፊት መሬቱን እናርሳለን፤ ስለዚህም ዐፈሩ ምን ዓይነት እንደ ሆነ እናውቃለን። ኢየሱስ ባገለገለበት ዘመን ግን ገበሬዎች ከዘሩ በኋላ ነበር

[134] S.D. Toussaint, "The Introductory and Concluding Parables of Matthew Thirteen" *BibSac* 121(1964): 351-355.

የሚያርሱት::[135] ስለዚህም መንገድ ዳር ያለው መሬት ለም ሊሆን ይችላል:: መሬቱ ውስጥ ያለው ሲገለበጥ ጭንጫማ መስሎ የታየን በኋላ ምን ዓይነት እንደ ሆነ ግልጽ ይሆናል:: ከመዝራታቸው በፊት መሬቱን ሊያርሱ እንኳ ብዙ በዘሩ መጠን የዚያኑ ያህል ሰብል ስለሚያገኙ በብዛት መዝራት ነበረባቸው:: አንዳንድ ዘሮች መንገድ ዳር ወይም ጭንጫማ መሬት ላይ ስለሚወድቁ ገበሬው የተዘራው ሁሉ ፍሬ ይሰጣል ብሎ አይጠብቅም:: ይሁን እንጂ መሬቱ ሁሉ በዘር መሸፈኑን እርግጠኛ ለመሆን እፍኝ ሙሉ ዘር መበተን ያስፈልጋል::

አራት የዐፈር ዓይነቶች አሉ፤ እያንዳንዱ የዐፈር ዓይነት የሰውን ልብ ሁኔታ ይወክላል፤ የመጀመሪያው መንገድ ዳር ያለው ነው:: ይህ ጠንካራ መሬት ነው፤ በዚያ መሬት ዘር ስለማይበቅል፣ ወፎች (ሰይጣን፣ ከማር 4÷15 ጋር ያነ) ለቅመው ይበሉታል:: ሁለተኛው፣ በጭንጫ መሐል ያለ ስስ ዐፈር ነው ማቴዎስና ማርቆስ ተክሉ ሥር እደማይሰድ ሲያመለክቱ፣ ሉቃስ ግን ርጥበት ሊኖረው እንደማይችል ያመለክታል:: ስለ እርሻ የሚያውቅ ማንኛውም ሰው ይህን ያህል ልዩነት እንደሌለ ይረዳል:: ርጥበት ሊኖረው የማይችለው ዐፈሩ ስስ ስለሆነ ነው:: ሦስተኛው፣ አረሙ ከዘሩ ጋር አብሮ ማደጉና ዘሩን አንቆ መያዙ ነው:: አራተኛው፣ ብዙ ፍሬ የሚሰጥ ጥሩ ዐፈር ነው:: ዐሥር እጥፍ ከተገኘ ጥሩ ምርት ተገኘ ይባላል:: ኢየሱስ የተናገረው መቶ እጥፍ ጥቂት የተጋነነ ቢመስልም ጨርሶ የማይሆን ግን አይደለም:: ንግግሩ እዚያ የነበሩ ገበሬዎችን ትኩረት መሳብ መቻሉ ግልጽ ነው::

ሦስተኛው የዐፈር ዓይነትን በተመለከተ የእህል ዘር በእሾክ መካከል ሊወድቅ እንደሚችል ማሰብ ትክክል አይደለም:: ከሞቃታማው የበጋ ወሮች በኋላ ሳይደርቅ የቀረ እሾክ ቢኖር እንኳ ዘሩ ከተዘራ በኋላ መሬቱ ሲታረስ አብሮ ይታረሳል:: እዚህ ላይ መውሰድ ያለብን ሥዕል

135 P.B. Payne "The Order of Sowing and Plowing in the Parable of the Sower," *NTS* 25 (1978): 123-129 እርሻ ነክ የሆኑ ዝርዝር ነገሮችን አቅርቦአል::



መልካም ዘር ከመጥፎ ዘር ጋር የሚያደርገውን ትግል ነው:: ሉቃስ፣ «አብሮ ማደግ» ተብሎ የሚተረጐም ሲምፍዩ የሚል ቃል ተጠቅሟል:: ምን ማለት እንደ ሆነ ግልጽ ነው:: ሕይወታችን የጠራ ወይም ንጹሕ መስሎ ሊታይ ይችላል:: «አረም» የሌለበት ይምሰል እንጂ፣ «መጥፎ ዘር» ሊኖር ይችላል::

በመሠረታዊ ደረጃ ዐፈሩ አንድ ዐይነት ነው:: ልዩነቱ ሀፈሩ ላይ የሆነው ነገር ነው (አረም፣ ድንጎይ ወይም በእግር መረገጡ):: ልዩነቱ እንዴት ሊኖር ቻለ? ቃሉን የሰማንበት ሁኔታ ነው ልዩነቱን ያመጣው:: ለይስሙላ ሳይሆን በትሕትና ቃሉን መስማት አለብን:: ቃሉን መስማት ብቻ ሳይሆን መታዘዝም አለብን:: በአይሁድ አስተሳሰብ መሠረት «መስማት» እና መታዘዝ የተያያዙ ናቸው:: በእያንዳንዱ ሰው ልብ ውስጥ ያለው «ዐፈር» ጥሩ ነው:: ልዩነቱን የሚያመጣው ፈቃዳችን ነው:: «ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ» የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ትርጉም ይህንኑ ነው የሚያመለክተው::

**ማቴ 13÷10-12**
**ከማር 4÷10-11፣**
**ሉቃ 8÷18 ጋር**

[10]ከዚያም ደቀ መዛሙርቱ ወደ እርሱ ቀርበው፣ (ብቻውን ባሆነ ጊዜ፣ ዐሥራ ሁለቱና አብረውት የነበሩት ሌሎች[ማር]) «ለምን ለሕዝቡ በምሳሌ ትናገራለህ?» አሉት::

[11]እርሱም እንዲህ አላቸው፤ «ለእናንተ የመንግሥተ ሰማያት ምስጢር ማወቅ ተሰጥቶአችኋል፤ ለእነርሱ ግን አልተሰጣቸውም:: (በውጭ ላሉት ግን ነገር ሁሉ በምሳሌ ይነገራቸዋል[ማር]) [12]ላለው ይጨመርለታል፤ ይበዛለትማል፤ ከሌለው ግን ያ ያለው እንኳ (ያለው የሚመስለው እንኳ[ሉቃ]) ይወሰድበታል::

ኢየሱስ ባሕሩ ላይ ከነበረ ጀልባ እያስተማረ ነበር:: ዐሥራ ሁለቱና ሌሎች የሚቀርቡት ጥቂት ደቀ መዛሙርት ከእርሱ ጋር ጀልባው ውስጥ ነበሩ:: በሕዝቡ መካከል የተፈጠረውን ግራ መጋባት ካዩ በኋላ ለምን ግራ የሚያጋባ ምሳሌ እንደሚጠቀም ኢየሱስን ጠየቁት::

ይህ ግን የእርሱ የሁልጊዜ አሠራር አልነበረም:: በዚያ ብዙ ሕዝብ ፊት ቆሞ እያለ ጀልባው ውስጥ በግል ሊጠይቁት ይችሉ ነበር:: ሕዝቡ ሁሉ ከሄደ በኋላ ቤት ውስጥ ደቀ መዛሙርቱን ብቻ ያስተምራቸዋል (ማቴ 13÷36)::

የእግዚአብሔር መንግሥት ምሥጢር በምርምር የሚደረስበት ሳይሆን በመገለጥ የምንረዳው ነው ምሥጢሩ ከተገለጠ በኋላ ለመረዳት በጣም ቀላል ነው::

ቁጥር 12 ላይ ያለው መርሕ ለተለያዩ ሁኔታዎች ይጠቅማል:: ብዙ በሰማን መጠን፣ ይበልጥ መረዳት እንችላለን:: ጥቂት በሰማን መጠን ግን የምንረዳው በጥቂቱ ይሆናል:: ልክ ባንክ እንደምናስቀምጠው ገንዘብ ነው:: አንድ ሰው ብዙ ብር ባንክ ውስጥ ሲያስቀምጥ የሚኖረው ገንዘብም ይበዛለታል:: ሰዎች የተለያዩ የምግብ ዐይነቶች ወዳሉት እንጂ፣ ባዶ ወደ ሆነ ሆቴል አይሄዱም:: ኀላፊነት የምንሰጠው፣ ኀላፊነት ለሚሰማቸው ነው:: በተመሳሳይ መልኩ የእግዚአብሔርን መንግሥት ባሕርይና ዐላማ ለሚረዱ፣ በእነዚህ ምሳሌዎች አማካይነት ተጨማሪ ትምህርት ይሰጣቸዋል:: የማያውቁ ወይም የማይረዱ ግን በእነዚህ ምሳሌዎች ይበልጥ ግራ ይጋባሉ::

ማቴ 13÷13-17 ከማር 4÷12፤ ሉቃ 8÷18 ጋር



13ስለዚህ እንዲህ በማለት በምሳሌ
የምነግራቸው ለዚህ ነው፤ «እያዩ ስለማያዩ፤ እየሰሙ
ስለማይሰሙ ወይንም [ሀ]ስለማያስተውሉ (እንዳይመለሱና
ኀጢአታቸው እንዳይሰረይላቸው[ማር]) ነው::
14እንዲህ ተብሎ የተነገረው የኢሳይያስ
ትንቢት በእነርሱ ይፈጸማል፤
«መስማትንስ ትሰማላችሁ፤ ነገር ግን አታስተውሉም፤ ማየትንም ታያላችሁ፤ ነገር ግን
ልብ አትሉም፡ 15የሕዝቡ ልብ ደንድኖአልና፤ ጆሮአቸውም አይሰማም፤ እንዳያዩም
ዐይናቸውን ጨፍነዋል፤ ይህ ባይሆን ኖሮ፣ በዐይናቸው አይተው፣ በጆሮአቸው ሰምተው፣
በልባቸውም አስተውለው፣ ወደ እኔ በተመለሱና በፈወስኋቸው ነበር::[ለ] 16የእናንተ
ዐይኖች ስለሚያዩ፣ ጆሮዎቻችሁም ስለሚሰሙ ግን የተባረኩ ናቸው:: 17እውነት
እላችኋለሁ፤ ብዙ ነቢያትና ብዙ ጻድቃን እናንተ የምታዩትን ለማየትና የምትሰሙትንም
ለመስማት ተመኝተው ነበር፤ ግን አልሆነላቸውም::

*[ሀ][ማር 4:]12 ኢሳይያስ 6÷9፣10*

*[ለ][ማቴ 3:]15 ኢሳይያስ 6÷9፣10*

ምሳሌዎቹ የእግዚአብሔርን መንግሥት ምሥጢር ከሰሚዎቹ ለአብዛኞቹ የሸሸገባቸው ዘዴዎች ነበሩ:: ይህ ከኢሳይያስ 6÷9-10 የተወሰደው ጥቅስ ማርቆስ 4÷12 ላይ እጅግ በተዋጣለት ሁኔታ በግሪኩ ተተርጉሞአል:: የዕብራይስጡ ፈሊጣዊ አነጋገር፣ «ያያሉ፣ ደግሞም ያያሉ ግን አያዩም፤ ይሰማሉ፣ ደግሞም ይሰማሉ፣ ግን አይሰሙም» በማለት ሊተረጐም ይችላል:: ማርቆስ፣ «እንዳይፈወሱና ኀጢአታቸው እንዳይሰረይላቸው» የሚል ጠቃሚ ዐረፍተ ነገር መርምሮአል:: እንዲህ ሲባል ግን ኢየሱስን ሲሰሙ ከነበሩ ከእነዚያ ሰዎች አንዱ እንኳ ወደ እርሱ አይመጣም ማለት አይደለም (ኢሳ 6÷13፤ ሮሜ 11÷25):: ይልቁንም ይህ እየተነገረ በነበረበት ጊዜ በክርስቶስ በኩል የመጣውን የእግዚአብሔርን ቃል መቀበል አልቻሉም ማለት ነው::

ስለዚህም የኢየሱስ ምሳሌዎች፣ አንዳንዶች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንይረዱና በንስሐ ወደ ድነት እንዳይመጡ አድርገዋል:: ኢየሱስ እንዲህ ያደረገው ለምንድነው? ከኢሳይያስ ዐውድ መመልከት እንደሚቻለው ይህ ለአለማመን የተሰጠ ምላሽ ነበር:: አንድ ሰው ፊቱን ከኢየሱስ ሲያዞር፣ ኢየሱስም በምሳሌዎቹ አማካይነት እንዲሁ ፊቱን ያዞርበታል:: ይህ አለማመን ፍርድን ማምጣት ብቻ ሳይሆን፣ የአንድን ሰው እውነትን የመረዳት ችሎታም ጨርሶ ሊያጠፋ ይችላል የሚለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሕ ፍጻ ሜ ነው (ዮሐ 3÷17-19፤ 9÷39-41፤ ዘፀ 8÷32፤ 9÷12፤ ሮሜ 9÷17-18፤ ሐሥ 28÷26-27፤ ማቴ 7÷6፤ ሉቃ 20÷1-8፤ ዮሐ 12÷39-41፤ራእ 22÷11)::

በተጨማሪም ይህ ከኢሳይያስ 6÷9-10 የተወሰደ ጥቅስ አዲስ ኪዳን ውስጥ ሦስት ጊዜ ተጠቅሶአል:: እዚህ ላይ ያለማወቃቸው ምክንያት ራሱ ሰባኪው ነበር:: ይህም በምሳሌዎቹ አማካይነት ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደ ሰወረባቸው ያሳያል:: ዮሐንስ 12÷40 ላይ የንስሐ ዕድል የነፈጋቸው እግዚአብሔር ራሱ ይመስላል:: ከየሐዋርያት ሥራ 28÷26-27 እንደምንመለከተው ደግሞ ያለማመናቸው ምክንያት ሕዝቡ ራሳቸው ነበሩ:: እዚህ ላይ በተደጋጋሚ የተጠቀሰው (ማቴ 13÷13-23 ውስጥ ዐሥራ ሦስት ጊዜ)፣ «መስማት» የሚለው ቃል ነው:: ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት ካልፈለጉ፣ ዕድሉ ይወሰድባቸዋል::

እግዚአብሔር ሰውን የማይቀበልበት ሁኔታ ይኖራልን? አዎን! ይሁን እንጂ ያለ ምክንያት አይደለም:: እግዚአብሔር አንድን ሰው የማይቀበለው አንዳንድ ነገሮችን መሠረት በማድረግ ነው:: (1) በሰው ኀጢአት ምክንያት (ኢሳ 6÷8-13)፤ (2) በእግዚአብሔርና በሰው መካከል በሚኖር አለመፈለግ (ዮሐ 3÷17-19)፤ (3) ትሩፋንን ለማንጻት (ሮሜ 11÷5-8)፤ (4) ለአሕዛብ የድነትን በር ለመክፈት (ሮሜ 11÷9)፤ (5) በንስሐ የማይመለሱ ሰዎች ጆሮና ልብ መዘጋት::

ማቴዎስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማየት ያለንን ዕድል ጕላ አድርጐ ለማሳየት ቁጥር 16-17 ያሉትን ጠቃሚ ዐረፍተ ነገሮች ጽፏል (ከሉቃ 10÷23-24፤ ዕብ 11÷39-40፤ 1ጴጥ 1÷10-12 ጋር ያነ):: የብሉይ ኪዳንን ወይም የአዲስ ኪዳን ታሪኮችን ስናነብ በጣም እንጓጓ ይሆናል:: እንዲህ ያሉ ነገሮች በተከሰቱበት ዘመን በመፈጠራቸው ዕድለኞች ናቸው ብለን አስበን ይሆናል:: ሆኖም፣ ከእነርሱ ይልቅ ይበልጥ የታደልን እኛ ነን:: የእግዚአብሔርን መንግሥት እንለማመዳለን፣ የተሟሉ ቅዱሳት መጻሕፍት አሉን፣ መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ይኖራል:: ነቢያት በጣም ሲናፍቁ የኖሩትን አግኝተናል::



**ማር 4÷13**

13ከዚያም ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፤ «ይህን ምሳሌ
አልተረዳችሁትምን? ታዲያ ሌሎቹን ምሳሌዎች ሁሉ እንዴት
ልትረዱ ትችላላችሁ?

**ማቴ 13÷18-23 ከማር 4÷14፣ ሉቃ 8÷12-15 ጋር**

18እንግዲህ የዘሪውን ምሳሌ ስሙ፤ (ዘሪው ቃሉን
ይዘራል[ማር]) 19የእግዚአብሔርን መንግሥት ቃል ሰምቶ
ከማያስተውል ከማንኛውም ሰው ልብ ውስጥ ክፉው
(ሰይጣን[ማር]) (ዲያብሎስ[ሉቃ]) መጥቶ (ሰምተው እንዳይድኑ[ሉቃ])
የተዘራውን ዘር ይነጥቃል:: ይህ እንግዲህ በመንገድ ዳር የተዘራው ዘር ነው::
20በድንጋያማ መሬት ላይ የተዘራው፣ ቃሉን ሰምቶ ወዲያውኑ በደስታ የሚቀበለውን
ሰው ይመስላል:: 21ነገር ግን ሥር መስደድ ባለመቻሉ ብዙ አይቆይም፤ በቃሉ ምክንያት
መከራ ወይም ስደት ሲመጣ ወዲያውኑ ይሰናከላል:: 22በእሾኽ መካከል የተዘራው ዘር
ቃሉን ሰምቶ ስዚህ ዓለም በመጨነቅና በብልጽግና ሐሳብ (ደስታ[ሉቃ]) (እንዲሁም
የሌሎች ነገሮች ምኞት[ማር]) በመታለል ታንቆ ያላፈራውን ሰው ይመስላል:: 23በጥሩ
መሬት ላይ የተዘራው ዘር ግን (ቃሉን በሚሰሙበት ጊዜ በደስታ[ሉቃ]) ቃሉን ሰምቶ
የሚያስተውለውን (የሚቀበለውን[ማር]) ሰው ይመስላል፤ በእርግጥም ፍሬ ያፈራል፤ አንዱ
መቶ፣ አንዱ ሥልሳ፣ አንዱም ሠላሳ ፍሬ ሰጠ::

ኢየሱስ የምሳሌውን ትርጉም ስለ ሰጠን ዕድለኞች ነን:: ከሚከተሉት አራት ሰዎችን ዐይነት አቅርቧል:-

1. መንገድ:- ለእግዚአብሔር ቃል ግድ የሌላቸው ሰዎች:: ወደ ውስጣቸው ዘልቆ አይገባም:: «አምነው እንዳይድኑ» ሰይጣን ነጥቆ ይወስደዋል::
2. ድንጋያማ ቦታ:- በመከራ ወይም በስደት የሚሰናከሉ ሰዎች፤ እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ለመቀበልና ለመንደ ምን ያህል ፈጣኖች እንደ ሆኑ ለማመልከት ማቴዎስና ማርቆስ፣ «ወዲያውኑ» የሚል ቃል ተጠቅመዋል:: እንዲህ ያሉት በፍጥነት የሚከስሙ ሰዎች ናቸው ቃሉን ሲሰሙ ቶሎ

ይቀበላሉ የሚጉዳ ወይም የሚያሳዝን ነገር ሲገጥማቸው ግን እርግፍ አድርገው የተውታል::

3. እሾኽ ወይም ማነቆ የሆነ ነገር:- እዚህም ላይ ቢሆን መልካሙ ዘር ከአረሙ ጋር ስለሚያደርገው ፉክክር በድጋሚ ማመልከት ያስፈልጋል:: አብረው እያደጉ ሳለ አረሙ አሸንፎ ይወጣል:: ኢየሱስ ለክርስትና ሕይወት አደገኛ የሆኑ ሦስት ነገሮችን አመልክቷል፤ ለዚህ ዓለም መጨነቅ፣ የብልጽግና ሐሳብና ደስታ ፈላጊነት::
4. ጥሩ ዐፈር:- እነዚህ ቃሉን ሰምተው የሚታዘዙ ናቸው ብዙ ፍሬም ያፈራሉ::

ኢየሱስ ፍሬ ስለ ማፍራት ሦስት አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎችን አስቀምጦአል፤ (1) ንጹሕና መልካም ልብ:: እንዲህ ያለው ሰው ቃሉን የሚሰማው እንዲሁ ለመስማት ብቻ አይደለም:: (2) መልካም ሕይወት እንዲኖረን ቃሉን አጥብቀን መያዝ ይኖርብናል:: ትክክለኛውም ይኸው ነው:: (3) በሰሙት ቃል መጽናት:: የማይጸና ሰው በእርግጥ ድኖአል ማለት አይቻልም (ማቴ 24÷13፤ ራእ 2÷10):: መጀመሪያውኑ ሊገጥመን ስለሚችለው ተግዳሮት ረጋ ብለን ማሰብ አለብን:: ያኔ የያዝነውን አጥብቀን እንይዛለን:: የመጨረሻውን ደወል እስክንሰማ ድረስ በያዝነው መጽናት ይኖርብናል::

**የመብራቱ ምሳሌ (ማር 4÷21-25፤ ሉቃ 8÷16-18 ማቴ 5÷14-16 ጋር ያነ)**

(እንዲሁም አላቸው[ማር]) 16መብራትን አብርቶ ጋን ውስጥ ወይም በዐልጋ ሥር የሚያስቀምጥ ማንም የለምዩ ይልቁንም ወደ ቤት የሚገቡ ብርሃኑን እንዲያዩ በመቅረዝ ላይ ያስቀምጠዋል:: 17የማይገለጥ የተሰወረ፣ የማይታወቅ ወደ ብርሃን የሚይወጣ፣ የተደበቀ ነገር የለምና:: (ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ[ማር]) 18እንግዲህ እንዴት



እንደምትሰሙ ተጠንቀቁ፤ (በምትሰፈሩበት መስፈሪያ ይሰፈርላችኋል፤ እንዲያውም ከዚያ የበለጠ ይጨመርላችኋል[ማር]) ላለው ይጨመርለታልና፤ ከሌለው ግን ያው ያለው የሚመስለው እንኳ ይወሰድበታል::

[ሉቃ 8÷16፤ ማቴ 5÷14-16፤ 54 ሐን ማብራሪያ ይመለከቷል]


«እንዴት እንደምትሰሙ ተጠንቀቁ» (ቃል በቃል፣ «እንዴት እንደምትሰሙ ተጠበቁ» ወይም፣ «ዐይኖቻችሁን ጆሮዎቻችሁ ላይ አድርጉ»):: የዚህ ምንባብ አንኳር ሐሳብ ያለው እዚህ ላይ ነው:: ብርሃን የምናገኘው የኢየሱስን ቃል በጆሮዎቻችን ሳይሆን በልባችን ስንሰማ ነው:: የኢየሱስ ቃል ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ባለን ግንዛቤ ላይ ያበራልናል::

**§ 64ሐ የአዳጊው ዘር ምሳሌ (ማር 4÷26-29)**

26ከዚያም፣ እንዲህ አለ፤ የእግዚአብሔር መንግሥት ይህን ትመስላለች፤ አንድ ሰው መሬት ላይ ዘር ይዘራል:: 27ሰውየው ሌሊት ይተኛል፤ ቀን ይነሣል ነገር ግን እርሱ ሳያውቅ ያ ዘር በቅሎ ያድጋል፤ 28ምድርም ራሷ በመጀመሪያ ቡቃያውን፣ ቀጥሎ ዛላውን፣ ከዚያም በዛላው ላይ የጐመራ ፍሬ ታስገኛለች፤ 29ፍሬው እንደ በሰለም መከር በመድረሱ፣ ሰውየው ወዲያው ማጭዱን አንሥቶ አጨዳ ይጀምራል::

በማርቆስ ወንጌል ውስጥ ብቻ የምናገኘው ይህ ምሳሌ ስለ ዐፈሮቹ፣ የቀረውን ምሳሌ ተከትሎ የመጣ መሆኑ ግልጽ ነው:: በአንድ በኩል ዐፈሩ (ሰው) ዘሩን (የእግዚአብሔር ቃል) የመቀበል ኀላፊነት አለበት:: በሌላ በኩል ምስጢራዊ ዕድገቱን በተመለከተ ግን ኀላፊነቱ የእግዚአብሔር ነው:: ሰው የእግዚአብሔር ቃል ማደግ የሚችልባቸውን ሁኔታ ያመቻቻል:: የማደጉ ኀላፊነት ግን በፍጹም የእኛ አይደለም:: በሌላ አነጋገር እኛ እንኰተኩታለን፣ እግዚአብሔር ግን ያሳድጋል::

እነዚህ ተጓዳኝ ምሳሌዎች በእግዚአብሔር ሉዓላዊ አሠራርና በሰው ኀላፊነት መካከል ሊኖር የሚገባውን ሚዛናዊነት ይጠብቁልናል::



አስተዳደጉ ግን ምስጢር ነው፤ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደ አትክልት ዕድገት ነው:: ከትንሽ ዘር ይጀምርና አንዳንዴ ሳይታወቅ በቀጣይነት እያደገ (ቀንና ሌሊት) የጉመራ መከር መሆን ደረጃ ላይ ይደርሳል::

§ 64 መ
የእንክርዳዱ ምሳሌ
(ማቴ 13÷24-30)



[24]ኢየሱስም ሌላ ምሳሌ እንዲህ ሲል ነገራቸው፤
«መንግሥተ ሰማያት በዕርሻው ቦታ ጥሩ ዘር የዘራውን
ሰው ተመስላለች:: [25]ነገር ግን ሰው ሁሉ ተኝቶ ሳለ
ጠላቱ መጥቶ በስንዴው መካከል እንክርዳድ ዘርቶ ሄደ::
[26]ስንዴው በቅሎ ማፍራት ሲጀምር እንክርዳዱም አብሮ
ብቅ አለ::

[27]«የዕርሻው ባለቤት አገልጋዮችም ወደ እርሱ ቀርበው፣ 'ጌታ ሆይ፤ በዕርሻህ
ቦታ ጥሩ ዘር ዘርተህ አልነበረምን?' እንክርዳዱ ከየት መጣ አሉት::
[28]እርሱም፣ የጠላት ሥራ ነው አላቸው:: አገልጋዮቹም፣ እንክርዳዱን ሄደን
እንድንነቅለው ትፈልጋለህ? ብለው ጠየቁት::
[29]እርሱ ግን፣ አይሆንም፤ ምክንያቱም እንክርዳዱን እንነቅላለን ስትሉ
ስንዴውንም አብራችሁ ልትነቅሉ ትችላላችሁ፤ [30]ተዉአቸው፤ እስከ መከር ጊዜ
አብረው ይደጉ:: በዚያን ጊዜ አጫጆቹን እንክርዳዱን አስቀድማችሁ ንቀሉ፤ በእሳትም
እንዲቃጠል በየነዶው እሰሩት፤ ስንዴውን ግን ሰብስባችሁ በጎተራዬ ክተቱ አላቸው::


እንዲህ ያለው እርሻ ነክ ተንኰል መፈጸም የተለመደ ባይሆንም ፈጽሞ የማይደረግ ነው ማለት ግን አይቻልም::[136] ማጥቃት የፈለገ

[136] A.J. Kerr, "Matthew 13:25 Sowing Zizania among Another's Wheat: Realistic or Artificial?" *JTS* 48/1 (1997): 108-109, ላይ ይህን ወንጀል



ጠላት እርሻ ውስጥ 'ዳርኔል' (darnel-Gk= *zizania*) የተባለውን የዐረም ዓይነት መዝራት ይችላል:: ይህ ዐረም ፈጽሞ ስንዴን ስለሚመስል ዘሩ አድጐ "ራሱን" ቀና ቀና ማድረግ እስከሚጀምር ድረስ ልዩነቱን እንኳ ማወቅ አይቻልም:: በዚያ ጊዜ ደግሞ ሥሩ በአንድነት ከበቀሉት ስንዴ ሥሮች ጋር ስለሚያያዝ ነቅሎ ማውጣት እንኳ አይቻልም:: ስለሆነም ዐረሙን እነቅላለሁ ሲባል ስንዴውንም አብሮ መንቀል ሊኖር ይችላል::

መፍትሔው እስከ መከር ድረስ መጠበቅ ብቻ ነው፤ ሁለቱም ይታጨዱና ይለያሉ:: እንክርዳዱ ተሰብስቦ ይቃጠላል:: ስንዴው ግን በጐተራ ይከተታል:: በተመሳሳይ መንገድ በዚህ ዓለም መልካምና ክፉ አብረው እንዲኖሩ ተፈቅዶአል:: መጥፎ ሰዎችን ማጥፋት ቢፈለግ ብዙ መልካም ሰዎች አብረው ሊጐዱ ይችላሉ:: ይሁን እንጂ ክፉ ሁሉ የሚነቀልበት ቀን ይመጣል:: የሚቀረው መልካሙ ብቻ ይሆናል:: የእግዚአብሔር መንግሥት በሙላት ይገለጣል:: አሁን ግን በዚህ በኀጢአት በወደቀ ዓለም ሁሉ አንድ ባልሆነበት የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ መኖር የግድ ነው::



አንዳንዶች ይህን ጥቅስ ከቤተ ክርስቲያን የሥነ ሥርዓት እርምጃ ጋር አያይዘው ተጠቅመውበታል::[137] እንደ እነርሱ

አስመልክቶ የሮማውያንን ሕግ ጠቅሷል:: ኢየሱስ ያቀረበውን ምሳሌ ታሪካዊ እውነታ የሚክዱ በዘመኑ የነበረውን ሐቅ አላገናዘቡም ማለት ነው::


[137] ይህን በተመለከተ አሳማኝ መከራከሪያ ለማቅረብ R.McIver, "The Parable of the Weeds Among the Wheat ( Mt 13:24-30, 36-43) and the Relationship between the Kingdom and the Church as Portrayed in the Gospel of Matthew," *JBL* 114/4 (1995): 643-659 ይመልከቱ:: በመተርጐም ረገድ "ሁሉን አቀፍነት" (Universalist) ሊገጥመው ስለሚችል ችግር አስመልክቶ የሚከተለውን አቅርበዋል (1) እስከ ፍርድ ቀን ድረስ ክፉዎች በዚህ ዓለም እንደሚኖሩ ኢየሱስ የተናገረው ለምንድ ነው? በውስጠ ተዋቂነት መናገሩ አይደለም? (2) እርሻው ይህን ዓለም ቢሆን ኖሮ ደቀ መዛሙርቱ እንክርዳዱን መንቀል እንዳለባቸው ያሰቡት ለምንድ ነው? (3) እርሻው ይህ ዓለም ከሆነ

ከሆነ በደል የፈጸሙ ሰዎችን ከቤተ ክርስቲያን ማስወገድ የለብንም ማለት ነው፤ ሆኖም እንክርዳድ የሞላበት እርሻ የዚህ ዓለም እንጂ የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ አይደለም:: በተጨማሪም ቤተ ክርስቲያን በደል የፈጸሙ አባሎቿን ሥርዓት የማስያዝ ግዴታ እንዳለባት አዲስ ኪዳን ግልጽ አድርጓል::

§ 64
የሰናፍጭ ምሳሌ
(ማቴ 13÷31-32፤ ማር 4÷30-32፤
ሉቃ 13÷18-19 ጋር ያነ



³⁰ደግሞም እንዲህ አለ፤ የእግዚአብሔርን መንግሥት (መንግሥተ ሰማያት[ማቴ]) ከምን ጋር እናነጻጽራታለን? በምንስ ምሳሌ እንገልጻታለን? ³¹በምድር ላይ ከሚዘራው ዘር ሁሉ እጅግ ያነሰችውን የሰናፍጭ ቅንጣት ትመስላለች፤ ³²ተዘርታ ካደገች በኋላ ግን፣ በአትክልቱ ቦታ ከሚገኙት ዕፅዋት ሁሉ ትበልጣለች፤ የሰማይ ወፎችም በትልልቅ ቅርንጫፎቿ ጥላ ሥር ያርፋሉ::



ማርቆስ ይህን ምሳሌ ያስቀመጠው ስለ አዳጊው ዘር ከተናገረው ምሳሌ ቀጥሎ ነበር [§ 64]:: እርግጥ ነው፣ ሁለቱም የተያያዙ ናቸው:: ዘሩ ማደግ ብቻ ሳይሆን (በእግዚአብሔር ተአምር) አነስተኛ እና ከሆነ ጅማሬው ጋር ሲነፃፀር በጣም ትልቅ ሆኖ ነበር:: እንደዚሁም፣ አሁን አነስተኛ መስላ የምትታየው የእግዚአብሔር መንግሥት፣ ታድጋለች፣ ትሰፋለች:: ኢየሱስ ከዐሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ጋር የጀመረው ትህትና ያለበት ጅማሬ፣ ማለትም ይህ መንግሥት በዓለም ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አምጥቷል::

---

አዝመራው ያልተለየው ለምንድ ነው? ክርስቲያኖች የተለዩ መሆናቸው በግልጽ መታየት የለበትም?




በመሠረቱ የሰናፍጭ ቅንጣት በዓለም ካሉት ዘሮች ሁሉ አነስተኛ ዘር አይደለችም:: (ትንሿ ጥቁሯ orchid)[138] በመባል የምትታወቀዋ ናት:: ይሁን እንጂ ትንሽ ከመሆኗ አንጻር ትልቅ ሆና የማደግ ሁነኛ ምሳሌ ሆናለች፤ አንዳንድ የሰናፍጭ ተክሎች ከዐሥር እስከ ዐሥራ ሁለት ጫማ ድረስ ያድጋሉ፤ ይህ ደግሞ በትንንሽ ማረፊያ ይበቃል፣ ዛፍ የተባለው ከዚህ የተነሣ ነው::[139]

አንዳንዶች ወፎቹና ጥላው በእግዚአብሔር መንግሥት የሚጠለሉ ባዕዳን ሕዝቦች ምሳሌ ነው ብለዋል (ሕዝ 17÷22-24፤ ከዳን 4÷12 ጋር ያነጻጽሩ)::[140] ይህ የምሳሌውን ትርጉም ከሚገባው በላይ መለጠጥ ቢሆንም፣ ከታሪክ እንደምንመለከተው የእግዚአብሔር መንግሥት በዚህ ዓለም ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አሳድሯል::

§ 64
የእርሾው ምሳሌ
ማቴ 13÷33-35
ማር 4÷33-34
ሉቃ 13÷20-21 ጋር ያነጻጽሩ

³³ለሁንም ሌላ ምሳሌ እንዲህ ሲል ነገራቸው፤ «መንግሥተ ሰማይ ሴት ወስዳ ሊጡ በሙሉ እስኪቦካ ድረስ በሦስት መስፈሪያ ዱቄት ውስጥ ከመደባለቅ የሸሸገችውን እርሾ ትመስላለች::»



ትንሿ የሰናፍጭ ዘር አድጋ ዛፍ እንደ ሆነች ሁሉ ቅንጣቷ እርሾም ሊጡን ሁሉ ታቦካለች::[141] እንደ እርሾ ሁሉ አሁን ትንሽ የምትመስለን የእግዚአብሔር መንግሥት ከጥቂቱ

---

[138] J.A. Sproule, "The Problem of the Mustard Seed," *GTJ* 1 (1980): 37-42 የኢየሱስን ምሳሌያዊ አነጋገር ያብራራል::

[139] ኢየሱስ የተጠቀመበት "ሌኮሳኖን" (*laxanon*) የሚለው ቃል ዘፍ ( ማቴ፣ ሉቃ) ወይም ቁጥቋጦ ሳይሆን የሚበላ ተክል ወይም ቅጠላ ቅጠል ነው፤ እርግጥ ነው በዚያ ጊዜ ሰናፍጭም ቢሆን በጣም አነሥተኛ በሚባሉ ተክሎች የሚመደብ ነበር::

[140] E.g,, R.W Funk, "The Looking -Glass Tree is for Birds," *Int* 27 (1973): 3-9.

[141] ሦስት መስፈሪያ ከ20-45 ሊትር ያህል ነው:: ይህ ደግሞ 100 ሰዎችን መመገብ ይችላል::

ጅማሬዋ በላይ የሆነ ተፅዕኖ ታሳድራለች:: በቅዱሳት መጻሕፍት መሠረት እርሾ ክፉ ነገርን የሚያመለክት ቢሆንም ሁሌም እንደዚያ ነው ማለት አይደለም (ዘሌ 7÷13-14፤ 23÷17):: እዚህ ላይ እርሾ የእግዚአብሔር መንግሥትን በጐ ተፅዕኖ ለማመልከት ነው ጥቅም ላይ የዋለው::

**ማር 4÷33**

33 ኢየሱስም ሰዎች መረዳት በሚችሉበት መጠን፣ እነዚህን በመሳሰሉ ብዙ ምሳሌዎች ነገራቸው:: ምንም ነገር ያለ ምሳሌ አይነግራቸውም ነበር:: እርሱና ደቀ መዛሙርቱ ብቻ በሚሆኑበት ጊዜ ግን ሁሉንም ነገር በዝርዝር ያስረዳቸው ነበር::

**ማቴ 13÷35**

35 በዚህም በነቢዩ እንዲህ ተብሎ የተነገረው ተፈጸመ፤ «አፌን በምሳሌ እከፍታለሁ፤ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የተሰወረውንም እናገራለሁ::»

ይህ ስብከት ሙሉ በሙሉ በምሳሌዎች የተቀነባበረ ነው፤ አብዛኞቹ የኢየሱስ አድማጮች ግራ ተጋብተው ነበር (ማቴ 13÷10-17):: ወደ ቤት ከገቡ በኋላ ግን ኢየሱስ እነዚህን ምሳሌዎች ለደቀ መዛሙርቱ አብራራላቸው::

ማቴዎስ ይህን የብሉይ ኪዳን ጥቅስ የወሰደው ከአሳፍ ነው፤ ይሁን እንጂ መዝሙር 72÷2 የግድ ትንቢታዊ አንድምታ አለው ማለት አይደለም:: ይልቁንም ኢየሱስ የጥንት እስራኤላዊያን ትምህርት ጥላ ነው ማለቱ ነበር:: አሳፍ ምሥጢራዊ በሆነ አነጋገር የእግዚአብሔርን ታላላቅ ሥራዎች እንደሚዘረዝር ሁሉ ኢየሱስም ስውር በሆነ አነጋገር ታላቁን የእግዚአብሔርን መንግሥት እየገለፀ ነበር::



**§ 64ለ**
**የእንክርዳዱ ምሳሌ ትርጉም**
**(ማቴ 13÷36-43)**

36 ከዚያም ሕዝቡን ትቶ ወደ ቤት ገባ:: ደቀ መዛሙርቱም ወደ እርሱ ቀርበው፣ «በዕርሻው ውስጥ ስላለው እንክርዳድ የተናገርኸውን ምሳሌ ትርጉም ንገረን» አሉት::

37 እርሱም እንዲህ ሲል መለሰ፤ «ጥሩውን ዘር የዘራው የሰው ልጅ ነው፤ 38 ዕርሻውም ይህ ዓለም ነው፤ ጥሩው ዘር የእግዚአብሔርን መንግሥት ልጆች ያመለክታል፤ እንክርዳዱም የክፉው ልጆች ናቸው፤ 39 ዘርቶት የሄደው ጠላትም ዲያብሎስ ነው፤ መከሩ የዓለም መጨረሻ ሲሆን አጫጆቹም መላእክት ናቸው::»

40 እንክርዳዱ ተነቅሎ በእሳት እንደሚቃጠል ሁሉ በዓለም መጨረሻም እንዲሁ ይሆናል:: 41 የሰው ልጅ መላእክቱን ይልካል፤ እነርሱም ለኀጢአት ምክንያት የሆኑትንና ክፉ የሚያደርጉትን ሁሉ ለቀመው ከመንግሥቱ ያወጣሉ:: 42 ለቅሶና ጥርስ ማፋጨት ወደሰበት ወደ እቶን እሳት ይጥሏቸዋል:: 43 በዚያን ጊዜ ጻድቃን በአባታቸው መንግሥት እንደ ፀሐይ ያበራሉ:: ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ::

ኢየሱስ ሕዝቡን ትቶ ወደ ቤት ገባ (ማቴ 13÷1 ጋር ያነጻጽሩ):: የምሳሌው ትርጉም ገላጭ ነው፤ የምሳሌውን ትርጉም ብቻ ሳይሆን የኢየሱስን አተረጓጐም ዘዴ ጭምር እናይበታለን:: በመጀመሪያ፣ መከር የሚለውን ቃል ኢየሱስ የተጠቀመበት አይሁድ ፍርድን ለማመልከት በሚጠቀሙበት የተለመደ ምሳሌ እንደ ነበር እንመለከታለን:: ስለሆነም በምሳሌዎች በመጠቀሙ አድማጮቹ ይረዱታል ማለት ነው:: በሁለተኛ ደረጃ ኢየሱስ ሰይጣን፣ ፍርድ፣ የዓለም መጨረሻ፣ ገሃነም ቃል በቃል የሚወሰዱ መሆናቸውን አመልክቷል:: ሦስተኛ፣ የኢየሱስ አተረጓጐም በውስጠ ወይራ አነጋገር ነበር ይህም ማለት ምሳሌው ውስጥ ላሉ ለእያንዳንዳቸው ትርጉም ሰጥቶአል:: ፈጠራ ወይም የማይጨበጥ ሳይሆን ውስጠ ወይራ አቀራረብ ነበር::

**§ 64ሸ**
**የተደበቀ ሀብት ምሳሌ**
**(ማቴ 13፥44)**

44 መንግሥተ ሰማይ በዕርሻ ውስጥ የተደበቀ ሀብት ትመስላለች፤ አንድ ሰው ባገኛት ጊዜ መልሶ ሸሸጋት፤ ከመደሰቱም የተነሣ ሄዶ ያለውን ሁሉ በመሸጥ ያንን የዕርሻ ቦታ ገዛ።

ሕዝቡ ገንዘቡን የሚያስቀምጥበት ባንክ ስላልነበር ሀብታሞች በጥበቃዎች የሚጠበቅ ግምጃ ቤት ውስጥ ሲያስቀምጡ፣ ተራ ሰዎች ግን ሀብታቸውን የተሻለ በሚሉት ሰዋራ ቦታ ያኖሩ ነበር። በድንገት ከሞቱ ሌላ ሰው እስካገኘው ድረስ ተቀብሮ ይቀር ነበር።

በደንቡ መሠረት መሬት ውስጥ የተቀበረ ሀብት ሕጋዊ ባለቤት ባለ መሬቱ ነበር። አንዳንዶች የተደበቀ ሀብት እንዳለበት እያወቁ ያንን መሬት መግዛት ምን ያህል ግብረ ገባዊ ነው የሚል ጥያቄ ያነሳሉ። የምሳሌው ዋና ነጥብ ግን ይህ አይደለም።[142] ኢየሱስ መንፈሳዊ እውነትን ለማብራራት ሲል አታላይነትን እያበረታታ አይደለም (ከሉቃ 16፥1-8፤ 18፥1-8 ጋር ያነ)። ዋናው ቁም ነገር መንግሥተ ሰማይ ታላቅ ዋጋ ያላት መሆኑን ማሳየት ነው። የተሰወረ ሀብት ለማግኘት እንደምንደክም ሁሉ መንግሥተ ሰማይን ለማግኘት ማንኛውንም ዋጋ መክፈል ይኖርብናል።

[142] P.S Hawkings, "Parable as Metaphor," *CSR* 12 (1983): 226-236 ላይ እንደሚሉት ከሆነ የምሳሌው ዋነኛ ነጥብ የሰውየው ብልጣ ብልጥ አካሄድ ነው። እንደ እርሳቸው አባባል የምሳሌው ዋነኛ ነጥብ፣ «እግዚአብሔር ዓላማውን ለመፈጸም በዚህ ምሳሌ በምንመለከተው ዓይነት ሰውና ሁኔታዎች ውስጥ እንኳ ይሠራል» የሚል ነው። ይሁን እንጂ በምላሹ J.W Sider, "Interpreting the Hid Treasure," *CSR* 13 (1994): 360-372 ላይ አሳማኝ በሆነ ሁኔታ እንደሚከራከሩት፣ ይህን ያህል ሁነኛ ስፍራ ሊሰጠው የሚገባ አይደለም። በሌሎቹ ተጓዳኝ ምሳሌዎች፣ ያም ከፍተኛ ዋጋ ስላለው ዕንቁ በቀረበው ምሳሌ እንዲህ ያለ ሁኔታ አንመለከትም። ሥነ ምግባር ዋነኛ ጉዳይ በሆነባቸው ምሳሌዎች ዝርዝር ጉዳዮች ሲተነተኑና ጎላ ብለው ሲወጡ ይታያል።



**§ 64ቀ**
**የዕንቁው ምሳሌ**
**(ማቴ 13፥45-46)**

45 እንዲሁም መንግሥተ ሰማይ ውብ ዕንቁ የሚፈልግ ነጋዴ ትመስላለች። 46 እጅግ ውድ የሆነ ዕንቁ ባገኘም ጊዜ ሄዶ ያለውን ሁሉ ሸጦ ገዛው።


የዚህ ምሳሌ መልእክት ያለፈው ዓይነት ሲሆን፣ የመንግሥተ ሰማይን ክቡር ዋጋም የሚያመለክት ነው። ያንን ለማግኘት ሲባል ማንኛውንም ነገር መስጠት የሚያስቆጭ አይሆንም። ልዩነቱ ነጋዴው እጅግ ዋጋ ያለውን ዕንቁ ሆን ብሎ መፈለጉ ነው። ዕርሻውን የገዛው ሰው በአጋጣሚ ነበር ያገኘው። እንደ ቆርኔሌዎስ አጥብቀን እግዚአብሔርን ብንፈልገውም (ሐሥ 10) ወይም ደግሞ እንደ ሳምራዊቷ ሴት በድንገት ብናገኘውም (ዮሐ 4) የግላችን ልናደርገው ማንኛውንም ዋጋ መክፈል ይኖርብናል። ኢየሱስ እርሱን እንዳይከተሉ በመካከል ጣልቃ የሚገባ ማንኛውንም ነገር እንዲያስወግዱ ለደቀ መዛሙርት ሁሉ ጥሪ ያቀርባል። አንዳንዴ ገንዘብ ሊሆን ይችላል (ማቴ 19፥21)፣ ያም ሆኖ ሙሉ መሥዋዕት መክፈልን ይጠይቃል። «እርስ በርስ የሚቃረን በሚመስል መልኩ ድንቅ ነጻ ስጦታ ቢሆንም፣ ማንኛውንም ዋጋ ያስከፍላል።»[143]

**§ 64በ**
**የመረቡ ምሳሌ**
**ማቴ 13፥47-50**


47 ደግሞም መንግሥተ ሰማይ ወደ ባሕር ተጥሎ የዓሣ ዓይነቶችን የያዘ መረብ ትመስላለች፤ 48 ዓሣ አጥማጆቹ መረቡ ሲሞላላቸው ጐትተው ወደ ባሕሩ ዳር አወጡት፤ ከዚያም ተቀምጠው ጥሩ ጥሩውን እየለዩ በቅርጫት ውስጥ ጨመሩ፤

[143] F. Stagg, *Matthew in The Broadman Bible Commentary*, Vol. 8 (Nashville: Broadman, 1969), p. 159. M. Bailey, "The Parables of the Hidden Treasure and of the Pearl Merchant," *BibSac* 156 (April-June 1999): 175-189፣ በእነዚህ ሁለት ምሳሌዎች ጸጋና ከሰው የሚጠበቅ ነገርን በተገቢው ሁኔታ በማነጻጸር አቅርበዋል።

መጥፎ መጥፎውን ግን ጣሉት:: 49በዓለም መጨረሻም ልክ እንደዚሁ ይሆናል፤ መላእክት መጥተው ኀጢአተኞችን ከጻድቃን በመለየት፣ 50ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ወዳለበት ወደ እቶን እሳት ይጥሏቸዋል::



እዚህ ላይ የተጠቀሰው መረብ ዓሣ አጥማጆች ዘወትር የሚጠቀሙበት ዓይነት መረብ ሳይሆን ሳጄኔ (*Sagene*) የሚባለው ነው:: ይህ ዓይነቱ መረብ ከጀልባ ኋላ ታስሮ ወደ ባሕር የሚጣለው ነው:: ጀልባው ወደ ፊት ሲሄድ ሁሉንም ዓይነት[144] የዓሣ ዘር ይሰበስባል:: ጥሩውን ከመጥፎው፣ ትልቁን ከትንሹ የሚለዩት ወደ ባሕር ዳርቻ ሲመለሱ ብቻ ነው::



ምሳሌው በብዙ መልኩ ከስንዴና ከእንክርዳዱ ምሳሌ ጋር ይመሳሰላል:: ሁለቱም ጻድቃንና ኀጢአት ተደባልቀው እንደማይኖሩና በዓለም መጨረሻ በሚሆነው ፍርድ ግን እንደሚለዩ ያመለክታሉ:: ኢየሱስ ሁለቱንም ለአድማጮቹ ተርጉሟል፤ እግረ መንገዱንም ስለ ገሃነም ምንነት አመልክቷል (ማቴ 13÷42፣50) ልዩነቱ የእንክርዳዱ ምሳሌ ለመጠበቅ አጽንዖት ሲሰጥ የመረቡ ምሳሌ ግን አጽንዖት የሰጠው ለመለየቱ ሥራ መሆኑ ብቻ ነው::

**§ 64ቀ**
**የአዲሱና አሮጌው ሀብት ምሳሌ**
**(ማቴ 13÷51-53)**

51ኢየሱስ «ይህ ሁሉ ገብቷችኋል?» አላቸው:: እነርሱም፣ «አዎን» አሉት::

52እርሱም፣ «ስለዚህ የመንግሥተ ሰማይን ምስጢር የተረዳ ማንኛውም የኦሪት ሕግ መምህር፣ ከከበረ ሀብቱ ከምቾት አዲሱንም አሮጌውንም የሚያወጣ ባለንብረት ይመስላል» አላቸው:: 53ኢየሱስ እነዚህን ምሳሌዎች እንደ ጨረሰ፣ ከዚያ ስፍራ ተነሥቶ ሄደ::



[144] ቃል በቃል ትርጉሙ «ሕዝቦችን ሁሉ»፤ ዓሣዎችን በተመለከተ በዚህ መልክ መናገሩ እንግዳ ቢሆንም ስለ ሰዎች ግን እንዲህ ማለት የተለመደ ነው:: ገና በአገልግሎቱ መጀመሪያ ላይ እንኳ ኢየሱስ የአንድ ሕዝብ ሳይሆን የዓለም ሁሉ መሲሕ መሆኑን አመልክቷል::



ደቀ መዛሙርቱ ምሳሌውን ተረድተው እንደ ሆነ ባቀረበው ጥያቄ፣ «በሚገባ» የግል ቃል መጨመር ይቻላል:: ቁም ነገሩ የምሳሌዎቹን መልእክት መረዳታቸው አይደለም:: ምሳሌዎቹን መረዳታቸውን (በሚገባ) የሚናገሩ ከሆነ የእግዚአብሔርን መንግሥት እውነት የማስተማር ኀላፊነት ይኖርባቸዋል ማለት ነው ጸሐፍት የፈሪሳዊ ትምህርትና መመሪያዎችን እንደ ተቀበሉ ሁሉ፣ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርትም የእግዚአብሔርን መንግሥት ዋና ዋና ነጥቦች ተምረዋል::

እንደ የእግዚአብሔር መንግሥት መምህራን አዲሱንም አሮጌውንም የማምጣት ኀላፊነት ይኖርባቸዋል:: አንድ ባለጠጋ ሰው ቤቱን በጥንታዊና ዘመናዊ ቅርሶች እንደሚያስጌጥ ሁሉ መምህሩም ጥንታዊ እውነቶችንና ዘመናዊ እውነቶችን መግለጽና ማገናዘብ መቻል ይኖርበታል:: እነዚህ ደቀመዛሙርት ኢየሱስ ጥንታዊ የእግዚአብሔር ዕቅድ በአሁኑ ጊዜ መፈጸሙን ማመልከት ይኖርባቸዋል ማለት ነው::

ኢየሱስ ቀኑን ሙሉ ሲያስተምር ከዋለ በኋላ ከቅፍርናሆም ተነስቶ በጀልባ ወደ ጌርጌሴኖን አካባቢ አመራ:: ታዲያ ከእነዚህ የእግዚአብሔር መንግሥት ምሳሌዎች የተማርነው ምንድነው?



1. የእግዚአብሔር መንግሥት የስንዴን እርሻን ትመስላለች:: የስንዴው ዕድገት የሰውን የመቀበል ፍላጐትና (§ 64 ለ) የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት (§ 64 ሐ) መሠረት ያደረገ ነው::

2. ኀጥአንን ከጻድቃን የመለየቱ ሥራ እስከ ፍርድ ቀን ድረስ አይጀምርም ( § 64 መ እና ሠ)::
3. የእግዚአብሔር መንግሥት በከፍተኛ ደረጃ በማደጓ በጐ ተፅዕኖ ታሳድራለች ( § 64 ሠ እና ረ)::
4. የእግዚአብሔር መንግሥት ከሁሉም የበለጠ ዋጋ ያላት ናት ( § 64ሸ፣ ቀ እና በ)::

**§ 65**
**የማዕበሉን ፀጥ ማሰኘቱ**
**(ማቴ 8÷18፣23-27፤[145]**
**ማር 4÷35-41፤**
**ሉቃ 8÷22-25**

ብርቱና ጠቃሚ ታሪክ ነው:: በሦስቱ ወንጌሎች ውስጥ ኢየሱስ ግዑዝ ነገሮች ላይ ኀይሉን ሲገልጽ የመጀመሪያው ነው:: ሌላው ቀርቶ በጣም በሚቀርቡት ተከታዮች ላይ እንኳ ፍርሃትና መገረምን አሳድሮአል:: አንዳንዶች ሁኔታውን አጋጣሚ ወይም የሰዎች ምናብ የፈጠረው ነው የሚል ገለጻ ሊሰጡት ሞክረዋል:: ይሁን እንጂ አንዱም እንኳ ቢሆን በብዙ የዓይን ምስክሮች ፊት የተደረገውን ማስተባበል አይችልም:: በተጨማሪም ልዕለ ተፈጥሮአዊ አሠራር መኖሩን የሚክዱ ሰዎችም እንኳ ቢሆኑ ከሳይንስም ሆነ ከፍልስፍና አንጻር በቂ መከላከያ አይኖራቸውም::

[145] ማቴዎስ ይህንን ክስተት ከቅደም ተከተላዊ ቦታው በማውጣት ሌሎች ብዙ ተአምራትን ባሰፈረበት ከምዕራፍ 8-9 ባለው መካከል አስቀምጦታል:: ይህንን ያደረገው በዓላማ ነው:: አጠቃላይ በሆነ መልኩ ተአምራቱ «ይህ ኢየሱስ ማነው?» ለሚለው ቀላል ጥያቄ መልስ ይሰጣሉ:: በፈሪሳውያን ተቃውሞ፣ በሕዝቡ ግንዛቤ ጉድለት፣ በገዛ ቤተሰቡ ተጠራጣሪነት፣ ሌላው ቀርቶ በደቀ መዛሙርቱ አለማስተዋል መካከል እንኳ ተአምራቱ ስለ ኢየሱስ ማንነት የሚያመለክቱት አላቸው:: P.F. Feiler, "The Stilling of the Storm in Mathew: A Response to Gunther Bornkamm," *JETS* 26/4 (1983): 399-406 ጋር ያነ::



በዚህ ጊዜ ይኸው ሁኔታ በአንድ ዓመት በታሪክ ውስጥ ከተፈፀመ እውነታ ያለፈ ሆኖአል:: ተአምራት በተግባር የተገለጹ የእግዚአብሔር መንግሥት ምሳሌዎች[146] ናቸው:: በዚያው ሌሊት ኢየሱስ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት በምሳሌዎች ብቻ ከሰበከ በኋላ የመንግሥቱን ምንነት በተግባር ለማሳየት ሁለት ነገሮችን አደረገ:: በመጀመሪያ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ኀይል ገለጸ (ከመዝ 104÷7፤ 107÷23-30 ጋር ያነ)::[147] በሌላ አነጋገር የእግዚአብሔር መንግሥት የሰውን ልጅ ታሪክ ሰብሮ ገባ ማለት ይቻላል:: ሁለተኛ ኢየሱስ ሕዝቡን ከማዕበሉ አዳነ::[148]

**(ማር 4÷35-38፤**
**ማቴ 8÷18, 24-25፤**
**ሉቃ 8÷23-24 ጋር**
**ያነ)**

35ያን ቀን በመሸ ጊዜ፣ (ብዙ ሰዎች በዙሪያው ባዩ
ጊዜ[ማቴ]) «ወደ ማዶ እንሻገር» አላቸው:: 36እነርሱ
ሕዝቡን ትተው በጀልባዋ ውስጥ እንዳለ በዚያው
ይዘውት ሄዱ፤ ሌሎች ጀልባዎችም አብረውት ነበሩ::
37(ድንገት[ማቴ]) በዚህ ጊዜ ኀይለኛ ዐውሎ ነፋስ ተነሣ፤ ማዕበሉም ውሃ እስኪሞላት
ድረስ ጀልባዋን ያናውጣት ነበር:: (አደጋ አፋፍ ላይ ደረሱ[ሉቃ]):: 38ኢየሱስ ግን ትራስ
ተንተርሶ ከጀልባዋ በስተ ኋላ በኩል ተኝቶ ነበር:: እነርሱም ቀስቀሰውት፣ (ጌታ
ሆይ[ሉቃ]) «መምህር ሆይ፣ ስናልቅ አይገድህምን?» አሉት::

[146] Cf. C.L Blomberg, "New Testament Miracles and Higher Criticism: Climbing up the Slippery Slope," *JETS* 27/4 (1984): 425-438.
[147] P.J Achtemeier, "Person and Deed: Jesus and the Storm Tossed Sea," *Int* 16 (1962): 169-176.
[148] ይህ ክርስቲያኖች ስለሚልፉበት የሕይዋት ማዕበል ኢየሱስ አስቀድሞ ማየቱን የሚያመለክት ምሳሌ መሆኑ ተነግሯል (ለምሳሌ፣ N. Pittenger, "Great Calm" *ExpT* 85 [1974]: 209-210):: ምንም እንኳ ኢየሱስ በተግባርና ሰው ይህን ባይሆንም፣ ከዐውዱ ማየት የሚቻለው ኢየሱስ ሕዝቡን የሚያድን ሩኅሩኅ ጌታ መሆኑን ነው:: አንዳንዶች ደግሞ ከዚህ ምንባብ አጋንንትን ስለማስለቀቅ፣ ዮናስንና እግዚአብሔር በባሕር ላይ ያለውን ሥልጣን መመልከታቸውን ይናገራሉ (መዝ 104÷7፤ 107÷23-30)::

ኢየሱስ ቤት ውስጥ በምሳሌዎች አማካይነት እያቀረበ የነበረውን ስብከት ጨርሶአል:: ምናልባትም በሩ ላይ ወደ ውጭ ሲወጣ እንዲያስተምራቸው እየጠየቁ ያሉ ሰዎች ሳይኖሩ አይቀሩም:: ከሰፈር ውጭ ካልሄዱ በቀር በዚያ ሌሊት መተኛት እንደማይችሉ ለደቀ መዛሙርቱ ግልጽ ሳይሆንላቸው አልቀረም (ማር 4÷35):: ስለዚህም በድንገት ተነስተው ከዚያ ቦታ በጀልባ ሄዱ፤ የቱንም ያህል ቢፈጥኑ እንኳ ከሕዝቡ መሰወር አልቻሉም:: ሕዝቡ በሌሎች ጀልባዎች ሆነው ኢየሱስን መከተል ሞከሩ:: ሆኖም ብዙም ሳይቆይ መረዳት እንደሚችሉት ተሳስተው ነበር:: ኀይለኛ ማዕበል እየተነሣ ነበር:: ማዕበሉ ወደ ኋላ ይመልሳቸዋል፤ አልያም ወደ ባሕሩ ያሰጥማቸዋል::

በገሊላ ባሕር ሁሌም እንደሚሆነው ማዕበሉ በድንገት ነበር የተነሣው:: የገሊላ ባሕር ከባህር ወለል በታች 685 ጫማ ላይ ያረፈ ሲሆን፤ እስከ 2000 ጫማዎች ከፍታ ባላቸው ኮረብቶች ተከብቦአል:: እነዚህን ኮረብቶች ተሻግሮ የሚመጣው ነፋስ በከፍተኛ ኀይል ቁልቁል ይወርድ ነበር:: «ኃይለኛ ዐውሎ ነፋስ» ለማለት የተጠቀመበት ግሪክ ቃል ላይላፐስ [*lailaps]* የተሰኘው ሲሆን 'ሀሪኬን' በመባል የሚታወቀውን የዐውሎ ንፋስ ዐይነት ይመለከታል:: እጅግ አደገኛ ዐውሎ ነፋስ ነበር::

በዚህ ጊዜ ኢየሱስ ትራስ (ምናልባት ከፍየል ቆዳ የተሠራ) ተንተርሶ ተኝቶ ነበር:: ስለ ኢየሱስ መተኛት ሲነገረን ይህ የመጀመሪያ ጊዜ ነው:: ጀልባዋ፣ «በኀይለኛ ዐውሎ ነፋስ» እየተናወጠችና «አደጋ ላይ» ባለችበት ጊዜ መሆኑ ደግሞ ይበልጥ አስገራሚ ያደርገዋል:: ሁለቱም ቃሎች ቁርጡ የታወቀ ሁኔታን የሚያመለክቱ ባለመሆናቸው ደቀ መዛሙርቱ ምን ያህል ከባድ ጭንቀት ውስጥ መሆናቸውን መረዳት ይቻላል:: በሌላ አነጋገር ጀልባዋ በውሃ እየተሞላች ነበር:: በጣም ጠንካራ ብትሆንም ፍጥነት የሌላት የዓሣ ማጥመጃ ጀልባ ነበረች::

ዐሥራ ሰዎች «ቤት ሙሉ» ሊሆኑ ይችላሉ፤ ማዕበሉ የጀልባይቱን ጐን እየመታ ውስጧ ሲገባ እነርሱም ቀስ በቀስ ወደ ባሕሩ



ጥልቅ ሊሰጥሙ ነው:: ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስን ቀስቅሰው፣ «ጌታ ሆይ፤ ጌታ ሆይ፤ ማለቃችን እኮ ነው አሉት» ( ሉቃ 8÷24):: በዚህ ሁሉ መጣል መተኛት መቻሉ ደቀ መዛሙርቱን ከማስገረም አልፎ ሳያናድዳቸው አልቀረም:: ለተደረገው ተአምር የሰጡት ምላሽ ኢየሱስ ማዕበሉን ፀጥ ማድረግ እንደሚችል በፍጹም ያልጠበቁት ጉዳይ እንደ ነበር:: ያሳያል እጆች ሁሉ ተረባርበው በመቅዘፍ በተቻለ ፍጥነት ጀልባዋን ከማዕበሉ ማውጣት እንዳለባቸው ነበር ያሰቡት::

**ማቴ 4÷39-41**
**ከሉቃ 8÷25፤ ማቴ**
**8÷27 ጋር**

39እርሱም ነተሥቶ ነፋሱን ገሠጸው፤ ባሕሩንም፣ «ጸጥ፣ ረጭ በል!» አለው ነፋሱም ጸጥ፣ ረጭ አለ፤ ፍጹምም ጸጥታ ሆነ::

40ደቀ መዛሙርቱንም፣ «ስለ ምን እንዲህ ፈራችሁ? እስከዚህ እምነት የላችሁምን?» አላቸው::

41እነርሱም በፍርሀት ተውጠው (በፍርሀትና በመደነቅ[ሉቃ]) እርስ በርሳቸው፣ «ነፋሱም ሞገዱም የሚታዘዙለት ይህ ማን ነው?» (ምን ዓይነት ሰው ነው?[ማቴ]) ተባባሉ!

ነፋስና ማዕበሉን በተመለከተ ጥቅም ላይ የዋሉት ገሠጸው (*epitiman*) እና ጸጥ ረጭ (*Phimoun*) የተሰኙት ቃላት ጋኔን ስላስወጣበት ሁኔታ በተነገረውም ታሪክ ተጠቅሰዋል (ከማር 1÷25 ጋር ያነጻጽሩ) :: ስለዚህም ኢየሱስ ባሕሩን ጸጥ ባሰኘበትና ጋኔን ባስወጣበት ሁኔታ ጥብቅ ግንኙነት ነበት ማለት ነው:: ሁሉም በእርሱ ቁጥጥርና ሥልጣን በታች ናቸው፤ ሁለቱም የኢየሱስን መለኮታዊ ሥልጣን ያመለክታሉ::

ተፈጥሮ እንኳ ለኢየሱስ ይታዘዛል፤ የገሊላ ባሕር ጸጥ አለ:: እንደፈጣሪነቱና (ዮሐ 1÷18፤ ቆላ 1÷16) ፍጥረቱን ሁሉ ደግፎ ያቆመ እንደመሆኑ (ቆላ 1÷17 ዕብ 1÷3) አጽናፈ አለሙ የጌታውን ትእዛዝ ይሰማል::

እምነት የጐደላቸው በመሆኑ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን መገሠጹን የሚነግረን ማርቆስ ብቻ ነው (ይህን ደግሞ አመልክቷል (ከማር 7÷18፤ 8÷17-18፣21፣32፣33፤ 9÷19 ጋር ያነጻጽሩ):: ኢየሱስ በሕመም፣ በአጋንንትና ሞት ላይ ያለውን ኀይል አሳይቷል:: አሁን ደግሞ በግዑዙ ፍጥረት ላይ እንኳ የበላይ መሆኑን አሳየ:: ለዓሣ አጥማጆች እንዲህ ያለው ነገር በፍጹም የተለመደ አይደለም:: ስለሆነም እንዲህ ላለው ተአምር እምነት ባያሳዩ የሚገርም አይሆንም:: በፍጹም ያልታሰበና ያልተጠበቀ ነገር ነበር::

በቅፍርናሆም «ይህ ነገር ምንድን ነው?» በማለት ጠይቀው ነበር (ማር 1÷27):: አሁን ግን ጥያቄው፣ «ይህ ግን ነው?» የሚል ሆኗል፤ ይህ ተአምር ለእንዲህ ዐይነቱ ጥያቄ መልስ ለመስጠት የታቀደ ነበር:: ፈሪሳውያን እየተቃወሙ፣ ሕዝቡም እየተገረሙ ነበር:: ሌላው ቀርቶ በጣም የሚቀርቡት ሰዎች እንኳ በእርግጥ ማን መሆኑን አላወቁም ነበር:: ተግባሩ ግን እውነትን ገለጠ:: ኢየሱስ በሰው አምሳል የተገለጠ እግዚአብሔር ነው::

## § 66
## በጌርሴኖን አጋንት ያደረበት ሰው መፈወሱ
## (ማቴ 8÷28-34 ማር 5÷1-20፤ ሉቃ 8÷26-39)

እንዲህ ያለ ታሪክ ፍጹም ያልተለመደ ነው:: ኢየሱስ ነፋስን ተቆጣጥሯል:: አሁን ደግሞ መንፈሳዊ የጨለማ ኀይላትን ሊቆጣጠር ነው::

(ማር 5:)1ባሕሩን ተሻግረው ጌርሴኖር (ከገሊላ ባሻገር ወዳለው[ሉቃ]) ወደ ተባለ አገር መጡ::[ሀ] 2ኢየሱስ ከጀልባ እንደ ወረደ፣ ርኩስ መንፈስ ያደረበት ሰው (ሁለት ሰዎች[ማቴ]) ከመቃብር ቦታ ወጥቶ ሲገናኘው ወደ እርሱ መጣ:: (ይህ ሰው ለብዙ ጊዜ ልብስ ሳይለብስ፣ በቤትም ሳይኖር[ሉቃ]) 3ይህ ሰው በመቃብር ቦታ ውስጥ የሚኖርና ማንም በሰንሰለት እንኳ ሊያስረው የማይችል ነበር:: 4ብዙ ጊዜ በእግር ብረትና በሰንሰለት ይታሰር ነበር (እየታሰረ ቢጠበቅም[ሉቃ])፤ ነገር ግን የእጅ ሰንሰለቱን ይበጥስ፣ የእግር ብረቱንም ይሰብር ነበር:: (ያደረበት ጋኔን ወደ በረሐ ይነዳው ነበር[ሉቃ]):: ማንም ይዞ ሊያቆየው የሚችል አልነበረም:: (በዚያ መንገድ ሰው ማለፍ እስከማይችል ድረስ እጅግ አደገኞች ነበሩ[ማቴ]):: 5በመቃብሮቹና በተራራዎቹ መካከል ቀንና ሌሊት እየተዘዋወረ በመጮኸ ሰውነቱን በድንጋይ ይቀራርጥ ነበር::

ሦስቱ ወንጌሎች የሚያቀርቡትን ታሪክ በማያያዝ ብንመለከት ኢየሱስ ከቅፍርናሆም የተነሣው ከምሽቱ ዐሥራ ሁለት እስከ አንድ ሰዓት ባለው መካከል ሊሆን እንደሚችል እንረዳለን (ከማር 4÷35 ጋር ያነጻጽሩ):: በማዕበሉ ምክንያት ባሕሩን ተሻግሮ ለማለፍ (ከ8 ኪሎ ሜትር ያነሰ) ከሦስት እስከ አራት ሰዓት ሳይወስድባቸው አልቀረም:: ስለሆነም በዚህ ጊዜ ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ሊሆን ይችላል ማለት ነው:: ሥራው የተፈፀመው በምሽቱ ዐሳማዎችን ሲጠብቁ የነበሩ እረኞች ፊት ነበር::

ቦታው ከገሊላ ማዶ ከባሕሩ ምሥራቅ ዳርቻ የአሕዛብ ወረዳ ነበር:: ወንጌል ወደ አሕዛብ መድረሱን ተከታትሎ የሚተርክ እንደ መሆኑ መጠን ይህ ለሉቃስ የተለየ ፋይዳ ነበረው:: ማቴዎስ የሚነግረን ቦታው ጌራሳ ሳይሆን ጌርሴኖን መሆኑን ነው:: ጌርሴኖን 26 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ከባሕር በስተኋላ 11 ኪሎ ሜትር ላይ የነበረች በጣም ታዋቂ ከተማ ነበረች:: ስለሆነም ቦታው የጌርሴኖን ክልል ውስጥ ነበር ለማለት ነው:: ከባሕሩ አንድ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ጌራሳ የተባለች ትንሽ ከተማ ነበረች:: ዐሣሞቹ እየተንደረደሩ ወደ ባሕር የገቡበት ባሕር አጠገብ ያለው ተራራ የነበረው በዚህ ስለ ነበር፣ ኢየሱስ ያረፈው ምናልባት እዚህ ቦታ ሳይሆን አይቀርም:: ያ አካባቢ ጌሬሳ ነበር ማለት ትክክል አይሆንም:: የስማቸው ተመሳሳይ መሆን አንዳንድ ጸሐፊዎችን ግራ አጋብቶአል::

ይህ ቦታ ጠባብ የባሕር ዳርቻ ያለው ሲሆን ዋሻዎች ከበዙባቸው ከፍ ያሉ ገደሎች ጋር በቀጥታ ይገናኛል:: የሥነ ቁፋሮ ባለሙያዎች የሰው አካልን ማኖር የሚችሉ ጕድጓዳ ቦታዎች ያለበት ሃያ ስኩዌር ጫማ የሚሸፍን የመቃብር ቦታ አግኝተዋል:: የሞቱ ሰዎች የሚቀበሩት እዚህ ነበር:: አንዳንድ ድሆች ይህን ቦታ ለመቃብር ብቻ ሳይሆን ለመኖሪያነት ጭምር ይጠቀሙበት ነበር:: በዚህ ዘመን ግን ይህ የተለመደ አይደለም::

ማቴዎስ ኢየሱስን የተገናኙት ሁለት አጋንት ያደረባቸው ሰዎች እንደነበሩ ይናገራል:: ለሉቃስና ማርቆስ ግን ከሁለቱ ዋናና እየተናገረ የነበረው ላይ ነበር ትኩረታቸውን ያደረጉት:: እየሮጠ ወደ ኢየሱስ መጥቶ እግሩ ሥር ወደቀ:: እዚህ ላይ አጋንት ያደሩበት ሰውን በተመለከተ ትኩረት የሚያሻው ጉዳይ እንመለከታለን (Liefeld, P .913 ) (1) ዕርቃኑን ነበር፣ ይህ ለሰው ክብር የማይሰጥ መሆኑን ያመለክታል፤ (2) ከማኅበረሰቡ የተገለለ ነበር፤ (3) ተገቢ ባልሆነ ቦታ ይኖር ነበር (መቃብር)፤ (4) የኢየሱስን አምላክነት ተገንዝቦአል፤ (5) ጋኔኑ አንደበቱን ተቆጣጥሮት ነበር፤ (6) ይጮኽ ነበር፤ (7) ከሰው በላይ የሆነ ኀይል ነበረው፤ ሰንሰለትን መበጣጠሱ ምን ያህል ብርቱ እንደ ነበር ያሳያል:: ከዚህ ሁሉ በላይ ገዳይ ብቻ ሳይሆን ራስን ለማጥፋት ሙከራ የሚያደርግም ነበር (ማቴ 8÷28፤ ማር 5÷5):: የሰፈሩ ሰው የሚያወራለትና በጣም የሚፈራው ነበር::

[6]ይህም ሰው ኢየሱስን ከሩቅ ባየው ጊዜ ወደ እርሱ ሮጦ ከፊቱ ተንበርክኮ ሰገደለት፤ [7]በታላቅ ድምፅ ጮኾም፣ «አንተ የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ሆይ፤ ከእኔ ምን አለህ? እንዳታሠቃየኝ በእግዚአብሔር ይዤሃለሁ!» (እለምንሃለሁ[ሉቃ]) አለው:: [8]ይህንንም ያለው ኢየሱስ፣ «አንተ ርኩስ መንፈስ ከዚህ ሰው ውጣ! ብሎት ስለ ነበር ነው::»

ማር 5÷6-10
ሉቃ 8÷28 31፤
ማቴ 8÷29 ጋር



[9]ከዚያም ኢየሱስ፣ «ስምህ ማን ነው?» ብሎ ጠየቀው:: «ብዙ ነንና ስሜ ሌጌዎን ነው» አለው:: [10]ከአገር እንዳያስወጣቸውም (እንዳይሰድዳቸው ብሎ እንዳያዛቸውም[ሉቃ]) አጥብቆ ለመነው::

«ከእኔ ምን አለህ?» (ቃል በቃል:- ለእኔስ ለአንተስ ምንድን ነው?) የሚለውን ዘይቤያዊ አነጋገር በተለያየ መንገድ መረዳት ይቻላል፤ «ምን የጋራ ነገር አለን?» ወይም፣ «ከእኔ ጋር ምን ጉዳይ አለህ?» ወይም፣ «ለምን በሕይወቴ ጣልቃ ትገባለህ?» ማለት ሊሆን ይችላል:: በመሠረቱ የዚህ ፍጥጫ ትርጉም ወይም ፋይዳ ምን እንደ ሆነ ኢየሱስን እየጠየቀ ነበር::

አጋንንት የነበሩበት የዚህ ሰው ንግግር ሁለተኛ ክፍል ማለትም፣ «የልዑል እግዚአብሔር ልጅ» ከአጋንንት አንደበት መሰማቱ ግር የሚያሰኝ ነው:: በብሉይ ኪዳን «ልዑል እግዚአብሔር» የይሆዋ ሐቀኛ ወይም መደበኛ መጠሪያ ስም ነበር (ዘፍ 14÷18-22፤ ዘኍ 24÷16፤ ኢሳ.14:14፤ ዳን 3÷26፤ 4÷2):: እንዲህ ያለ የተቀደሰ ስም በአጋንንት አንደበት የተጠራው ለምን ነበር? ምናልባት ኢየሱስ የጋኔኑን ስም ከመጥራቱ በፊት፣ ጋኔኑ የእግዚአብሔርን ስም ለመጥራት መሞከሩ ሊሆን ይችላል:: በዚያን ዘመን በጋኔኑ ላይ አይሎ ለመገኘትና ማስወጣት ከተፈለገ ጋኔኑን ለማባረር እንዲቻል ኃይለኛ የሆኑትን ሰዎች ወይም «አማልክት» ስም መደርደር የተለመደ ነገር ነበር:: ይበልጥ ታዋቂ ወይም ተፈሪ የሆኑትን ስሞች ማቅረብ የቻለ ቀድሞ እንደሚያሸንፍ ይታሰብ ነበር::

ለዚህ ሰው ብርታት የሰጡት ብዙ የስም ዝርዝሮች ነበሩ:: እርሱ የተናገረው ግን ስለ አንዱ ማለትም ስለ ሌጌዎን ብቻ ነበር:: ይህ ቃል ባጠቃላይ 6000 ጭፍራዎችን ስላካተተው የሮም ሠራዊት የሚገልጽ ነበር:: ሆኖም የጭፍራው ቁጥር የግድ ቃል በቃል መወሰድ አይኖርበትም:: በአይሁድ አነጋገር ፈሊጥ ብዙ አጋንንት የሰፈሩበትን

ሰው፣ «ሌጌዎን» በማለት መጥራት የተለመደ ነበር:: ሰውየው በጣም ብዙ መናፍስት ሰፍረውበት ስለ ነበር ከባድ ችግር ውስጥ ነበር::

አጋንንቱ በቁጥር ከኢየሱስ የበለጡ ነበሩ:: ያም ሆኖ ግን በጣም ፈርተውታል:: እርሱን ለመቅጣት በቂ ኀይልና ሥልጣን እንዳለው አውቀዋል:: እንዲያውም በጥልቁ ውስጥ የሚታሠሩበት የሚመጣው የፍርድ ቀን እንደቀረበም በሚገባ ተገንዝበዋል (ማቴ 25÷41፤ 2ጴጥ 2÷4፤ ይሁዳ 6 ጋር ያነ):: ጊዜው ሳይደርስ እንዳይቀጣቸው ጌታን ለመኑት::

«እንጦርጦስ» የሚለው ቃል በመጀመሪያ «ጥልቁ» የሚል ትርጉም ነበረው:: በአጠቃላይ ሙታን የሚኖሩበትን ስፍራ የሚመለከት ነው:: ጥንት ከተፈጠረው ምስቅልቅል አንሥቶ ክፉ መናፍስት እስከሚታሠሩበት ጊዜ ድረስ ለነበሩባቸው ሁኔታዎች የሚሆኑ የተለያዩ ትርጉሞች አሉት (ሮሜ 10÷7፤ ራእ 9÷1-3፤ 11÷7፤ 17÷8፤20÷1-3 ጋር ያነ):: ማቴዎስ፣ «ጊዜው ሳይደርስ» የሚል ማሳሰቢያ (በ8÷29)፣ ጨምሯል:: የኋላ ኋላ ሰይጣንና አጫፋሪዎች ሁሉ ይቀጣሉ በወህኒም ተጥለው ይዘጋባቸዋል (ራእ 20÷1-3፣10):: ምሕረት እንዲደረግላቸውም አይጠይቁም:: ምክንያቱም፣ ይህ እንደማይቻል ያውቃሉ:: ሆኖም ሙሉ ጊዜያቸውን በምድር ላይ ችግር ለመፍጠር ያውሉት ዘንድ ይጠይቃሉ::

ማር 5÷11-13
ማቴ 8÷30-31
ጋር

[ከእነርሱ ትንሽ ራቅ ብሎ[ማቴ]] 11በአቅራቢያውም
በሚገኝ ኮረብታ ላይ ትልቅ የዐሣማ መንጋ ተሰማርቶ
ነበር:: 12ርኩሳን መናፍስቱም ኢየሱስን [የምታስወጣን
ከሆነ[ማቴ]]፣ «ወደ ዐሣማዎቹ ስደደን፣ እንድንገባባቸውም
ፍቀድልን» ብለው ለመኑት:: 13እርሱም ፈቀደላቸው::
ርኩሳን መናፍስቱም ወጥተው በዐሣማዎቹ ገቡባቸው፤ ሁለት
ሺህ ያህል ዐሣማዎችም በገደሉ አፋፍ በመንደርደር ቁልቁል
ወርደው በባሕር ውስጥ ሰጠሙ::



በዚያ መንጋ 2000 ያህል ዐሣማዎች ነበሩ:: የአጋንንቱና የዐሣማዎቹ ቍጥር ትክክል ከሆነ በአንድ ዐሣማ ሦስት አጋንንት ገብተው ነገር ማለት ይቻላል:: ራሳቸውን ማጥፋታቸውም አይገርምም:: ይሁን እንጂ፣ ሁኔታው የሰዎችን ንብረት በማጥፋት ኢየሱስን አያስጠይቀውምን? በፍጹም አያስጠይቀውም:: ኢየሱስ ፈቀደላቸው እንጂ ያንን እንዲያደርጉ አላነሳሳቸውም:: ሰይጣን በሠራው ሥራ እግዚአብሔርን መውቀስ የለብንም:: ከዚህም በላይ ዐሣማዎች በአይሁድ ዘንድ ርኩሳን እንስሳት ነበሩ:: ኢየሱስ ለዐሣማ መንጋ ክብር እንዲሰጥ መጠበቅም የለብንም:: ዋናው መልእክት ከ2000 ዐሣማዎች ይልቅ ኢየሱስ ለአንድ ነፍስ ከፍ ያለ ግምት ያለው መሆኑ ነው:: ይህን ደግሞ መንቀፍ አይቻልም::

አጋንንቱ ዐሣማዎቹ ውስጥ እንዲገቡ የጠየቁትና የገቡባቸውን እንሰሳት ወዲያውኑ ከገደል አፋፍ እንዲወረወሩ ያደረጉት ለምን ነበር? ምናልባትም ለዐሣማዎቹ ዕልቂት ኢየሱስ ተጠያቂ እንደሚሆን ስለሚያውቁ ሊሆን ይችላል:: በዚህም ምክንያት በኢየሱስ ላይ ችግር እንዲፈጠር ጥረት እያደረጉ ነበር:: በዚህ ላይ ደግሞ አጋንንት በባሕርያቸው አጥፊዎች ናቸው:: በዐሣማዎቹ ላይ ያደረጉት በሰውዬው ላይ ካደረጉት ምንም የተለየ አልነበረም:: ሰይጣንና ጀሌዎቹ የራሳቸው ለሆኑት ያስባሉ የሚባለው እውነት አይደለም:: እጆቻቸው ያረፉበትን ማንኛውንም ነገር ማጥፋት መለያ ባሕርያቸው ነው::

ማር 5÷14-17
ማቴ 8÷34 ሉቃ
8÷37 ጋር

14እረኞቹ ሸሽተው ሄዱ፤ ወሬውን በከተማና
በገጠር አዳረሱት፤ ሕዝቡም የሆነውን ለማየት ካለበት
ወጣ:: [መላው የከተማው ነዋሪ ኢየሱስን ለመገናኘት
ወጣ[ማቴ]] 15ወደ ኢየሱስም በመጡ ጊዜ፣ የአጋንንት
ሠራዊት አድሮበት የነበረው ሰው ልብስ ለብሶና

አእምሮው ተመልሶለት በዚያ ተቀምጦ አዩት [ኢየሱስ እግር ሥር[ሉቃ]] ፈሩም። [16]ይህን
ያዩ ሰዎችም አጋንንት ስላደረበት ሰው የተደረገውንና ስለ ዐሣማዎቹም ለሕዝበ
አወሩ። [17]ከዚያም ሕዝቡ ታላቅ ፍርሃት ስላደረባቸው[ሉቃ] አገራቸውን ለቆ
እንዲሄድላቸው ኢየሱስን ይለምኑት ጀመር።

ይህ ሲሆን ወደ እኩለ ሌሊት እየተቃረበ ሳይሆን አይቀርም። እረኞቹ (ወይም ዓሳማ ጨባቂዎቹ) የሆነውን ሁሉ እያወሩ በሚሆዱበት ጊዜ የዐሣማዎቹን ባለቤቶች እያነቋቸው ነበር። በዚያ ውድቅት ሌሊት አስቸኳይ የከተማ ነዋሪዎች ስብሰባ ተደረገ።

አጋንንት አድረውበት የነበረው ሰው ከስንት ጊዜ በኋላ እንደሆነ ባይታወቅም ለመጀመሪያ ጊዜ ነጻነቱን አገኘ። የከተማው ሰዎች ጕሕ ሲቀድ ማለዳ ባሕሩ ዳር ተሰበሰቡ። አጋንንት የነበሩበት ሰው ምናልባትም የኢየሱስን መጐናጸፊያ እንደ ልብስ ለብሶ፣ አእምሮው ተመልሶለት፣ በዚያ ተቀምጦ አዩት። ይህን ሲያዩ በጣም ፈሩ። ግን፣ ያስፈራቸው ምን ነበር? አጋንንት የነበሩበት ሰው ምን ያህል ኀይለኛ እንደ ነበርና በሰንሰለት እንኳ አስረው ሊያቆዩት እንዳልቻሉ ያውቃሉ። ኢየሱስ ግን እነርሱ ያልቻሉትን አድርጓል። እንደዚያ ያለው ኃይል ከእነርሱ በላይ ነበር። ገንዘብ የሚያስገኝላቸው ዋነኛ ምንጭ እንደ ወደመባቸውም ያውቃሉ። ለዚህ ዳፉ የሚያደርጉት ሰው ይፈልጋሉ። ለዚህ ዓለማ ኢየሱስን አግኝተዋል። የእርሱን ሥልጣን ከመቀበል ይልቅ፣ በፍርሃት ምክንያት ከአገራቸው እንዲወጣላቸው አደረጉ።

ይህ የማኅበረሰቡ ውሳኔ («ሕዝቡ ሁሉ» ከሚለው ጋር ያነ) ነው። የሁኔታውን ውስብስብነት እነርሱ ሊኖራቸው የሚገባውን አቋም ከማስላት ይልቅ ኢየሱስ ከአገራቸው እንዲሄድላቸው መጠየቁ ለእነርሱ ቀላል ነው። በጣም ብዙ ዓሣዎችን ካጠመዱ በኋላ ጴጥሮስ ኢየሱስን ከእርሱ እንዲለይ ጠይቆት ነበር (ሉቃ 5፥8)። ሆኖም አንድ ትልቅ ልዩነት ነበር። ጴጥሮስ እንደዚህ ያለው ስለ ክርስቶስ ቅዱስነትና ስለ



እርሱ ኃጢአተኝነት ፍንጭ ስለታየው ነበር። እነዚያ ሰዎች እንደዚያ ያደረጉት የኢየሱስን ኀይል ፍንጭ በማየታቸውና ከዚህ ኀይል ራሳቸውን ለመጠበቅ ሲሉ ነበር። ኢየሱስ ጴጥሮስ በነበረበት ቦታ ቆይቶ አገለገለ። ከጌርሴኖን ሰዎች አለማመን የተነሣ በጠየቁት መሠረት ኢየሱስ አገራቸውን ለቆ ሄደ። እርሱ ጨዋ ነው። ማንንም አይጫኑንም።

**ማር 5፥18-20**

[18]ኢየሱስ ወደ ጀልባዩቱ በሚገባበት ጊዜ፣
አጋንንት አድሮበት የነበረው ሰው አብሮት ለመሄድ
ለመነው። [19]ኢየሱስ አልፈቀደለትም፤ ነገር ግን፣ «ወደ
ቤትህ ሂድ ለዘመዶችህም ጌታ ምን ያህል ታላቅ ነገር እንዳደረገልህና ያሳየህን
ምሕረት ንገራቸው አለው። [20]ሰውየውም ሄደ፤ ኢየሱስ ያደረገለትን ነገር ሁሉ ዐሥር
ከተማ በተባለው አገር ያወራ ጀመር፤ የሰሙትም ሁሉ ተደነቁ።

አጋንንት የነበሩበት ሰው አብሮት እንዲሄድ ኢየሱስን ይለምነው ጀመር። አብሮት ለመሄድ የፈለገው ለምን ነበር? ኢየሱስን በመውደዱና ባደረገለት ነገር ባለውለታነት ስለተሰማው እንደሚሆን ግልጽ ነው። ወደ ኢየሱስ ተጠግቶ ከኖረ አጋንንቱ እንደ ገና ሊገቡበት እንደማይችሉ ዐውቆአል። ኢየሱስን ከመውደዱ ባለፈ ግን ለእነዚያ የጌርጌሴኖን ሰዎች አጋንንት የነበሩበት ሰው እንደሆነ ነበር የሚታወቀው። በዚያ አካባቢ ለነበረው ህብረተሰብ ስለ ማንነቱ የሚያሳስብ ጠባሳ በሰውነቱ ላይ ምን ጊዜም ይዞ ነው የሚኖረው። የከተማው ሕዝብ ከ2000 ዐሣማዎች እልቂት ጋር በተዘመደ ሁኔታ ያስተውሰዋል። እርሱ ግን አዲስ ጅማሬና አዲስ ማንነት ይፈልጋል። እንደ ኢየሱስ ግን በዚያው በነበረበት ማኅበረ ሰብ በቀድሞ ማንነት መመስከሩ ይበልጥ አስፈላጊ ነበር።

ኢየሱስ ሰውየውን ወደ ቤተ ሰቡ ላከው። የሚያስተላልፈው መልእክት ግልጽ ነው። ስለ ሁለት ነገሮች መናገር አለበት፤ (ሀ) «ጌታ ምን ያህል ታላቅ ነገር እንዳደረገለት» እና (ለ) «ያሳየህን (ያሳየውን)

ምሕረት»:: ብዙውን ጊዜ ወንጌል የማዳረሱን ሥራ ውስብስብ እናደርገዋለን:: እዚህ ላይ የምናየው የአንድ ምሽት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ብቻ ያገኘውን ከአጋንንት ነፃ የወጣውን ሰው ነበር:: ወደ ቤቱ በቀጥታ ሄዶ ታሪኩን ተናገረ:: ውጤቱ እጅግ የሚገርም ነበር:: ወደ መላው ከተማ ብቻ ሳይሆን፣ ዲካፖሊስ በተባሉት ዐሥር የግሪክ ከተሞች[149] ስብስብ ሁሉ በመሄድ ታሪኩን ተናገረ::

ታሪኩ እዚህ ላይ አላበቃም:: በሚቀጥለው ጊዜ ኢየሱስ ወደዚያ አካባቢ ሲመለስ ከፍ ያለ አቀባበል ተደርጐለት፣ 4000 ሰዎችንም መግቦአል እንዲህ ሊሆን የቻለው ከዚህ ሰው ምስክርነት የተነሣ መሆኑ ጥርጥር የለውም::

**§67**
**ሁለት ሴቶችን መፈወሱ**
**(ማቴ 9÷18-26፤ ማር 5÷21-43 ሉቃ 8÷40-56)**

ቀደም ብሎ በነበረው ቀን በምሳሌዎች ካስተማረ፣ በዚያው ሌሊት ባሕሩን ጸጥ ካሰኘ፣ አጋንንት ያደሩበትን ሰው ከፈወሰውና ከዚያ አገር ተገፍቶ ከወጣ በኋላ ኢየሱስ ጥቂት ዕረፍት ሳያደርግ አልቀረም:: ጀልባ ውስጥ እያለ ጥቂት ከማሸለቡ ውጪ ሌሊቱን ምንም እንቅልፍ ሳያገኝ ነበር ከጌርጌሴኖን ወደ ቅፍርናሆም የተመለሰው:: እንደሚመጣ በመጠበቅ ሕዝቡ በባሕሩ ዳር ተሰብስቦ ነበር:: ደክሞት ቢዝልም የሚያርፍበት ሁኔታ አልነበረም::

---

[149] ዲካፖሊስ ስሙ እንደሚያመለክተው በመጀመሪያ የዐሥር ከተሞች ስብስብ ነበር:: በኋላ ግን ሌሎች ከተሞችም ተጨምረዋል:: ከሦርያ ጋር የተያያዘ ቢሆንም፣ ወደ ሮም ባለ ሥልጣኖች ይግባኝ ማለት የሚያስችለው የራሱ አስተዳደር ነበረው:: የግሪክ ባሕልና የአስተሳሰብ ቅኝት እንደነበረው ግልፅ ነው:: ይሁን እንጂ ብዙ ጊዜ ሲባል እንደነበረው ራስ ገዝ ፌደራላዊ ሥርዓት ነበር ለማለት አሳማኝ መረጃ የለንም:: S.T. Parker, "The Decapolis Reviewed," *JBL* 94 (1975): 437-441 ጋር ያነ::



አጋንንት በነበሩበት ሰው፣ ደም ይፈሳት በነበረችው በኢያኢሮስ ልጅ ፈውስ ተመሳሳይ የሚያደርጋቸው አንድ የጋራ ጉዳይ ነበር:: ይኸውም፣ ከሃይማኖት ሥርዐት፣ አንጻር ሁሉም እንደ ርኩስ መቈጠራቸው ነበር:: አጋንንት፣ የሴት የወር አበባና ሞት አንድን ሰው ርኩስ ከማድረጋቸው ባሻገር እነርሱ የሚነኳቸው ሁሉ እንደ ርኩስ ይቈጠሩ ነበር:: ከአይሁድ ሃይማኖት መምህራን መካከል እንደነዚህ ያሉትን ሰዎች የዳሰሳና ንጹሕ እንዲሆኑ ያደረጋቸው ኢየሱስ ብቻ ነው::

**ማር 5÷21-24**
**ሉቃ 8÷40-42፤**
**ማር 9÷18**

21ኢየሱስ እንደ ገና በጀልባ ወደ ማዶ በተሻገረ
ጊዜ፣ [መምጣቱን ይጠባበቁ ስለ ነበር[ሉቃ]] ብዙ ሕዝብ
በዙሪያው ተሰባሰበ፤ በባሕሩ ዳርቻም እንዳለ 22ከምኲራብ
አለቆች አንዱ ኢያኢሮስ የተባለው ወደዚያ መጥቶ ስለ
ነበር፣ ኢየሱስን ባየው ጊዜ በእግሩ ላይ ወድቆ፣ 23ትንሿ ልጄ በሞት አፋፍ ላይ ናትና
ድና በሕይወት እንድትኖር መጥተህ እጅህን ጫንባት በማለት [ወደ ቤቱ
እንዲሄድለት[ሉቃ]] አጥብቆ ለመነው:: 24ኢየሱስም አብሮት ሄደ::

ይህች ልጅ የኢያኢሮስ ብቸኛ ሴት ልጅ (*monogenes*, ሉቃ 8÷42) ብቻ ሳትሆን አንድያ ልጅ ነበረች (ሉቃ 7÷12፤ ዮሐ 3÷16 ጋር ያነጻጽሩ):: ዐሥራ ሁለት ዓመት ይሆናት ነበር:: ይህ ዕድሜ አይሁዳዊት ልጃገረድ ሙሉ ሴት ወደ መሆን ደረጃ የምትሸጋገርበት ነበር:: ስለሆነም ላለፉት ዐሥራ ሁለት ዓመታት እነዚህ ባልና ሚስት ሌላ ልጅ መውለድ አልቻሉም ነበር:: ብዙ ልጆች ለመውለድ የነበራቸው ዕድል የመነመነ ነበር:: ስለ ልጅቱ እየተነጋገሩ ሳሉ እንኳ የሥጋ ልጃቸው ሕይወት ከእጃቸው እያመለጠ ነበር::[150]

---

[150] የሚከተሉትን ነጥቦች ስንገነዘብ ልጅቱ መሞት አለመሞቷን በተመለከተ የሚነሳ መሳይ ቅራኔ ሁሉ መልስ ያገኛል፤ (ሀ) የመጀመሪያው መቶኛ ዓመት ሕክምና አንድ ሰው መሞት አለመሞቱን በትክክል የሚያውቅበት የቴክኖሎጂ

የምኵራብ አለቃ እንደ መሆኑ ኢያኢሮስ በማኅበረ ሰቡ የተከበረ ሰው ነበር:: ያልተካነ ሰው ከመሆኑ አንጻር የምኵራብን አገልግሎትና ሌሎች ጉዳዮችን ማስፈጸም የእርሱ ሥራ ነበር:: በኢየሱስ ላይ ተቃውሞ በበዛበት ሰሞን ኢያኢሮስ ርዳታ ፍለጋ ወደ እርሱ መምጣቱ በነበረው ሥልጣን ችግር ሊያመጣበት ይችላል:: ይሁን እንጂ የሁኔታው አጣዳፊነት የኢየሱስን ርዳታ እንዲፈልግ አድርጎታል:: ኢየሱስ ወደ ቅፍርናሆም የመጣው ከአንድ ቀን በፊት በመሆኑ፣ የዚህች ልጅ ሕመም ሌሊቱን ሳይባባስ እንዳልቀረ ማሰብ እንችላለን:: በእንዲህ ያለ ጭንቅ ውስጥ በነበረ ጊዜ ኢያኢሮስ በኢየሱስ እግር ሥር በመውደቅ (ክብር መስጠትንና አምልኮን ለመግለጽ የሚደረግ) ራሱን ዝቅ አደረገ:: ኢየሱስ ወዲያውኑ ልመናውን ተቀብሎ እየተጣደፈ የነበረውን አጀብ ይዞ ወደ ኢያኢሮስ ቤት መሄድ ጀመረ::

> ብዙ ሕዝብም ዙሪያውን እያጨናነቀው
> [ያጨናንቀው[ሰቃ]] ተከተለው:: 25 ዐሥራ ሁለት ዓመት ደም
> ሲፈሳት የኖረችም ሴት በዚያ ነበረች፤ 26 በብዙ ባለ
> መድኀኒቶች ዘንድ በመንከራተት ያላትን ሁሉ ብትጨርስም፣
> ሕመሙ ባሰባት እንጂ አልተሻላትም ነበር:: 27 ስለ ኢየሱስ በሰማች ጊዜ፣ ከበስተኋላው
> በሰዎች መካከል መጥታ ልብሱን [የልብሱን ጫፍ[ማቴ]] ነካች፤ 28 ምክንያቱም፣ «እንደ
> ምንም ብዬ ልብሱን ብቻ እንኳ ብነካ እፈወሳለሁ»የሚል እምነት ነበራት:: 29 የሚፈሰው
> ደሟ ወዲያውኑ ቆመ፤ ከሥቃይዋ መገላገሏንም በሰውነቷ ታወቃት::

ማር 5፥24-29፤
ሉቃ 8፥42፤
ማቴ 9፥20 ጋር

ሕዝቡ ኢየሱስን «እያጨናነቁ» ነበር:: እንክርዳዱ ጥሩውን ዘር አንቆ መያዙን በሚያመለክተው ምሳሌ የተጠቀሰው ይሄው ቃል ነበር:: እንዲህ ያለውን መጨናነቅን የሚሳዩ ሌሎች ሁለት ቃላት አሉ፤

እውቀት አልነበረውም፤ (ለ) ማቴዎስ የተጠቀመበት (*arti eteleutesen*) የሚለው ቃል፣ «ሞት አፋፍ ላይ ነበረች» ተብሎ ሊተረጐምም ይችላል:: ስለሆነም ወደ ሞት ተቃርባ ነበር እንጂ ገና አልሞተችም ነበር ማለት ነው::



[*synechousin*] «መጋፋት» እና [*apothlibousin*]፣ «መጨናነቅ» የተሰኙት ሲሆኑ ሁለቱም ሉቃስ 8፥45 ውስጥ ተጠቅሰዋል:: ሕዝቡ በፍጹም ጨዋነት የጐደለው ነው:: ይህች ሴትና ኢያኢሮስ ወደ ኢየሱስ ለመምጣት ምን ያህል ብርቱዎችና የመጋፋት ብቃት እንደነበራቸው ማሰብ ይቻላል:: የነበረባቸው ችግር ወደ ፊት እንዲገሠግሡ አስችሎአቸዋል::

ሕዝቡ በብዙ አጀብ ወደ ኢያኢሮስ ቤት እያመራ ነበር:: የዚህችን ልጅ ሕይወት ለማዳን ቶሎ መድረስ ያስፈልግ ነበር:: ይሁን እንጂ ስሟ ማን እንደሆነ ባልታወቀ ከዚህች ሴት የተነሣ ጉዞው በድንገት ቆመ:: ዐሥራ ሁለት ዓመት ሙሉ ደም ይፈሳት ነበር::[151] ምንም እንኳ ደም እንዲፈሳት ያደረጋት ሕመሟ ባይጠቀስም፣ ከማሕፀን ጋር የተያያዘ ችግር ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል:: እንዲህ ያለው ሕመም በብዛት የሚገኝ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል:: ኤደርሼይም ይህን መሳይ ክስተት የተለመደ እንደነበረ ሲያመለክት:-

> በአንድ የታልሙድ ገጽ ላይ ከዐሥራ አንድ ያላነሱ ፈውስ ሰጪ ነገሮች የሰፈሩ ሲሆን፣ ከእነዚህ ስድስቱ እንደ ኀይል ወይም ብርታት ሰጪ ሊወሰዱ የሚችሉ ናቸው፤ የተቀሩት ግን የዕውቀት ማጣት ውጤት የሆኑ ከንቱ እምነቶች ናቸው:: በበጋ ወቅት የሰጉን እንቁላል ዐመድ በናይለን ጨርቅ መያዝ፣ በክረምት በጥጥ ጨርቅ ቀዳጅ መያዝ፣ ወይም ደግሞ በነጭ ሴት አህያ ፋንድያ ውስጥ የገብስ ፍሬ ዛላ እንደ ማግኘት የመሳሰሉ ከንቱ ነገሮች ማለት ነው (I:620)::

[151] ሴትዮዋ የታመመችበት ዘመንና የኢያኢሮስ ልጅ ዕድሜ ተመሳሳይ የሆነው ምናልባት በአጋጣሚ ሊሆን ይችላል:: ምንም እንኳ፣ «ዐሥራ ሁለት ዓመት» የሚለው ቃል ከሁለቱ ሴቶች ጋር የተያያዘ ቢሆንም ይህን መነሻ በማድረግ ምሳሌያዊ ትርጉም መስጠት መሞከር ነገሩን እንደ መለጠጥ ነው::

በዘሌዋውያን 15፥25-33 ባለው የሙሴ ሕግ እንዲሁም በአይሁድ ባሕል የዚህችን ሴት ማኅበረ ሰባዊ እንቅስቃሴ የሚገቱ ከበድ ያሉ ጫናዎች ሳያስቀምጡ አይቀሩም ነበር:: ከቤተ መቅደስ አምልኮ፣ ከሕዝባዊ ስብሰባዎች ትገለል ነበር፤ እርሷ የነካችው ሁሉ በእሷ ሰበብ ርኩስ እንደሚሆን ይቈጠር ነበር (ዘኍ 19፥22):: ችግሩ የጤና ብቻ ሳይሆን፣ ማኅበራዊም ችግር ነበር::

በጣም ግልጽ በሆኑ የራሱ ምክንያቶች ባለ መድኃኒቱ ሉቃስ ችላ ያላቸውን መረጃዎች ማርቆስ ያቀርብልናል:- «በብዙ ባለ መድኃኒቶች ዘንድ በመንከራተት ያላትን ሁሉ ብትጨርስም፣ ሕመሙ ባሰባት እንጂ አልተሻላትም ነበር» (ማር 5፥26)::

ይህች ሴት የወሰደችው እርምጃ የፈዋሽ ሰው ኀይል ወደ ልብሱ ሊተላለፍ ይችላል በሚለው የግሪክ ተረታዊ እምነት ላይ የተመሠረተ ሊሆን ይችላል:: ያም ሆኖ ውጤት አግኝታበታለች! ኢየሱስ እምነቷን አክብሮአል፤ ሆን ብላ የልብሱን ዘርፍ በመንካቷ ብቻ ተፈውሳለች:: የነካችው የጸሎት መጐናጸፊያውን ዘርፍ ወይም ጥለት ሊሆን ይችላል (ዘኍ 15፥38-39፤ ዘዳ 22፥12):: ይህ ደግሞ ያልተለመደ የፈውስ ተአምር ነበር:: ሆኖም እንዲህ ያለ ነገር ሲደረግ ይህ የመጨረሻው አይሆንም (ከሐሥ 5፥15 እንደምንመለከተው በጴጥሮስ ጥላ፣ [ከሐሥ 19፥11-12 እንደምንመለከተው በጳውሎስ መሐረብ]):: ምንም እንኳ በዘመኑ የነበረውን አጉል እምነት ብትከተልም እግዚአብሔር እምነቷን አክብሯል::

ማር 5፥30-31
ሉቃ 8፥45 ጋር

[30]ወዲያውኑ ኢየሱስ፣ ኀይል ከእርሱ እንደ ወጣ ዐውቆ፣ ወደ ሕዝቡ ዘወር በማለት፣ «ልብሴን የነካው ማን ነው?» አለ:: [ሁሉም መንካታቸውን በካዱ ጊዜ ጴጥሮስ፣ ጌታ ሆይ[ሉቃ]] [31]«ሕዝቡ ተጨናንቆ ሲጋፋህ እያየህ፣ «ማን ነው የነካኝ እንዴት ትላለህ?» አሉት::

ሉቃ 8፥46

[46]ኢየሱስ ግን፣ «አንድ ሰው ነክቶኛል ኀይል ከእኔ እንደ ወጣ ዐውቃለሁና» አለ::

ማር 5፥32-34
ሉቃ 8፥47፤ማቴ 9፥22 ጋር

[32]ኢየሱስ ግን ይህንን ያደረገው ማን እንደ ሆነ ለማየት ዙሪያውን ተመለከተ:: [33]ሴትዮዋም [ሳትታወቅ መሄድ እንዳልቻለች በተረዳች ጊዜ[ሉቃ]] ምን እንደ ተደረገላት ባወቀች ጊዜ እየፈራችና እየተንቀጠቀጠች መጥታ በፊቱ ተደፋች፤ እውነቱንም ሁሉ ነገረችው:: [ለምን እንደ ነካችውና እንዴት ወዲያውኑ እንደ ተፈወሰች በሕዝቡ ሁሉ ፊት ተናገረች[ሉቃ]] [34]እርሱም፣ [አይዞሽ[ማቴ]] ልጄ ሆይ፣ እምነትሽ አድኖሻል፤ በሰላም ሂጂ፤ ከሥቃይሽም ዕረፊ» አላት::

ኢየሱስ ኀይል ከእርሱ እንደ ወጣ ዐውቋል:: ስለዚህ ልብሱን የነካው ማን እንደ ሆነ ጠየቀ:: ከጥቂት ጊዜ በፊት ሁሉም ከእርሱ ጋር ሲጋፋ አልነበሩ ይመስል እርሱን መንካታቸውን መካዳቸው የሚገርም ነው! ጴጥሮስ እንደሚረዳው ግን ጥያቄው ምክንያታዊ አልነበረም:: በዚያ ጭንቅንቅ ውስጥ እያለ አንድ ሰው ልብሱን እንደ ነካው ኢየሱስ እንዴት ሊታወቀው ይችላል?

የነካው ማን መሆኑን ኢየሱስ በእርግጥ ላያውቅ ይችል ነበር? ካላወቀ ይህች ሴት ከእርሱ «ፈውስን እንዴት መዝዛ ማውጣት ቻለች»? ሁለት በቂ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ:: በመጀመሪያ፣ ሴትዮዋ ስትነካው ኢየሱስ ስለ እምነቷ ዐውቋል:: ስለዚህም ፈወሳት:: አሁን ግን ለሕዝቡ ሁሉ እንድትታወቅ በማድረግ ጭል ጭል ይል የነበረ እምነቷን ቦግ ብሎ እንዲበራ ፈልጓል:: ሊሆን እንደሚችል የሚገመተው ምክንያት ሁለተኛው ደግሞ፣ ኢየሱስ ይህች ሴት ማን መሆኗን ባያውቅም፣ እግዚአብሔር አባቱ ግን ያውቅ ነበር የሚል ነው:: እግዚአብሔር እየሆነ ያለውን ነገር በማወቁ ኀይሉ በልጁ በኩል አልፎ ወደዚህች ሴት ሰውነት እንዲገባ ፈቀደ:: ኢየሱስ የሰዎችን ልብ ዘልቆ በማየት ችሎታው

አማካይነት ምንም እንኳ የዚያች ሴት አጉል አስተሳሰብ ስሕተት ቢሆንም እምነቷ ግን ትክክል እንደ ነበር ለሕዝቡ ማሳየት ይችል ዘንድ በአጀቡ መካከል እሷን ፈለገ::

ሴትዬዋ ሳትታወቅ ማለፍ አልቻለችም::[152] ምናልባትም ይህ ኢየሱስ ማን እንደ ሆነች ሳያውቅ እንዳልቀረ የሚያመለክት ሊሆን ይችላል:: ምናልባትም ዐይኖቿዋን ትኩር ብሎ ተመልክቶም ሊሆን ይችላል:: ምናልባትም ያጋለጣት መፍራትና መንቀጥቀጧ ሊሆን ይችላል::

ይህ ደግሞ ባልፈለገችው ሁኔታ በሁሉም ፊት ይፋ ምስክርነት እንድትሰጥ አድርጓል:: ለነገሩ ከወር አበባ ጋር ስለ ተያያዘ ፈሳሽ ችግር በግልጽ ለሰዎች የሚነግሩት ጉዳይ አልነበረም:: ኢየሱስም ችግሯን እንድትገልጽ በማድረግ ሊያሳፍራት እየሞከረ አልነበረም:: ይሁን እንጂ የሕዝቡን ተወት አድርገን የእርሷ እምነት እንዲያድግ ከተፈለገ የተደረገላትን በግልጽ መናገር ነበረባት::

የኢየሱስ የርኅራኄ ቃላት እርሱን በመንካቷ ያደረባትን ፍርሃት ብቻ ሳይሆን ከእንግዲህ ወዲህ ሕዝቡ በችግሯ ላይ የነበረውን መጸየፍ ጨርሶ እንዲወገድ አድርጓል:: ሙሉ በሙለ በመፈወሷ፣ ሙሉ በሙሉ የማኅበረ ሰቡ አባል ሆኖ መደባለቅ ትችላለች::

ኢየሱስ «ልጄ» በማለት ሲናገር የምናየው እዚህ ላይ ብቻ ነው:: በተጨማሪም፣ «በሰላም ሂጂ» ሲል የተጠቀመው፣ «ሻሎም» የተሰኘውን የዕብራይስጥ ቃል የሚያስተጋባ ነበር:: ይህ ቃል ከሰላምታ ወይም ለአንድ ሰው አካላዊ ጤንነት በጐውን ከመመኘት ያለፈ ነበር:: በእግዚአብሔርም ሆነ በሰው ፊት አንድ ሰው በሙላት ይሆን ዘንድ

---

[152] ሉቃ 8÷47ን አዲሱ መደበኛ ትርጒም፣ «ሳትታወቅ መሄድ እንዳልቻለች» በማለት በአሁን ጊዜ ነው ያስቀመጠው:: ይሁን እንጂ የሚናገረው ስለ ኀላፊ ጊዜ በመሆኑ፣ «ሳትታወቅ መሄድ አልቻለችም» ተብሎ ነው መነበብ ያለበት::



መጸለይን ያመለክታል:: በዐሥራ ሁለት ዓመት ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲህ ያለ ሰላምታ ቀረበላት::

ማር 5÷35-40
ሉቃ 8÷49-53
ጋር

35ኢየሱስም በመነጋገር ላይ እያለ፣ ሰዎች
ከምኵራብ አለቃ ከኢያኢሮስ ቤት መጥተው፣ «ልጅህ
ሞታለች፤ ከእንግዲህ መምህሩን ለምን ታደክመዋለህ?
[ስታድክመው[ሉቃ]] አሉት::
36ኢየሱስ ግን ሰዎቹ የተናገሩትን ችላ በማለት የምኵራቡን አለቃ፣ እመን
ብቻ እንጂ አትፍራ» [ልጅህ ትድናለች[ሉቃ]] አለው::
37ከጴጥሮስና ከያዕቆብ እንዲሁም ከያዕቆብ ወንድም ከዮሐንስ [እንዲሁም
ከልጅቱ አባትና እናት] በቀር ማንም እንዲከተለው አልፈቀደም:: 38ወደ ምኵራቡ
አለቃ ቤት እንደ ደረሱ፣ ኢየሱስ ግርግሩንና ሰዎቹም ዋይ ዋይ እያሉ አምርረው
ሲያለቅሱ [እምቢልተኞችንም[ማቴ]] ተመለከተ:: 39ወደ ቤትም ገብቶ፣ ይህ ሁሉ ግርግርና
ልቅሶ ምንድን ነው? [አልታልቅሱ[ሉቃ]] [ዞር በሉ[ማቴ]] ብላቴናዪቱ ተኝታለች እንጂ
አልሞተችም አላቸው:: 40ሰዎቹ ግን [መሞቷን ስላወቁ[ሉቃ]] ሳቁበት::

መንገድ ላይ በመዘግየታቸው ኢያኢሮስ ጥቂት ሳይቅበጠበጥ እንዳልቀረ አይጠረጠርም:: የልጁን መሞት ዜና ሲነግሩት ደግሞ ብስጭቱ ሊባባስ እንደሚችል ግልጽ ነው:: የግሪኩ ቅጂ አጽንዖት ለመስጠት፣ «ሞት» የሚለውን ቃል በዐረፍተ ነገሩ መጀመሪያ ላይ አስቀምጦታል:: ስለሆነም የተጻፈው ሲነበብ «ልጅህ ሞታለች» የሚል ነው::

አገልጋዮቹ ከኢያኢሮስና ከኢየሱስም ጋር ሀሳብ ገብቷቸዋል:: ያለ አግባብ እንዲጨነቅ አልፈለጉም:: ኢየሱስ ግን ሀሳባቸውን አልተቀበለም:: በፍጥነት የኢያኢሮስን ትኩረት በመሳብ ከፍርሃት ይልቅ በእምነት ላይ እንዲያተኵር አደረገ::

ማርቆስ እንደሚያቀርበው ከሆነ ኢየሱስ ሕዝቡ በነበረበት ቦታ እንዲቆምና ወደ ኢያኢሮስ ቤት እንዲመጣ ያልፈቀደ ይመስላል:: ሉቃስም ቢሆን ከልጅቱ አባትና እናት ጋር ሦስት ደቀ መዛሙርት (ጴጥሮስ፣ ያዕቆብና ዮሐንስ) ብቻ ወደ ቤት እንዲገቡ ኢየሱስ መፍቀዱን የተናገረው ሉቃስ ምናልባት ጉዳዩን ይበልጥ ግልጽ በሆነ መንገድ አቅርቦት ሊሆን ይችላል:: ኢየሱስ በመለወጥ ተራራ በነበረ ጊዜ (ማቴ 17÷1፤ ማር 9÷2፤ ሉቃ 9÷28) ሁኔታውን የማየት፣ ወደ ጌቴሰማኒ አትክትል ቦታ እርሱን ተከትለው የመሄድ የተለየ ዕድል የተሰጣቸው ለእነዚህ ቀረቤታ ለነበራቸው ሦስት ደቀ መዛሙርት ነበር (ማቴ 26÷37፤ ማር 14÷33)::

ከቤቱ ውጪ ጫኸትና ግርግር ነበር:: በአይሁድ የቀበር ሥርዐት ሕዝቡ በአንድነት ተሰብስበው መንጫጫታቸው የተለመደ ነበር:: በጣም ድሆች የሆኑ ቤተ ሰቦች እንኳ ቢያንስ ሁለት እንቢልተኞችና አንድ አልቃሽ ማቆም ነበረባቸው (*m. Ketub* 4:4):: «ልቅሶ» ሲባል ሀዘንን ለማሳየት ደረት መምታትን ይጨምራል:: ለቀስተኞቹ ተሰብስበው ስለ ነበር ኢየሱስና ኢያኢሮስ እዚያ ለመድረስ ረዘም ያለ ጊዜ ሳይወስድባቸው እንዳልቀረ ግልጽ ነው::

ልጅቱ ተኝታለች እንጂ አልሞተችም በማለት ኢየሱስ ሕዝቡ ማልቀሱን እንዲያቆም ተናገረ:: አልዓዛርንም ከሞት ሲያስነሣ ይህንኑ ዘይቤያዊ ቋንቋ ነበር የተጠቀመው (ዮሐ 11÷11ን፣ ከማቴ 27÷52፤ ሐሥ 13÷36፤ 1ቆሮ 11÷30፤ 15÷20:51፤ 1ተሰ 4÷14 ጋር ያነጻጽሩ):: ሕዝቡ አባባሉን ቃል በቃል በመውሰድ ሳቁበት:: የሞተ ሰው በሚገባ ያውቃሉ:: ይህን ያህል ሞኞች አይደሉም፤ ኢየሱስ ግን ሞኝ ሳይሆን እንዳልቀረ አስበዋል:: «ልብሴን የነካው ማን ነው?» በማለት ኢየሱስ በጠየቀ ጊዜ ጴጥሮስ ተመሳሳይ ዓይነት ስሕተት ፈጽሞአል::



**ማር 5÷40-43**
**ሉቃ 8÷54-56**

ሰዎቹን ሁሉ ከቤት ካስወጣ በኋላ፣ የብላቴናዪቱን
አባትና እናት እንዲሁም አብረውት የመጡትን ደቀ
መዛሙርት አስከትሎ ብላቴናዪቱ ወዳለችበት ገባ::
[41]ከዚያም የብላቴናዪቱን እጅ ይዞ፣ «ጣሊታ ቁሚ!» አላት፤ ትርጉሙም፣ «አንቺ ልጅ
ተነሺ» ማለት ነው:: [42]ብላቴናዪቱም ወዲያውኑ ተነሥታ ቆመች፤ [የልጅቷም መንፈስ
ተመለሰ[ሉቃ]] ወዲያ ወዲህም ሄደች:: ዕድሜዋም ዐሥራ ሁለት ዓመት ነበር:: ሰዎቹም
[ወላጆቿም[ሉቃ]] በሁኔታው እጅግ ተደነቁ:: [43]እርሱም ይህ ነገር ማን እንዳያውቅ
አጥብቆ አስጠነቀቃቸው፤ የሚበላ ነገር እንዲሰጧትም ነገራቸው::

**ማቴ 9÷26**

[26]ወሬውም በአካባቢው ሁሉ ተሰራጨ::

ኢየሱስ ይህችን ትንሽ ልጅ ከሞት ሲያስነሣት ሙሉ በሙሉ ጤነኛ ሆነች:: «መንቃት» ብቻ ሳይሆን፣ ተነሥታ ወዲያና ወዲህ ተመላለሰች:: ኢየሱስም የሚበላ ነገር እንዲሰጧት ለወላጆቿ ነገራቸው::

ስለ ተደረገው ተአምር ለማንም እንዳይናገሩ ኢየሱስ ወላጆቿን ማዘዙ ሌላው አስገራሚ ነገር ነው:: ኢየሱስ ምክንያታዊ ያልሆነ ነገር ተናግሮአል ከተባለ፣ ያ ንግግር ይህ መሆን አለበት! ቀደም ሲል ሕዝቡ መሞቷን ዐውቀዋል:: ከሞት ከተነሣች በኋላ ይህን ደብቆ መያዝ በፍጹም የማይሆን ነበር:: ምናልባት ኢየሱስ እየተናገረ ያለው ልጅቱን ከሞት ያስነሣበትን ዝርዝር ሁኔታ ለማንም እንዳይናገሩ ነበር ማለት ይቻላል:: በሌላ አነጋገር ኢየሱስ እንዴት ከሞት እንዳስነሣት አትናገሩ ማለት ነው:: ለምን እንደሆነ ይገባናል:: ሕዝቡ ቀደም ሲልም እያጉረመረሙ ነበር:: የዚያ አገር ሕዝብ እምነት እንዲያድግ በጌርሴኖን አጋንንት ለወጡለት ሰው የሆነለትን ሁሉ እንዲናገር አዞት ነበር:: በዚህ ቦታ ግን የሕዝብ እምነት አድናቆትና ግርግሩ ፈንቅሎ ወጥቷል:: በዚህ ቦታ ኢየሱስ ምንም ዓይነት ማስተዋወቂያ አያስፈልገውም! እንዲያውም ከሚቀጥለው ምዕራፍ (ሉቃ 9÷7-9) እንደምንመለከተው እንደ ተአምር

አድራጊ የኢየሱስ ዝና በጣም እየሰፋ በመሄዱ ይፋ በሆነ መንገድ በሄሮድስ ወደ መጠየቅ አድርሶት ነበር። ይህ ሁሉ ጊዜው ከመድረሱ በፊት ስለ ማንነቱ ማስተዋወቅንና ስለ መሲሒነቱ ያልተሟላ ግንዛቤን ሊያስከትል ይችላል። ልጅቱ ተኝታ እንደ ነበር ለሕዝቡ ቀደም ብሎ ተነግሮ ነበር። ስለሆነም ይህን ከሰመመን እንደ መንቃት ሊያስቡት ይችላሉ። ይህንንም ቢሆን እንደ አንድ አስደናቂ ተአምር ሊመለከቱት ቢችሉም፣ ከሞት የማስነሣትን ያህል አስገራሚ ላይሆን ይችላል። ምንም እንኳ ኢየሱስ ይህን ታምራት ተዳፍኖ እንዲቀር ለማድረግ ቢሞክርም፣ ወሬው እንደ ሰደድ እሳት ይሰፋፋ ጀመር።[153]

ይህ ኢየሱስ ከሞት ካስነሣቸው ሦስት ሰዎች ይህ ሁለተኛው ነው። የመጀመሪያው በናይን የነበረው የመበለትዋ ልጅ ነበር (ሉቃ 7÷11)። ሦስተኛው ደግሞ የኢየሱስ ወዳጅ የነበረው የቢታንያው አልዓዛር ይሆናል (ዮሐ 11)። እንደ ብሉይ ኪዳን አቻዎቹ እንደ ኤልያስና እንደ ኤልሳዕ ሁሉ (1ነገ 17÷20-24፤ 2ነገ 4÷17-37 ጋር ያነ) ሙታንን እንኳ የሚያስነሣ የእግዚአብሔር ኃይል በኢየሱስ ውስጥ እያለፈ ነበር።

**§ 68**
**የዐይነ ስውሮቹና ጋኔን የነበረበት ሰው መፈወስ**
**(ማቴ 9÷27-34)**

የሁለቱ ዕውሮችና ጋኔን የነበረበት ዲዳ ሰው ፈውስ ተመሳሳይ ሲሆኑ ሌሎች ሁኔታዎች በቀጣዩ የኢየሱስ ሕይወት በኋላ ይደገማሉ። ለምሳሌ ያህል በማቴዎስ 20÷29-34 በኢያሪኮ፣ «የዳዊት ልጅ ሆይ ማረን» በማለት ይጮኹ ስለ ነበሩ ሁለት ዕውሮች እናነባለን። አንዳንዶች ይህ

[153] የሚከተሉት ኢየሱስ ተአምራት እንዳደረገ ለማንም እንደይናገሩ እንዳዘዘ የሚያመለክቱ ተጨማሪ ጥቅሶች ናቸው፤ ማቴ 8÷4 (ማር 1÷44፤ ሉቃ 5÷14)፣ ማቴ 9÷30፤ 12÷16፤ ማር 3÷12፤ 5÷43 (ሉቃ 8÷56)፤ ማር 7÷36፤ 8÷26።



ማቴዎስ አጽንዖት ለመስጠት ሲል በድጋሚ ያቀረበው አንድ ዓይነት ሁኔታ እንደሆነ ይናገራሉ። ይሁን እንጂ ይበልጥ ተቀባይነት ያለው አቀራረብ ማቴዎስ የጻፈው ስለ ስለ ሁለት ተመሳሳይ ሆኖም የተለያዩ ሁኔታዎች ነበር የሚለው ነው። በሁለት የተለያዩ ቦታዎችና (ቅፍርናሆምና ኢያሪኮ)፣ በሁለት የተለያዩ የኢየሱስ አገልግሎት ወቅቶች ነበር የተፈጸሙት። በተጨማሪም ማቴዎስ 9 ላይ ያለው የተፈጸመው ቤት ውስጥ ሲሆን፣ ማቴዎስ 20 ላይ ያለው ግን ኢየሱስ በከተማ ውስጥ እያለፈ እያለ መንገድ ዳር ነበር የተፈጸመው። በመጀመሪያ ላይ ሁለቱ ሰዎች ኢየሱስን ተከትለው የነበረ ሲሆን፣ በሁለተኛው ግን መንገድ ዳር ተቀምጠው ነበር። ትረካዎቹ የተጠቀሙባቸውም ቃላት ሆነ የሁለቱ ውይይቶች ዓላማ በጣም የተለያየ ነበር። ዐይነ ዕውርነት በፓለስቲና በጣም የተለመደ ስለ ነበር ስለ ዕውራን መፈወስ ሁለት የተለያዩ ታሪኮች ብናነብ የሚገርም አይደለም።

በተመሳሳይ ጊዜ የተፈጸሙ ይመስል ማቴዎስ ይህን ሁኔታ ከኢያኢሮስ ልጅ መነሣት ጋር አያይዞታል። ይሁን እንጂ፣ በሌላ ቦታ እንደምናየው ማቴዎስ በተመሳሳይ ጭብጥ የተፈጸሙ በመጠኑ የተያዙ ታሪኮችን አንድ ላይ ያቀርባቸዋል። ስለሆነም እነዚህ ሁኔታዎች የግድ በአንድ ቀን ውስጥ የተፈጸሙ ባይሆኑም በኢየሱስ አገልግሎት በተመሳሳይ ወቅት ላይ የተፈጸሙ ናቸው። በበርካታ መንገዶች ቀደም ካለው ትረካ ጋር ይያያዛሉ። (1) ሁለቱም እምነትን መሠረት ያደረገ ፈውስን ያመለክታሉ (ለምሳሌ፣ ደም ይፈሳት የነበረችው ሴት)። (2) በሁለቱም ጊዜ ለማንም እንዳይናገሩ ታዘው ነገር። (3) ሁለቱም የኢየሱስን ርዳታ ፈልገው ስለ መጡ ግለ ሰቦች ያመለክታሉ። (4) ሁለቱም የኢየሱስ ዝና እየሰፋ መሄዱን ይናገራሉ።

በእነዚህ ሦስት ፈውሶች ማቴዎስ በምዕራፍ 8-9 ያሰባሰባቸውን የፈውስ ታኮች ይደመድማሉ። በጣም አጭርና አንዳንዴም ድግግሞሽ ያላቸው ይመስላል። ያም ሆነ ይህ እነዚህ ፈውሶች በአጠቃላይ

ተከታታይ የፈውሶች የኢየሱስን ዝና እየሰፋ መምጣት፣ የዝናው እየየሰፋ መሄድ ያስከተለውን ችግር፣ በኢየሱስና በዘመኑ በነበሩ የሃይማኖት መሪዎች መካከል እየተካረረ የመጣውን ችግር (ቊ 34) ጣልቃ በማስገባት ይቀርባሉ::

ማቴ 9፥27-31

[27]ኢየሱስም ከዚያ እንደ ሄደ ሁለት ዕውራን «የዳዊት ልጅ ሆይ፣ ማረን» በማለት እየጮኹ ተከተሉት::

[28]ዕውራን ስውሮቹም ኢየሱስ ወደ ገባበት ቤት ተከትለው ገቡ፣ ኢየሱስም፣ «ዐይናችሁን ሳበሩላችሁ እንደምችል ታምናላችሁን» ሲል ጠየቃቸው::

እነርሱም፣ «አዎን፣ ጌታ ሆይ» ብለው መለሱለት:: [29]ከዚያም ኢየሱስ ዐይናቸውን ዳሰሰ፣ «እንደ እምነታችሁ ይሁንላችሁ» አላቸው:: [30]ዐይናቸውም በሩ፤ ኢየሱስ፣ «ይህን ማንም እንዳያውቅ» ብሎ በጥብቅ አስጠነቀቃቸው:: [31]እነርሱ ግን ወጥተው በአካባቢው ሁሉ ስለ ኢየሱስ አወሩ::

የሕዝቡን ግፊያና ውካታ ግምት ውስጥ በማስገባት (ማር 5፥24)፣ በዚህ ላይ ደግሞ እነዚህ ሰዎች ዐይነ ስውራን መሆናቸውን በማገናዘብ ኢየሱስን እስከ ቤት (ምናልባት የጴጥሮስ ወይም የማቴዎስ ቤት) ድረስ መከተላቸው እንዲያውም ተከትለውት ቤት ውስጥ መግባታቸው የዓላማ ጽናት እንደ ነበራቸው ያመለክታል:: ጉዞውን አቋርጦ እስከሚቆም ድረስ ተከትለውታል:: በዚህ መሓል ደግሞ፣ «የዳዊት ልጅ ሆይ ማረን» በማለት ከሕዝቡ ጫጫታ በላይ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ይጮኹ ነበር:: ኢየሱስ ባገለገለበት ዘመን ይህ የተለመደ መሲሐዊ መጠሪያ ነበር (ማቴ 15፥22፤ 20፥30፤ 21፥9:15፤ 22፥42)[154]

[154] «የዳዊት ልጅ» የሚለውን መጠሪያ ማቴዎስ ዐሥር ጊዜ፣ ማርቆስና ሉቃስ እያንዳንዳቸው አራት ጊዜ ሲጠቀሙበት ዮሐንስ ግን ጨርሶ አልተጠቀመበትም:: በተጨማሪም ማቴዎስ አብዛኛውን ጊዜ ይህንን መጠሪያ የጠቀሰው ከኅብረተሰቡ የተገለሉትን ከመፈወሱ ሁኔታ ጋር በተያያዘ ነው:: J.D. Kingsbury, "The Title 'Son of David' in Matthew's Gospel," *JBL* 95/4



ሥጋዊ ብርሃን አጥተው ይሆናል፤ ሆኖም ኢየሱስ ማን መሆኑን ግን በግልጽ ማየት ችለው ነበር:: መሲሑ ዕውራንን እንደሚፈውስ ኢሳይያስ 35፥5-6 ያለው በያዙት ተስፋ እንዲጸኑ ያደርጋቸዋል::

ኢየሱስ እምነታቸውንና የዓላማ ጽናታቸውን በማክበር ሊፈውሳቸው ቢፈልግም ከእንግዲህ በሕዝቡ ዘንድ ታዋቂ መሆንን አልፈለገም:: ተከትሎት የነበረውን ሕዝብ ትኵረት መሳብ በማይችልበት ሁኔታ ገለልተኛ ሁኔታ በቤት ውስጥ እነዚህን ሰዎች የመፈወስ ዕድል አግኝቷል:: አሁንም ቢሆን ለማንም እንዳያወሩ ነግሮቸአው ነበር:: ማቴዎስ የተጠቀመው ጠንከር ያለ፣ ሆኖም ቁጣን የማያመለክት አገላለጽን ነበር:: ኤምብሪማዖማይ (*Embrimaomai*) የሚለው ቃል ስሜትን ፈንቅሎ የሚወጣ ሁኔታን፣ እንዲያውም የብስጭት፣ «ኀይለ ቃልን» ሊያመለክት ይችላል::[155] እንደዚያ ያለ ጠንካራ ማስጠንቀቂያ ቢሰጣቸውም፣ እነርሱ ግን ከመናገር ወደ ኋላ አላሉም:: የኢየሱስ ታዋቂነት እየሰፋ የመምጣቱን ያህል፣ በእርሱም ላይ የተነሣው ተቃውሞም እየበረታ ሄደ::

ማቴ 9፥32-34

[32]ከዚያም ሲወጡ፣ በጋኔን የተያዘ ድዳ ሰው ወደ እርሱ አመጡ:: [33]ጋኔኑ ከወጣለት በኋላ ድዳው መናገር ጀመረ፤ ሕዝቡም ተደንቀው፣ «እንዲህ ያለ ነገር በእስራኤል ምድር ታይቶ አያውቅም» አሉ::

[34]ፈሪሳውያን ግን አጋንንትን የሚያስወጣው በአጋንንት አለቃ ነው» አሉ::

(1976): 591-602 ላይ አይሁድ እንደ መሲሕና ንጉሥ ሊቀበሉት ፈቃደኛ ካለመሆናቸው አንጻር ሙግታዊ አነጋገር መሆኑን ያመለክታል:: ከኅብረተሰቡ የተገለሉት ዐይነ ስውሮቹ እውነተኛ ንጉሣቸውን «ማየት» ሲችሉ የሃይማኖት መሪዎቹ ዓይን ግን እርሱን እንዳያዩ ታወሩ::

[155] ቃሉ በአዲስ ኪዳን ጥቅም ላይ የዋለው አራት ጊዜ ብቻ ሲሆን፣ ጥቅም ላይ በዋለበት ስፍራ ሁሉ ጥልቅ ስሜትን ለመግለጽ ነበር (ማር 1፥43፤ 14፥5፤ ዮሐ 11፥33፣38)::

ይህ ምስኪን ሰው በአጋንንት በመያዝና በዲዳነት እየተሰቃየ ነበር፡፡ ኮፎስ (Kophos) የሚለው ቃል ድዳነትን፣ ደንቆሮነትን ወይም ሁለቱንም ማመልከት ይችላል፡፡ ብዙ ጊዜ ደግሞ ሁለቱ ይያያዛሉ፡፡ አንድ ሰው ከድንቁርና ጋር ከተወለደ፣ የመናገርም ችግር ሊኖረው ይችላል፡፡ የዚህ ሰው አካላዊ ችግር ከጋኔኑ ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ማለት ግን የማንኛውም አካላዊ ጉድለት ምክንያት አጋንንት ናቸው ማለት አይደለም (ማር 7፥32-34 ጋር ያነ)፡፡

ኢየሱስ ለፈሪሳውያን ክስ (ማቴ 9፥34) ቢያንስ እዚህ ቦታ ላይ መልስ አልሰጠም፡፡ ይሁን እንጂ ይኸው ክስ ኢየሱስ የተሟላ መልስ በሰጠበት በማቴዎስ 12፥24-37 በድጋሚ ተሰንዝሯል፡፡ ቅደም ተከተላዊ የጊዜ አቀራረብ ሥርዓታችን ትክክል ከሆነ ማቴዎስ 12፥24-37 ላይ ያለው የተፈጸመው ማቴዎስ 9፥3 ላይ ካለው ሁኔታ አስቀድሞ ነው፡፡ ስለዚህ ኢየሱስ ለቀረበበት ክስ መልስ የሰጠ በመሆኑ፣ እዚህ ላይ ምላሽ የሰጠበትን ሙግት በድጋሚ ዝም ማሰኘት አያስፈልገውም ማለት ነው፡፡ ያም ሆኖ ፈሪሳውያን ይህንኑ ክስ (*elegon*) ማቅረባቸውን ቀጥለዋል፡፡

በሕዝቡ በኩል መጨናነቅ፣ በአይሁድ መሪዎች ዘንድ ደግሞ ተቃውሞ እየጨመረ ቢሄድም ኢየሱስ፣ «በምኩራቦቻቸው እያስተማረ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት የምሥራች እየሰበከ፣ እንዲሁም ደዌንና ሕመምን ሁሉ እየፈወሰ በከተሞቹና በመደንደሮቹ» እየተዘዋወረ ማገልገሉን ቀጥሏል (ማቴ 9፥35)፡፡

**§69**
**ኢየሱስ ወደ ናዝሬት ያደረገው የመጨረሻ ጉዞ**
**(ማቴ 13፥54-58፤ ማር 6፥1-6)**

በዚህ አጭር ትረካ ኢየሱስ ባደገበት ከተማ ይኖሩ በነበሩ ሰዎች መገፋቱን እንመለከታለን፡፡ ይህ ግን በኢየሩሳሌም ለሚጠብቀው ትኩረት አመልካች ነበር፡፡ በዋናው ከተማ የአይሁድ ንጉሥ ኢየሱስ በገዛ ወገኖቹ ሊገፋና በኋላም ሊገደል ነው (ዮሐ 1፡11)፡፡ የናዝሬት ጉዞውና በሉቃስ 4 ላይ የተዘገበው ተመሳሳይ ሁኔታዎች ሳይሆኑ አይቀሩም፡፡ ወደ ፊት የሚያከናውናቸውን ተግባሮች ቊልፍ መሪ ሐሳቦች ለማጉላት ሲል ሉቃስ ይህን ያሰፈረው በኢየሱስ አገልግሎት መጀመሪያ ላይ ነበር (ከሉቃ 4፥14-15 ጋር ያነ)፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ማቴዎስና ማርቆስ ይህንን ትረካ ለኢየሱስ አገልግሎት መደምደሚያነት ተጠቅመውበታል፡፡

**ማር 6፥1-6**
**ማቴ 13፥55፡58**
**ጋር**

[1]ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ከዚያ ተነሥቶ ወደ ገዛ አገሩ ሄደ፤ ደቀ መዛሙርቱም ተከተሉት፡፡ [2]ሰንበትም በደረሰ ጊዜ በምኵራብ ያስተምር ጀመር፤ የሰሙትም ብዙ ሰዎች ተደነቁ፡፡

እነርሱም እንዲህ አሉ፤ «ይህ ሰው እነዚህን ነገሮች ከየት አገኛቸው? ይህ የተሰጠው ጥበብ ምንድን ነው? ደግሞም እነዚህ ታምራት እንዴት በእጁ ይደረጋሉ? [3]ይህ ዐናጢው [የዐናጢው ልጅ[ማቴ]] አይደለምን? የማርያም ልጅ፣ የያዕቆብና የዮሴፍ፣ የይሁዳና የስምዖን ወንድም አይደለምን? እኅቶቹስ እዚህ እኛው ዘንድ አይደሉምን?» ከዚህም የተነሣ ተሰናከሉበት፡፡

[4]ኢየሱስም፣ «ነቢይ የማይከበረው በገዛ አገሩ፣ በዘመዶቹ መካከልና በቤተሰብ ዘንድ ብቻ ነው» አላቸው፡፡ [5]እዚያም በጥቂት ሕመምተኞች ላይ እጁን ጭኖ ከመፈወሱ በስተቀር ምንም [ብዙ[ማቴ]] ታምራት ሊሠራ አልቻለም፤ ባለማመናቸውም ተደነቀ፡፡

ኢየሱስ ከቅፍርናሆም የተነሣውና በቀጥታ ወደ ናዝሬት ያመራው የኢያኢሮስን ልጅ ከፈወሰ በኋላ ይመስላል፡፡ ከዚህ በኋላ ቅፍርናሆም የኢየሱስ አገልግሎት ማዕከል አትሆንም፡፡ እንደ ታዋቂ መምህር ሁሉ የደቀ መዛሙርት አጀብ አስከትሎ ወደ፣ «አገሩ»[156]

[156] ፓትሪስ (*Patris*) የሚለው ቃል በአጠቃላይ የሚያመለክተው፣ «ትውልድ አገር»ን ነው፡፡ ይሁን እንጂ ኢየሱስ በገሊላ ስለ ነበር ከዚያ ይልቅ በጣም

ተመልሷል:: ወደዚያ የተመለሰው ቤተ ሰቡን ለመጠየቅ ብቻ አልነበረም:: ከቤተሰቦቹ አብዛኞቹም በቅፍርናሆም መኖር ሳይጀምሩ አልቀረም (ዮሐ 2÷12):: አመጣጡ የሥራ ጉብኝት እንደሚያደርግ መምህር እንጂ ወደ አገሩ ተመልሶ እንደሚመጣ ጀግና ዓይነት አልነበረም::

ትምህርቱን ቢወዱትም፣ ጥበቡ ቢያስደነግጣቸውና በተአምራታዊ ኃይሉ ቢደነቁም፣ በምኩራብ የነበሩት ምዕመናን የኢየሱስን ማንነት አልተቀበሉትም:: ለምን? ምክንያቱ ኢየሱስ የሚያደርገው ትርጉም አልባ ስለ ሆነባቸው፣ ወይም ትምህርቱን በማስረጃ ባለማስደገፉ አልነበረም፤ ይልቁንም ዋናው ምክንያትም ከእርሱ ጋር በጣም በመላመዳቸው ነበር:: ብዙዎቹ በኢየሱስ ወይም በአባቱ[157] የተሠሩ የቤት ዕቃዎች ወይም ቤቶች ነበሯቸው:: ወላጆቹን ያውቃሉ፤[158] ኢየሱስንና ታናናሽ ወንድሞችና እኅቶቹን ከልጅነታቸው አንሥቶ በማሳደግ ተባብረው::[159] (4 ወንድሞች[160] እና ቢያንስ 2 እኅቶች)::[161]

---

ግልጽ መሆን አለበት:: ስለሆነም «ትውልድ ከተማ» የሚለው ትክክለኛ ትርጒም ነው ማለት ነው::

157 *tektos* የሚለው ቃል፣ «ግንበኛ» ለማለትም ይሆናል፤ ሆኖም ይህ አጠራር 'አናጢ' የሚለውን ያህል የተለመደ አልነበረም::

158 ብዙውን ጊዜ ልጆች የሚጠሩት በእናታቸው ሳይሆን በአባታቸው እንደ መሆኑ መጠን እዚህ ላይ የዮሴፍም ስም ያልተነሣው ሞቶ ስለ ነበር ሊሆን ይችላል (ዮሐ 2÷1-5፤ §29 ጋር ያነጻጽሩ):: አንዳንዶች ደግሞ ኢየሱስ ከድንግል መወለዱን ሕጋዊ ልጅ ያለመሆኑን ከማመን አንጻር «የማርያም ልጅ» የሚለውን አጠራር ያመጣችው የጥንት ቤተ ክርስቲያን ናት የሚል ሐሳብ አቅርበዋል:: ይሁን እንጂ H.K. Mc Arthur ይህን አጠራር ስለ ኢየሱስ ለመግለጽ የተጠቀሙበት የናዝሬት ሰዎች ሲሆኑ እነርሱም እንዲሁ ከዘሩ ወይም ትውልዱ ሐረጉ ጋር የተያያዘ የተለየ ሥነ ምግባራዊም ሆነ የትውልድ ሐረግ ትርጒም እንዳልሰጡት መብታቸውን አቅርበዋል ("Son of Mary," *NovT* 15 [1993]: 38-58).

159 እነዚህ ወንድሞችና እኅቶች የተባሉት የኢየሱስ የሥጋ ዘመዶቹ ሳይሆኑ (ከፊል ወንድሞች/እኅቶች) የአክስት የአጎት ልጆች (ጀሮም) ወይም፣ ዮሴፍ ከቀድሞ ሚስቱ የወለዳቸው ልጆች (ኤጲፋነስ) ናቸው የሚለው አመለካከት



መቼም፣ ይህ የመንደር ልጅ መሲሕ ነኝ ብሎ ሊያስብ አይችልም:: በትውልድ ቀዬ መኩራራት ያልተለመደ ነገር ነው:: ይልቁንም ልጆቻቸው ወደ ውጭ ሄደው በሄዱበት አገር ትልቅ ቢሆኑ ኖሮ ነበር የሚኩራሩት:: ወደ አገራቸው ተመልሰው ሲመጡ ሕፃናት ሳሉ ያደርጉት የነበረውን ሊያስታውሷቸው ይሞክራሉ:: ሁኔታቸው፣ «እርግጥ ትልቅ ነገር አድርገሃል ከዚህም የተነሣ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነሃል ሆኖም ይህን ያህል ትልቅነት አይሰማህ፤ ከአንተ የበላለጥን ሰዎች እዚህ መኖራችንን አትርሳ!» የሚል ዓይነት ይመስላል::

በመጀመሪያ የናዝሬት ጕዞው ኢየሱስን ለመግደል ሞክረው ነበር:: በዚህ ሁለተኛው ጕዞው ግን ሊቀበሉት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ብዙዎችን መፈወስ አልቻለም:: እዚህ ላይ ማቴዎስ የማርቆስን አቀራረብ ግልጽ በማድረግ ኢየሱስ ብዙ ተአምራት ያላደረገው ባለማመናቸው ምክንያት እንደ ነበር አመልክቷል (ምንም እንኳ ማርቆስ ጥቂት ሕመምተኞች መፈወሳቸውን ቢናገርም):: ችግሩ ኢየሱስ ኀይል ማጣቱ ሳይሆን፣ ሕዝቡ እንዲረዳቸው ወደ እርሱ አለመምጣታቸው ነበር:: ብዙ ጊዜ የኢየሱስ ምርጫ ሰዎችን ለእምነታቸው ምላሽ በመስጠት መፈወስ

---

የማርያምን ዘላለማዊ ድንግልና ለማሳየት በሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን አመለካከት ላይ የተመሠረተ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ግን ይህንን አይደግፍም፤ ደናግላን ካገቡት የበለጠ መንፈሳውያን መሆናቸውንም የሚያመለክት ሃሳብ አይሰጥም:: J.P. Meier, "The Brothers and Sisters of Jesus in Ecumenical Perspective," *CBQ* 54 (1992): 1-28 ካለው ጋር ያነጻጽሩ::

160 ከኢየሱስ ወንድሞች መካከል በጣም የሚታወቀው ያዕቆብ ሕይወቱ የተለወጠው ከሞት የተነሣው ኢየሱስ ከታየው በኋላ ነበር (1ቆሮ 15÷7):: በኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን እውቅ መሪ ከመሆኑም በላይ (ሐሥ 12÷17፤ 15÷13፤ 21÷18፤ ገላ 1÷19፤ 2÷9:12) የያዕቆብን መልእክት የጻፈው እርሱ እንደሆነም ይታሰባል:: «ጆሴፈስም ሆነ (*Ant.* XX: 200) አውሳቤዎስ (*Ecclesiastical History* 2.33) በአሰቃቂ ሁኔታ መገደሉን አስፍረዋል» (Wessel, p. 665):: ይሁዳም የይሁዳ መልእክት በመባል የሚታወቀው ጸሐፊ ሳይሆን እንደማይቀር ይታሰባል::

161 ዌሴል እንደሚያመለክተው፣ «ከዚህ ጥያቄ በስተጀርባ፣ ኢየሱስ በሕይወት ዘመን ሁሉ ሲሰፋፋ የኖረ አንድ ሐሜት ሊኖር እንደሚችል አመልክቷል፤ ይኸውም ከጋብቻ ውጪ የተወለደ ነው የሚለው ነው» (ዮሐ 4÷41፤ 9÷29፤ SBK, 1:39-43; Origen *Contra Celsum*, 1.28)," p. 665. ጋር ያነ::

ነበር:: በዚህ በናዝሬት ውስጥ ግን ምላሽ የሚሰጠው ምንም ነገር አልነበረም::

**§ 70ሀ**
**ሦስተኛ የገሊላ ጉዞ**
**(ማቴ 9÷35-38፤ ማር 6÷6)**

ማቴዎስ 9÷35-11÷1 አንድ ወጥ ክፍል ነው:: ኢየሱስ ዐሥራ ሁለቱን ለወንጌል ሥራ ከገሊላ ማዶ እንደ ላከ ይገልጻል:: ይህ ማቴዎስ ካስፈራቸው አምስት ታላላቅ ንግግሮች ሁለተኛው መሆኑ ነው:: ማርቆስና ሉቃስ ይህን፣ «ተልዕኮ»[162] አጭር በሆነ ሁኔታ ነው ያቀረቡት:: ሆኖም እርሱ ያቀረቡት ማቴዎስ ካስፈረው አንድ ስምንተኛ ይሆናል::[163]

[35]ኢየሱስ በምኩራቦቻቸው እያስተማረ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት የምሥራች እየሰበከ፣ እንዲሁም ደዌንና ሕመምን ሁሉ እየፈወሰ በከተሞቹና በመንደሮቹ ዞረ:: [36]ሕዝቡም እረኛ እንደሌለው በግ ተጨንቀውና ተመልካች የለሽ ሆነው ባየ ጊዜ አዘነላቸው:: [37]ደቀ መዛሙርቱንም እንዲህ አላቸው፤ «መከሩ ብዙ ነው፤ የመከሩ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው፤ [38]ስለዚህ የመከሩ ጌታ፣ ወደ መከሩ ሠራተኞችን እንዲልክ ለምኑት::»

---

162 R.e. Morosco, "Matthew's Formation of a Commissioning Type Scene Out of the Story of Jesus' Commissioning of the Twelve," *JBL* 103/4 (1984): 539-556 እንደሚለው ማቴዎስ የተጠቀመበት ቋንቋ በብሉይ ኪዳን ሰዎች ለተለያየ ኀላፊነት ሲሰማሩ ይናገሩ የነበሩ ከነበረው ትረካዎች ውስጥ ይጠቀሱ ከነበሩት ጋር በጣም ተመሳሳይ ሃሳቦችን የያዘ ነበር (ለምሳሌ ዘፀ 3÷1-4÷17):: (1) መግቢያ፣ (2) ተግዳሮት፣ (3) ተልዕኮ፣ (4) ተቃውሞ፣ (5) ማረጋገጫ፣ (6) ማጠቃለያ፣ (7) አዳጋች ሁኔታ ስለ ሆነም ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን የላከበት መንገድ በብሉይ ኪዳን ዘመን ይሆዋ ባሪያዎቹን ለአገልግሎቱ፣ ያስማራ ከነበረበት ሁኔታ ጋር ተመሳሳይ እንደ ነበር ለአንባቢዎቹ ለማሳየት ማቴዎስ ይህን ንግግር በተገቢው ሁኔታ አቀናብሮታል የሚል ሐሳብ በማቅረቡ ከአንባቢዎቹ አበረታች ምላሽ እንዲኖር አድርጓል::

163 ማርቆስና ሉቃስ አብዛኛውን የዚህን ንግግር ክፍል እዚህና በወንጌሎቻቸው በተሰባጠሩ ሌሎች ዐውዶችም አስፍረውታል:: ለተጓዳኝ ምንባቦች ሰንጠረዥ ለማየት R.E. Morosco, "Redaction Critcism and the Evangelical: Mt 10 A Test Case," *JETS* 22/4 (1979): 327 ይመ::



ይህ ሦስተኛው የኢየሱስ የገሊላ ጉዞ ነው:: ለብቻቸው ሳይልካቸው በፊት ዐሥራ ሁለቱ ኢየሱስ የሚያደርገውን በቅርብ ተገኝተው የሚመለከቱበት የመጨረሻ ጊዜ ይሆናል:: እዚህም ላይ ቢሆን ያው ሌላ ጊዜ የምናውቀው ኢየሱስ ነው፤ (1) በምኩራቦቹ የእግዚአብሔርን መንግሥት ሰበከ፣ (2) ማንኛውንም ዓይነት ሕመም ፈወሰ፣ (3) ለሕዝቡ በነበረው ርኅራኄ ይንቀሳቀሳ ነበር::

ኢየሱስ እያገለገለ በሕዝቡ መካከል ሲመላለስ ምን ያህል ችግር ውስጥ መሆናቸውን እየተመለከተ ያዝን ነበር:: ያ ደግሞ ብቻውን ማድረግ የሚችለው አልነበረም:: ስለሆነም ተጨማሪ ሠራተኞች ይላኩ ዘንድ እንዲጸልዩ ደቀ መዛሙርቱን ጠየቀ:: ብዙውን ጊዜ እንደሚሆነው ተጨማሪ ሠራተኞች እንዲላኩ ደቀ መዛሙርቱ ያቀረቡት ጸሎት (ቍ 38) መልስ ያገኘው ክርስቶስ በግል ሰዎችን ለአገልግሎት ባሰማራበት ጊዜ ነበር (ማቴ 10):: በዚህ ሁኔታ በቍጥር 37-38 ያለው ለማቴዎስ 10 ያዘጋጀናል:: ብዙ የችግረኛ ሰዎች ከፍተኛ ፍላጐት ከሚሰጡ ሰባኪዎች ቍጥር አነስተኛ ከመሆኑ ጋር ተጣምሮ ዛሬም ላለው የሚስዮናዊነት ሥራ ብርቱ ግፊት ምክንያት ነው::

**§70ለ**
**ደቀ መዛሙርት ሁለት ሁለት እየሆኑ ተላኩ**
**(ማቴ 10÷1-42፤ ማር 6÷7-11፤ ሉቃ 9÷1-5)**

ይህ አስደናቂና ምላሽን አጠንክሮ የሚጠይቅ ስብከት ነው:: እየተነተንነው ስንሄድ ከስብከቱ ሦስት ነገሮችን መመልከት ይቻላል:: በመጀመሪያ የአይሁድ አነጋገር ፈሊጥ አስተሳሰብ የሞላበት መሆኑን ነው:: ያም ሆኖ ማንኛውንም ብሔራዊ ድንበር አልፎ መሄድ የሚችል ነው:: የት ላይ እንደ ጀመረ ግልጽ ነው፤ ይሁን እንጂ አንባቢውን እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ተስፈንጥሮ እንዲሄድ ያደርገዋል:: ሁለተኛው ትንቢታዊ ይዘት ያለው መሆኑን ነው:: እንደዚህም በመሆኑ የመጀመሪያው የትንቢቱ ፍጻሜ በዚያ ጉዞ ወቅት የሚታይ ቢሆንም፣

ሙሉ በሙሉ የሚፈጸመው ግን በመላው ዓለም የወንጌል ተልዕኮ ነው:: ሦስተኛው ማቴዎስ እንደተለመደው የአሁንና የወደፊቱን ጊዜ፣ «መላክ»[164] በሚለው አንድ ነገረ መለኮታዊ ዐቢይ ርእስ ሥር ማስፈሩን ነው:: ስለሆነም ይህን ክፍል የምናነበው በአንድ በኩል የአሁኑን ጊዜ በሌላ በኩል ደግሞ ከአድማስ ባሻገር ያለውን እያሰብን ይሆናል::

ማቴ 10÷1፤ ማር 6÷7፤ ሉቃ 9÷1-2 ጋር

ኢየሱስ ዐሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ወደ እርሱ ጠርቶ ርኩሳን መናፍስትን እንዲያወጡ፣ ደዌንና ሕማምን ሁሉ እንዲፈውሱ ሥልጣንን ሰጣቸው [ሁለት ሁለቱን ላካቸው[ማር]]::

ኢየሱስ ሐዋርያት የተሰኘ ስም የተሰጣቸውን የቅርብ ደቀ መዛሙርቱን በገሊላ ወደ ነበሩ ከተሞችና መንደሮች ሁሉ ልኳቸዋል:: ሁለት ወይም ሦስት ምስክሮች እንደሚያስፈልጉ ሙሴ በሰጠው መመሪያ መሠረት ሁለት ሁለቱን ነበር የላካቸው:: ከዚህም በላይ አንዱ ሌላውን ከአደጋ መከላከልና ማበረታታት ይችላል፤ አንዱ ለሌላው ስጦታና ድጋፍ ሊሰጥ እንዲሁም እርስ በርሳቸው ስብከት የተለያዩ ኀላፊነቶችን ሊከፋፈሉ ይችላሉ:: በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የተጠቀሱት ሰባኪዎችም ይህንን ናሙና ተከትለዋል:: ጥበብ ያለበት ወንጌልን የማዳረስ መርሐ ይመስላል::

---

[164] ከማቴዎስ ምዕራፍ 10 ይዘት እንደምንረዳው ማቴዎስ ከዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ጉዞ ባሻገር በአእምሮው ያሰበ ይመስላል:: የምናያቸው መሳይ የሐሳብ አለመጣጣሞችና (ማቴ 10÷5-6፤ 10÷18 እና 9÷37-38፤ 10÷16-22) እንዲሁም በተለያዩ ዐውዶች ያሉ ተጓዳኝ ምንባቦች (ማቴ 10÷17-22 እና ማር 13÷9-13 ጋር ያነ) የሚያሳስቡን ማቴዎስ በየጊዜው የተሰጡ ተልዕኮ መሳይ ንግግሮችን በአንድ ስብከት ውስጥ «አሰባስቦ» ሊሆን እንደሚችል ነው (Morosco, pp. 323-331ን ይመ):: ይህ ትክክል ከሆነ የምናነበው ይህ ክፍል ለዐሥራ ሁለቱ የተሰጠ ማብራሪያ ብቻ ሳይሆን፣ ለክርስቲያን የወንጌል ሠራተኞች ሁሉ የተሰጠ መመሪያ ነው ማለት ይችላል:: በሌላ አነጋገር ለዐሥራ ሁለቱ ብቻ ሳይሆን ኢየሱስ ለእኛም ጭምር ምን እያለን እንደሆነ ትኩረት ልንሰጠው ይገባል::



ኢየሱስ ኀይልና ሥልጣን የሰጣቸው ሁለት ነገሮችን እንዲያደርጉ ነበር፤ (1) የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዲሰብኩ (ዮሐንስና ኢየሱስ እንዳደረጉት):: (2) ማንኛውንም ሕመምና በሽታ እንዲፈውሱ:: ሕመም ለሚለው ማቴዎስ ሦስት አቻ ቃሎችን ያቀርባል፤ በሽታ (*noson*)፣ ሕመም (*malakian*) እና በሽተኛ (*asthennountas*) ቃል በቃል ሲወሰድ፣ «ደካሞች» ማለት ነው (ቍ. 8):: በሌላ አነጋገር ለማንኛውም አካላዊ ጉድለት ማለትም አብሮ ለተወለደ የአካል ጉዳትም ይሁን፣ በተለያዩ አደጋዎች ወይም ቫይረስ ምክንያት ለሚመጣ ሕመም መፍትሔ መስጠት ይችላሉ:: በተጨማሪም፣ በአጋንንትም ላይ ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል:: ስለዚህም ለመንፈሳዊም ሆነ ለሥጋዊ ሕመሞች መፍትሔ መስጠት ይችላሉ::

ማቴ 10÷2-4

2የዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ስም የሚከተለው ነው:: መጀመሪያ ጴጥሮስ የተባለው ስምዖንና ወንድሙ እንድርያስ፣ የዘብዴዎስ ልጅ ያዕቆብና ወንድሙ ዮሐንስ፤
3ፊልጶስና በርተሎሜዎስ፣ ቶማስና ቀረጥ ሰብሳቢው ማቴዎስ፣ የእልፍዮስ ልጅ
ያዕቆብና ታዴዎስ የተባለው ልብድዮስ፣
4ቀነናዊው ስምዖንና በኋላ ኢየሱስን አሳልፎ
የሰጠው አስቆሮቱ ይሁዳ (§ 53፣ ማር 3÷13-19፤ ሉቃ 6÷12-16 ጋር ያነ)::

ማቴዎስ የዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያትን ስም ዝርዝር ያቀረበው ኢየሱስ ሐዋርያቱን ሁለት ሁለት እያደረገ በላከበት መልኩ ይመስላል::[165] በሥጋዊም ሆነ በመንፈሳዊ ደረጃ የሚገጥሟቸውን የጨለማ ኀይላት ተቃውሞ መቋቋም ይችሉ ዘንድ ሁለት ሁለት ሆነው ተልከዋል:: በጣም የሚገርመው ደግሞ የአስቆሮቱ ይሁዳ ከቀነናዊው ስምዖን ጋር መጣመሩ ነው:: ሁለቱ በአንድነት ሲሆኑ ምን ዓይነት

---

[165] *Kai* «እና» በሚለው መጠቀሙ ጥንዶችን ለማመልከት ሊሆን ይችላል:: አዲሱ መደበኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጒምም ጥንዶቹን ለመለየት ነጠላ ሠረዝ ስለሚጠቀም ጥንዶቹ ማን እንደሆነ ለማወቅ ይረዳል::

ጠንካራ ቡድን ይወጣቸው ይሆን:: ይሁዳ ከሌሎች ያነሰ ሕመምተኞችን መፈወሱን ወይም ከተቀሩት የተለየ ወንጌል መስበኩን የሚያሳይ ምንም ፍንጭ የለንም:: ከዚህ በመነሣት ሰዎች በሚያደርጉት ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴ እውነተኛ ባሕርያቸውን ማወቅ ከሚያስችል ድምዳሜ ላይ መድረስ በፍጹም አይቻልም::

*ማር 10፥5-10፤ ማር 6፥9 ጋር*

[5]እነዚህን ዐሥራ ሁለቱን ኢየሱስ እንዲህ ከሚል ትእዛዝ ጋር ላካቸው፤ «ወደ አሕዛብ አትሂዱ፤ ወደ ሳምራውያንም ከተማ አትግቡ:: [6]ይልቁንስ የእስራኤል ቤት ወደ ሆኑት ወደ ጠፉት በጎች ሂዱ:: [7]ሄዳችሁም፣ «መንግሥተ ሰማያት ቀርባለች ብላችሁ ስበኩ:: [8]በሽተኞችን ፈውሱ፣ ሙታንን አስነሡ፤ ለምጻሞችን አንጹ፤ አጋንንትን አስወጡ፤ በነጻ የተቀበላችሁትንም በነጻ ስጡ:: [9]በመቀነታችሁ ወርቅም ሆነ ብር ወይም መዳብ አትያዙ:: [10]ስመንገዳችሁም ከረጢት ወይም ትርፍ እጀ ጠባብ ወይም ጫማ ወይም በትር አትያዙ፤ [ከበትር በስተቀር እንጀራ ወይም ከረጢት ወይም ደግሞ ገንዘብ በመቀነታችሁ አትያዙ፤ ጫማ አድርጉ፤ ነገር ግን ሁለት እጀ ጠባብ አትልበሱ[ማር]] ለሠራተኛ የዕለት ጉርሱ ይገባዋልና::

*[8]የግሪኩ ቃል የግድ ከለመጽ ጋር ብቻ የተያያዘ ሳይሆን ልዩ ልዩ የቆዳ በሽታዎችንም ያመለክታል::*

*መመሪያዎቹ የተሰጡት ለዚያ በአገር ውስጥ ለተመደበው ጉዞ* ነበር:: በኋላ እንደምናየው ኢየሱስ ገንዘብ፣ ቦርሳ ሰይፍ እንዲይዙ ነግሮአቸው ይህንን ትእዛዝ ቀልብሶታል (ሉቃ 22፥35-36):: ይህ ግን ተግባር ላይ የሚውለው ደቀ መዛሙርት ወደ ዓለም ሁሉ በሚላኩበት ጊዜ ይሆናል (ማቴ 28፥18-20):: እነዚህ መመሪያዎች ጊዜያዊ ይሆኑ ዘንድ ይህንን ጉዞ የተለየ ያደረገው ምንድነው?

(1) ጉዞው አጭርና አጣዳፊ መሆኑ ነው:: ብዙ ገንዘብ ወይም መለወጫ ልብሶች አያስፈልጉም:: ጉዞው አጭር በመሆኑ መጠን ቀለል



ያሉ ነገሮችን መያዝና ቶሎ ቶሎ መራመድ ነበረባቸው:: በተጨማሪም በየሚሄዱባቸው በእያንዳንዱ ከተማ የሚቀበሏቸው ሰዎች በቤታቸው ሊስተናግዷቸውና ለጥቂት ቀኖች የሚበሉትን ሊሰጧቸው ይችላሉ:: ከሐዋርያቱ ከሚያገኙት የሕክምና ውለታ አንጻር ይህን ቢያደርጉ አይበዛባቸውም::

(2) ገና ከፍ ያለ ችግር የሚጋፈጡበት ሁኔታ ላይ አልነበሩም:: በተለያየ መልኩ ኢየሱስ ላይ ተቃውሞ ተነሥቶአል፤ በአካሉ ላይ ጉዳት የሚያደርስ ስደት ግን ገና አልተነሣም ነበር:: ስለሆነም ደቀ መዛሙርቱ የሚያሰጋ ሁኔታ ላይ አልነበሩም:: ራሳቸውን የሚከላከሉበት ሰይፍ አያስፈልጋቸውም::

(3) ጉዞው በገሊላ አካባቢ የተደረገ የአገር ውስጥ ጉዞ ነበር:: ኢየሱስ ለአሕዛብና ለሳምራውያን እንዳይሰብኩ ያዘዘው እነዚህን ሰዎች ባለመውደዱ ሳይሆን፣ ጉዞው አጭር በመሆኑና ከትክክለኛው ጊዜ ቀደም ብሎ በመደረጉ ነበር:: በአካባቢው ያሉ አይሁድ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት የሚያቀርበውን ይህንን ንግግር እጅግም አይረዱትም:: ባዕዳን እንዴት አድርገው ሊረዱት ይችላሉ? ከትንሣኤው በኋላ ሐዋርያቱ ወደ አሕዛብ ሁሉ የሚላኩበት ጊዜ ይመጣል (ማቴ 10፥18 እንኳ ስለዚህ ጉዳይ ፍንጭ ይሰጣል) አሁን ግን ያ ጊዜ አልደረሰም::[166] ሐዋርያቱ

---

[166] ማቴ 10፥5-6 እና ማቴ 15፥21-28 የኢየሱስን አገልግሎት በአይሁድ ብቻ ገድበውታል:: ኢየሱስ ወደ ፊት ወንጌልን ለአሕዛብ የማዳረስ ሐሳብ ነበረው (ማቴ 21፥13፤ ሉቃ 4፥16-30፤ ዮሐ 10፥16):: አሕዛብ ኢየሱስን ከመቀበላቸው በፊት ግን በመጀመሪያ ለአይሁድ ተልእኮውን መፈጸም ነበረበት (ሐሥ 13፥46፤ 28፥28፤ ሮሜ 1፥16፤ 11፥11-12:25-26)፣ ይህም ለኀጥአን ምትክ ሆኖ መሞቱን ይጨምራል:: J.J. Scott, "Gentiles and the Ministry of Jesus: Further Observations on Mt 10:5-6; 15:21-28," *JETS* 33/2 (1990): 161-169 ላይ በትክክል እንዳስተዋለው፣ «የመቶ አለቃው እንደ ከነዓናዊቷ ሴት ሁሉ ጥያቄው ተቀባይነት ያገኘው በእስራኤልና በሌሎች መካከል ያለውን ልዩነት በመረዳቱ ነበር:: ምንም እንኳ ኢየሱስ በመጨረሻው ጊዜ ስለሚሆነው የአሕዛብ ሁሉ መሰባሰብ አሻግሮ እየተመለከተ ቢሆንም የከነዓናዊቷን ሴት፣ የመቶ አለቃውን አገልጋይና አንዳንድ የተለዩ ሰዎችን ጉዳይ ወደፊት ከሚያደርገው ለየት አድርጐ ተመልክቶታል::

ለእነዚህ አካባቢዎች እንግዶች አለመሆናቸውንም መረዳት አለብን:: ለአንድ ዓመት ያህል ኢየሱስ በዚህ አካባቢ ከእነርሱ ጋር ሲዘዋወር ነበር:: ዝናው እየገነነ ሄዶ ነበር፤ ደቀ መዛሙርቱም የአርሱ ቅርብ ሰዎች መሆናቸው ታውቋል:: አድማጭም ሆነ ማረፊያ ቦታ የማግኘት ችግር አይገጥማቸውም::

በተጨማሪም አጠቃላይ በሆነ መልኩ ስንመለከተው ይህ መጀመሪያ ወደ አይሁድ ከዚያ በኋላ ወደ ሳምራውያን እንዲሄዱ ከተሰጠው መመሪያ ጋር ይስማማል (ሮሜ 1÷16፤ ሐሥ 13÷46፤ 18÷6፤ 19÷9፤ 28÷25-28)::

በማቴዎስ 10÷10 እና በማርቆስ 6÷8 መካከል እርስ በርሱ የሚቃረን የሚመስል ጉዳይ አለ:: ማቴዎስ፣ «በትር አትያዙ» ሲል፣ ማርቆስ ግን፣ «ከበትር በስተቀር ምንም ... አትያዙ» ይላል:: ማርቆስ የተጠቀመው አይሮ (*airo*) ማለት «ያዙ» ወይም «አንሱ» የሚል ቃል ሲሆን ማቴዎስ ደግሞ የተጠቀመው ታኦማይ (*ktaomai*) ማለት «ሸክፉ» ወይም «በጓዛአችሁ ጨምሩ» የሚለውን ነው:: ስለዚህ ማቴዎስ ለጉዞ የሚሆኑ ነገሮች በእጃቸው እንዳላቸው አድርጐ ስለ ቈጠረ ለመንገድ ይሆነኛል በማለት ተጨማሪ ሸክም ማብዛት እንደሌለባቸው አስቧል:: በሌላ አነጋገር ለጉዞ የሚያስፈልጋቸው በትር ቀደም ሲል በእርግጥ እጃቸው ላይ ነበር ማለት ነው:: ለዚህ ጊዜ የሚሆን ሌላ በትር አያስፈልጋቸውም::

ኤደርሼይም እንደሚለው ተጨማሪ ነገር እንዳይይዙ የተሰጠው ትእዛዝ ለአገልግሎት ወደ ቤተ መቅደስ ሲገቡ፣ «በትር፣ ጫማ ... እና የገንዘብ መያዣ ከረጢት» መያዝ እንደሌለባቸው የአይሁድ ሃይማኖት መምህራን ካወጡት ትእዛዝ ጋር ይስማማል:: «እነዚህ ሁለቱ ትዕዛዛት የሚያስተላልፉት ተምሳሌታዊ መልእክት አንድና ተመሳሳይ ነው፤ ይሄውም መላ እኔነታቸው በጌታ አገልግሎት በተያዘበት ሁኔታ ወደ ሌላ



ጉዳይ የማዘንበልን አዝማሚያ እንዳለባቸው ማመልከት ነው» (Edershiem, I:643)::

ሁለት እጀ ጠባቦችም መያዝ አልነበረባቸውም:: ተጨማሪ እጀ ጠባብ መያዝ ለሸክም አያመችም፤ ውጪ የሚተኙ ከሆነ ግን ለመጠቀም ቀለል የሚለው እሱ ነው:: ኢየሱስ አጠንክሮ እየነገራቸው ያለው ለሠራተኛ ቀለቡ ስለሚገባው የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ በእግዚአብሔር ሰዎች በኩል እንደሚያገኙ በእግዚአብሔር እንዲተማመኑ ነው (1ቆሮ 9÷14፤ 1ጢሞ 5÷17-18 ጋር ያነ):: ያም ሆኖ ግን ያለ ክፍለያ ማገልገል ነበረባቸው:: በሌላ አነጋገር የዚህን ጉዞ ወጪ ራሳቸው እንዲሸፍኑ አይጠበቅባቸውም፤ ከጉዞውም የተለየ ጥቅም ማግኘት የለባቸውም (1ጴጥ 5÷2)::

**ማቴ 10÷11-16**
**ማር 6÷11፤ ሉቃ 9÷5 ጋር**

[11]ወደ አንድ ከተማ ወይም መንደር ስትገቡ ሲቀበላችሁ ፈቃደኛ የሆነ ሰው ፈልጋችሁ በቤቱ ዕረፉ፤ እስክትወጡም ድረስ በዚያው ቆዩ:: [12]ወደ ማንኛውም ሰው ቤት ስትገቡ ሰላምታ አቅርቡ:: [13]ቤቱም የሚገባው ሆኖ ከተገኘ ሰላማችሁ ይድረሰው፤ የማይገባው ከሆነ ግን ሰላማችሁ ወደ እናንተ ይመለስላችሁ:: [14]ማንም ሰው ሊያስተናግዳችሁ ወይም የምትናገሩትን ሊሰማ ፈቃደኛ ካልሆነ፣ ከቤቱ ወይም ከከተማው ስትወጡ [ምስክር እንዲሆንባቸው[ማር፤ሉቃ]] የእግራችሁን ትቢያ አራግፋችሁ ውጡ:: [15]እውነት እላችኋለሁ፤ በፍርድ ቀን በዚያች ከተማ ከሚደርሰው ቅጣት ይልቅ በሰዶምና በገሞራ የሚደርሰው ይቀላል:: [16]እንደ በጐች በተኲላዎች መካከል እልካችኋለሁ (ሉቃ 10÷3 ጋር ያነ) ስለዚህ እንደ እባብ ብልኆች እንደ ርግብ የዋኆች ሁኑ::

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ከቤት ወደ ቤት እንዳይዘዋወሩ ከልክሏል:: ለምን? በሄዱበት ቦታ ታዋቂዎች ስለሚሆኑ ነው:: ብዙዎች

እነርሱ ቤት ውስጥ እንዲያርፉ ይጠይቋቸዋል:: ችግሩ እንዲህ ያለው ሁኔታ በርካታ ውድ ጊዜን የሚሻማ ከመሆኑም ባሻገር በእያንዳንዱ መንደር ነዋሪዎች መካከል ጤናማ ያልሆነ ፉክክር እንዲፈጠር ማድረጉ ነው:: ለሐዋርያቱም ትኩረታቸውን በሙሉ በስብከት አገልግሎታቸው ላይ ከማድረግ ይልቅ የተሻለ መስተንግዶ እንዲጠብቁ ሊፈትናቸው ይችላል::

ወደ ሰዎች ቤት ሲገቡ እንደ ቡራኬ ሊሆን የሚችል ሰላምታ ማቅረብ አለባቸው:: ሰላም የሚለው የዕብራይስጥ ቃል (በቁ. 12-13 ያለው) እንደ ዋዛ ከሚቀርብ ሰላምታ በጣም ያለፈ መልእክት ያለው ነው:: ሰላምታ የሚቀርብለት ሰው በሰውየው በአካላዊ፣ በማኅበራዊና በመንፈሳዊ «ሁለንተናው» መልካም እንዲሆንለት ምኞትን የመግለጫ ቃል ነው:: ስለሆነም ለዚያ ቤት የሚቀርብ የሐዋርያቱ ጸሎት ያህል ይሆናል ማለት ነው:: በእርግጥ ይህ ብርቱ በረከት ነው (ማቴ 18÷18)::

የማይቀበሉዋቸው ከሆነ ግን ያንን መንደር ከመባረክ ይልቅ የእግራቸውን አቧራ ማራገፍ ነበረባቸው:: ከአሕዛብ ክልል ወደ ቅድስት አገር ሲገቡ አይሁድ ብዙውን ጊዜ የእግራቸውን ትቢያ የማራገፍ ልማድ ነበራቸው:: ለአይሁድ ይህ ፈሊጣዊ ድርጊት፣ «ሌላው ቀርቶ የምትረግጡት መሬት እንኳ ርኩስ ነው፤ ከርኩሰታችሁ ራሴን አነጻለሁ» የማለት ትርጉም ነበረው (ሐሥ 13÷51፤ 18÷6 ጋር ያነ):: ይህ በግብታዊነት ቁጣን ከመግለጽ ያለፈ ነበር:: በክርስቶስ በኩል የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ዕቅድ መናቅ ከአሕዛብ ጋር ያስቈጥራችኋል የሚል ማስጠንቀቂያ ነበረው:: ሐዋርያቱን አለመቀበል፣ እግዚአብሔርን ያለመቀበል ያህል ነበር:: ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ከተማን የመርገም ሥልጣን ነበራቸው:: ሁኔታው በማቴዎስ 11÷20-30 እና 12÷39-42 ካነበብነው ጋር ይመሳሰላል:: ከነበራቸው ከፍ ያለ ዕድል የተነሣ የገሊላ ሰዎች ከሰዶምና ገሞራ እንኳ የከፋ ፍርድ ይጠብቃቸዋል::



መቼም፣ ሰው ሁሉ እጁን ዘርግቶ ሊቀበላቸው አይችልም:: ስለሆነም መጠንቀቅ ነበረባቸው:: ኢየሱስ የሰጠው ማስጠንቀቂያ (ቍ 16) አራት ንጽጽሮሽ ያለበት ነው፤ በጐችና ተኩላዎች፣ እባቦችና ርግቦች:: በእባቦችና በርግቦች መካከል ያለው ንጽጽሮሽ፣ ብልኀነትና የዋህነት እንደ ሆነ ተገልጾአል:: እነዚህ ሁለት ባሕርያት ብዙውን ጊዜ ተቃራኒዎች ቢሆኑም፣ አንደኛው ሌላኛውን የሚደመስሰው ግን አይደለም:: የሚያሳዝነው ግን ክርስቲያኖች የዋህ እባቦችና ብልህ ርግቦች ሆነው መገኘታቸው ነው:: ምንም እንኳ ገለጻ ባይሰጥበትም በበጐችና በተኩላዎች[167] መካከል ያለው ንጽጽርም ግልጽ ነው፤ ደካማነትና ጨካኝነት:: ብዙውን ጊዜ ምስኪኖችና አቅመ ቢሶች የሆኑ የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጐች (1ቆሮ 1÷26-28)፣ የሚኖሩት ጨካኝ በሆነ ዓለም ውስጥ ነው:: በእንዲህ ዓይነቱ አካባቢ በሕይወት የመኖር ዕድላችን በጣም ጠባብ ነው:: ይህም በእርግጥ የሚሆነው በእረኛው ጥበቃ ሥር የምንሰማራ ካልሆነ ነው::

ማቴ 10÷17-20

17ሰዎች ይዘው ለፍርድ ወደ ሸንጐ ያቀርቧችኋል፤
በምኵራቦቻቸውም ይገርፏችኋል (ማር 13÷9-13፤ ማቴ
24÷9-14፤ ሉቃ 21÷12-19 ጋር ያነ)፤ ስለዚህ ከእነርሱ
ተጠንቀቁ:: 18በእኔ ምክንያት ወደ ገዦችና ወደ ነገሥታት ትወሰዳላችሁ፤ በእነርሱና
በአሕዛብም ፊት ምስክር ትሆናላችሁ:: 19በምትያዙበትም ጊዜ ምን እንናገራለን፣ ምንስ
እንመልሳለን ብላችሁ አትጨነቁ፤ በዚያን ጊዜ የምትናገሩት ይሰጣችኋል፤ 20በእናንተ

[167] ኤደርሼም እንደሚለው፣ «በተኩላዎች መካከል ያሉ በጐች» የሚለው ተምሳሌታዊ አባባል «ሚድራሽ የተባለው ጽሑፍ እስራኤልን በጠላቶችዋ መካከል እየኖረች መሆኑን ያመለክታል:: ከተኩላዎች የሚታደጋቸውና ተኩላዎችን ድል የሚያደርግላቸው እረኛ ምንኛ ታላቅ እንደሆነም ጨምሮ ይገልጻል:: በተመሳሳይ ሁኔታ «እንደ እባብ ብልኖች እንደ ርግብ የዋች» ሁኑ የሚለው ምክር እስራኤል በእግዚአብሔር ፊት እንደ ርግብ የዋህ፣ በጠላቶችዋ አረማውያን ፊት ደግሞ እንደ እባብ ብልኀ መሆኗን በማመልከት በሚድራሽ ውስጥ ተገልጾአል» (I:645)::

የሚናገረው የሰማዩ አባታችሁ መንፈስ እንጂ እናንተ አይደላችሁምና (ሉቃ 12÷11-12፤ ዮሐ 14÷26 ጋር ያነ)::

በመጀመሪያ ጉዞዋቸው እንዲህ ያለ ነገር አልታየም ነበር፤ ስለዚህም ከቍጥር 17-23 ያለው የሚያመለክተው ስለ ኋለኛው ጉዞአቸው ነው:: ምናልባት ኢየሱስ ወደ ፊት ስለሚፈጸም ነገር ትንቢት እየተናገረ ሊሆን ይችላል:: ከዚህ ይልቅ በተለያየ ወቅት ኢየሱስ ስለ ጉዞው የሰጠውን ገለጻ ማቴዎስ አንድ ላይ አቀናብሮ አቅርቦታል ማለቱ ይበልጥ ትክክል ይሆናል:: ከማጣቀሻዎቹ መመልከት እንደሚቻለው እዚህ የምንመለከተውን አብዛኛውን ነገር በደብረ ዘይት ተራራ በሰጠው ገለጻ ውስጥ እናገኘዋለን:: የእነዚህ ተስፋዎች ፍጻሜ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ሊዘገቡ ይችላሉ:: ዛሬም ቢሆን በእምነት ስለ ኢየሱስ ለመናገር እርምጃ ስንወስድ መንፈስ ቅዱስ ከእኛ ጋር በመሆን በእኛ ውስጥ ይናገራል::

21ወንድም ወንድሙን ለሞት አሳልፎ ይሰጣል፤
አባትም ልጁን፣ ልጆች በወላጆቻቸው ላይ ያምጻሉ፤ ማቴ 10÷21-23
ያስገድሏቸዋልም:: 22ስለ ስሜ ሰዎች ሁሉ ይጠሏችኋል፤
ነገር ግን እስከ መጨረሻ የሚጸና እርሱ ይድናል:: 23በአንድ ስፍራ ሲያሳድዷችሁ ወደ
ሌላ ሽሹ፤ እውነት እላችኋለሁ፣ የእስራኤልን ከተሞች ሳታዳርሱ የሰው ልጅ ይመጣል::

በምሥራቃውያን አስተሳሰብ ቤተ ሰብ፣ ሃይማኖትና ፖለቲካ የማይለያዩ ነገሮች ናቸው:: አብዛኛውን ጊዜ በምዕራባውያን ዘንድ እንደ ተለመደው ሕይወትን በተለያዩ ክፍሎች እንደተከፋፈለ ሳይሆን በአንድነት የተያያዘ እንደ ሆነ አድርገው ነው የሚመለከቱት:: ስለሆነም በአንድ አቅጣጫ የሚደረግ ክህደት በሁሉም አቅጣጫ መከፋፈልን እንደሚያስከትል ነበር የሚታሰበው:: አንድ አይሁድ ሃይማኖቱን ከተወ፣ እንደ ሞተ ስለሚቈጠር ቤተ ሰቦቹ የቀብር ሥነ ሥርዓት ይፈጽሙለት ነበር:: ስለዚህ በእርሱ ምክንያት በቤተ ሰብ ውስጥ ስለሚመጣ



መከፋፈል ኢየሱስ ትንቢት መናገሩ ለምን እንደ ነበር መረዳት አያዳግትም::

በአዲስ ኪዳን እስከ መጨረሻ ስለ መጽናት የተነገረው የተለመደ አነጋገር ነበር (ማቴ 10÷22፤ 24÷13፤ ማር 13÷13፤ 1ቆሮ 1÷8፤ ዕብ 3÷14፤ ራእ 2÷26):: ደህንነት እስከ መጨረሻው ለሚዘልቁ እንጂ ሩጫውን ለጀመሩ አለመሆኑ ግልጽ ነው:: ለአንዳንዶች ሩጫው የሚያበቃው ያለ ጊዜያቸው በሰማዕትነት ሲገደሉ ነው:: የሌሎች ሩጫ ደግሞ የሚያበቃው በስተርጅና ተፈጥሮአዊ ሞት ሲሞቱ ይሆናል:: ለአንድ ትውልድ ደግሞ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ በክብር መመለስ ይሆናል::

ያም ሆኖ ግን እስከ መጨረሻው መጽናት ሲባል የግድ እስከዘሉ ድረስ መሸነፍ ማለት አይደለም:: ኢየሱስ ለዐሥራ ሁለቱ ከስደት እንዲሸሹ ነግሮአቸዋል:: ፈሪዎች አልነበሩም፣ ሞኞችም መሆን የለባቸውም:: ጸንቶ መቆምና መዋጋት (ሐሥ 8÷1፤ 16÷39-40፤ 21÷13)፣ እንዲሁም መሸሽ የሚያስፈልግበት ጊዜ አለ (ሐሥ 8÷1፤ 13÷51፤ 14÷6:20):: በተቻለ መጠን አካባቢውን ሁሉ ማዳረስ የሚያስፈልግበትም ጊዜ አለ:: ቍጥር 23 የሚያመለክተው እንዲህ ዓይነቱን ጊዜ ነው:: በመሠረቱ ኢየሱስ፣ «ልባቸውንና ጆሮዎቻቸውን ከደፈኑ ሰዎች ጋር ጊዜያችሁን አታባክኑ:: ይልቁንም መልካም ዐፈር ወዳለበት ቦታ ተሻገሩ!» ማለቱ ነበር::

እዚህ ላይ ጥያቄው፣ «የሰው ልጅ የሚመጣው መቼ ነው?» የሚል ነው (ቍ 23):: (1) ምናልባትም በዚያ ጊዜ ስለ ነበረው አገልግሎት እየተናገረ ሊሆን ይችላል:: ይሁን እንጂ ከዐውዱ ጋር የሚስማማ አይሆንም:: በቤተ ሰቦች መካከል እስከዚህ የጐላ መለያየት እየታየ አልነበረም፤ ሐዋርያቱም በሰማዕትነት እየተገደሉ አልነበረም:: (2) ምናልባትም ስለ መጨረሻው ጊዜ፣ ስለ ራሱ (ኢየሱስ ክርስቶስ) ዳግም ምፅዓት እየተናገረ ሊሆን ይችላል:: ይሁን እንጂ ባለፉት 2000

ዓመታት መላው የፓለስቲና ምድር በወንጌሉ መልእክት ብዙ ጊዜ ተነክቷል:: ስለሆነም ኢየሱስ ከመመለሱ በፊት የፓለስቲና ከተሞች በወንጌል አይደረሱም ማለት ትክክል አይደለም:: (3) ምናልባት በ70 ዓ.ም. ኢየሩሳሌም ስለምትደመሰስባት ስለ መጪው ፍርድ በምሳሌያዊ ሁኔታ እየተናገረ ይሆናል:: ይህ ከዚህ ምንባብና በማቴዎስ 24 ካሉ ተጓዳኝ ምንባቦች ጋር ይስማማል (ማር 13፥9-13፤ ዳን 7፥13፤ ዮሐ 11፥48 ጋር ያነ):: ስለዚህም ኢየሱስ፣ «በሮማውያን ከመወረሯና ኢየሩሳሌም ራሷ ከመደምሰሷ በፊት ፓለስቲናን በወንጌል ማዳረስ አትችሉም» ማለቱ እንደ ነበር እንረዳለን:: ከዚህ አባባሉ ደቀ መዛሙርቱ ምን ያህሉን እንደ ተረዱ አጠያያቂ ነው::[168]

[24]ደቀ መዝሙር ከመምህሩ፣ ሎሌም ከጌታው አይበልጥም፤ [25]ደቀ መዝሙር መምህሩን፣ ሎሌም ጌታውን ከመሰለ ይበቃዋል:: ባለቤቱን ብዔልዜቡል ካሉት ቤተ ሰዎቹንማ እንዴት አብልጠው አይሏቸውም!

**ማቴ 10፥24-25 ሉቃ 6፥40፤ ዮሐ 13፥16 ጋር ያነ**

ቊጥር 24ን ከሚገባ በላይ ቃል በቃል ልንወስደው አይገባም:: አልፎ አልፎ ቢሆንም ተማሪ ከመምህሩ በልጦ የሚገኝበት ጊዜ አለ (ዮሐ 14፥12 ጋር ያነ):: የዚህ ምሳሌ ዋና ነጥብ ግን ይህ አይደለም::

---

[168] ሲ.ኤች. ጊብሊን የተለየ ገለጻ ያቀርባል:: ዐውዱን ከቅደም ተከተላዊ ይዘቱ አንጻር ሳይሆን ምሳሌነትን ወይም ሥርዓትን በሚያመለክት መልኩ መረዳት አለብን:: በሌላ አነጋገር ቊ 23 ሐዋርያቱ ላይ ስለሚደርሰው ሁኔታ ትንቢት የሚናገር ሳይሆን፣ ክርስቲያኖች በአዲስ አካባቢ ወንጌልን ሲያዳርሱ ሊደርስባቸው ስለሚችል ሁኔታ እየተናገረ ነው:: (1) «አሕዛብ» እና «ሳምራውያን» (ቊ 5) ትክክለኛ ማንነትን ከመግለጽ ይልቅ በምሳሌያዊ ሁኔታ ነው የተጠቀመባቸው:: (2) «ሳታዳርሱ» የሚለው የወንጌል ማዳረስ ሥራን እንጂ መልክዓ ምድራዊ ክልልን የሚያመለክት አይደለም:: (3) የአካል/ ጥላ ንጽጽራዊ አፈታትን እየተጠቀመ ነበር:: ዋናው ጉዳይ፣ እኛ የጀመርነውን ስብከት ኢየሱስ በፍርድ ይደመድመዋል (በሽልማት ወይም በቅጣት):: የእኛን ወንጌል የማዳረስ ሥራ የሚጨርሰው እርሱ ነው:: "Theological Perspective and Matthew 10:23b," *TS* 29 (1968): 637-661 ጋር ያነጻጽሩ::



ይህ በሌሎች ሁለት ቦታዎችም ተነሥቶአል:: በሉቃስ 6፥39-40 ላይ ኢየሱስ፣ «ዕውር ዕውርን ሊመራ ይችላልን?» በማለት ጠይቆአል:: እንደዚያ ከሆነ ሁለቱም በተሳሳተ አቅጣጫ ይጓዛሉ:: ዮሐንስ 13፥16 ላይ ደግሞ ኢየሱስ የደቀ መዛሙርቱን እግር ካጠበ በኋላ እርሱ መምህራቸው መሆኑንና እነርሱም እንደ ደቀ መዛሙርት መምህራቸው ያደረገውን የማድረግ ኀላፊነት እንዳለባቸው ሲያሳስባቸው እንመለከታለን:: በሁለቱም ምሳሌዎች ዋነኛው ነጥብ ግልጽ ነው፤ ተማሪ አስተማሪውን መምሰል አለበት:: ስደትንም በተመለከተም እውነቱ ይኸው ነው:: ኢየሱስ ከተሰደደ፣ ተከታዮችም ይሰደዳሉ:: ኢየሱስን ብዔልዜቡልን ያገለግላል ካሉት (9፥34፤ 12፥24 ጋር ያነ)፣ ደቀ መዛመርቱንም እንደዚያው ይሏቸዋል::

**ማቴ 10፥26-31 ከሉቃ 12፥3 ጋር**

[26]ስለዚህ አትፍሯቸው፤ የተሸፈነ መገለጡ፣ የተደበቀ መውጣቱ አይቀርምና:: [27]በጨለማ የምነግራችሁን በብርሃን አውሩት፤ በጆሮአችሁ የሰማችሁትን በአደባባይ አውጁት፤ [28]ሥጋን መግደል እንጂ ነፍስን መግደል የማይችሉትን አትፍሩ፤ ይልቁንስ ነፍስንና ሥጋን በገሃነም ማጥፋት የሚቻለውን ፍሩ:: [29]በአንድ ሳንቲም ከሚሸጡት ሁለት ድንቢጦች አንዲቷ እንኳ ያለ አባታችሁ ፈቃድ ምድር ላይ አትወድቅም:: [30]የራስ ጠጕራችሁ እንኳ አንድ ሳይቀር የተቈጠረ ነው:: [31]ስለዚህ አትፍሩ፤ ከብዙ ድንቢጦች ይልቅ ዋጋችሁ የከበረ ነው::

ይህ ክፍል ሦስት ነጥቦችን ያቀርባል:: በመጀመሪያ፣ በፊታቸው ከሚጠብቃቸው ተቃውሞ ደቀ መዛሙርቱ ስለ ኢየሱስ ለመናገር ይፈራሉ:: የኋላ ኋላ እውነት ማሸነፉ ስለማይቀር ተቃውሞ ቢኖርም እንኳ መናገር እንጂ ዝም ማለት እንደሌለባቸው ኢየሱስ ያሳስባቸዋል::

በሁለተኛ ደረጃ መጪውን ስደት መፍራት የለባችሁም፤ ምክንያቱም አካላችሁን እንጂ ነፍሳችሁን መግደል አይችልም ይላቸዋል::

አንዳንዶች ቍጥር 28 ሰይጣንን የሚመለከት እንደ ሆነ ያስባሉ:: ይሁን እንጂ እንደዚያ አይልም፤ እንደዚያ ሊልም አይችልም:: ሰይጣን ማንንም ወደ ገሃነም ማግባት አይችልም:: እንዲህ ያለ ሥልጣን የለውም (ወይም ቁልፉ በእርሱ እጅ አይደለም፤ ራእ 20÷3)! በፍጹም! እኛ መፍራት ያለብን እግዚአብሔርን ነው:: ኀይልም ሆነ ሥልጣን ያለው እርሱ ብቻ ነው::

በሦስተኛ ደረጃ፣ የሚወደን ሰማያዊ አባታችን ስለሚያይ፣ ስለሚውቅና ስለሚጠነቀቅልን ስደትንም ሆነ ገሃነምን መፍራት የለብንም:: እርግጥ ነው፣ ስደትና አዳጋች ወቅቶች ሊገጥሙን ይችላሉ:: የረሳን ቢመስለንም እግዚአብሔር ግን በፍጹም አይረሳንም! እያንዳንዷ ትንሽ ድንቢጥ ጥቃቅን ስለ ሆነ ነገራችን እንኳ እግዚአብሔር እንደሚጠነቀቅ ልታሳስበን ይገባል:: ክፋትና መከራ እንዴት ሊመጡ እንደሚችሉ አንረዳ ይሆናል፤ ሆኖም የራስ ጠጕራችን እንኳ ሳይቀር በእግዚአብሔር የተቈጠረ መሆኑን በማወቃችን ደስ ይለናል::[169] ስለሆነም መከራችን ሁሉን ከሚያዩ የእርሱ ዓይኖች የተሠወረ አይደለም::

> [32]በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ፣ እኔም በሰማይ ባለው አባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ፤ [33]ነገር ግን በሰው ፊት የሚክደኝን፣ እኔም በሰማይ ባለው አባቴ ፊት እክደዋለሁ:: [በእግዚአበሔር መላእክት ፊት ይካዳል<sup>ሉቃ</sup>]::
>
> **ማቴ 10÷32-34 ሉቃ 12÷9 ጋር**

እዚህም ላይ በመከራ ጊዜ መጽናት እንደሚገባን ሌላ ተጨማሪ ምክንያት እንመለከታለን:: ምናልባትም፣ «ፍትሐዊ የአሠራር ሕግ» ልንለው እንችላለን:: በዚህ ምድር ለኢየሱስ የምናደርግለትን፣ እርሱም በሰማይ ለእኛ ያደርግልናል:: «የሚመሰክርልኝ» (*homologeo*) የሚለው ቃል በአንደበት መናገርን ይመለከታል:: ስለሆነም በአኗኗር ዘይቤ

[169] D.C. Allison, "The Hairs of Your Head are All Numbered," *ExpT* 101 (1990): 334-336.



ወንጌልን ማስፋፋት ትክክል ቢሆንም በቂ አይደለም:: በአንድ የሆነ ወቅት በአንደበታችንም ኢየሱስን መመስከር ይኖርብናል (ሮሜ 10÷9-10፤ ዕብ 3÷1፤ 13÷15):: ከዚህ በተጨማሪ ይህ መሆን ያለበት ዓለም ልትሰማ በምትችልበት መንገድ እንጂ ለቤተ ክርስቲያን አይደለም (ቍ. 27 ጋር ያነ)::

> **ማቴ 10÷34-36 ሉቃ 12÷51-52 ጋር**
>
> [34]እኔ የመጣሁት ሰላምን በምድር ለማስፈን አይምሰላችሁ፤ ሰይፍን እንጂ ሰላምን ለማውረድ አልመጣሁም:: [35]እኔ የመጣሁት ልጅን ከአባት፣
> ሴት ልጅን ከእናቷ፣
> ምራትንም ከዐማቷ ለመለያየት ነው፤
> [36]የሰው ጠላቶቹ፣
> የገዛ ቤተ ሰዎቹ ይሆናሉ::

ምንኛ እርስ በርስ የሚቃረን የሚመስል ንግግር ነው! ጨዋና ትሑት (ማቴ 11÷29)፣ ለመብቱ እንኳ የማይከራከር (ኢሳ 53÷7) የሰላም ንጉሥ (ኢሳ 9÷6) ለከፍተኛ መከፋፈል ምክንያት ይሆናል (ማቴ 10÷21):: ይሁን እንጂ በቍጥር 35 ላይ «ማስነሣት» (*dichazo*) በማለት ኢየሱስ የተናገረው ቃል በመጽሐፍ ቅዱሳችን ከቀረበው ይልቅ ከባድ ነው:: ቃሉ፣ «ዓመፅ ማነሣሣትን» ወይም «አለመግባባት መዝራትን» ያመለክታል:: የኢየሱስ መሪ ዓላማ ሰላምን ማምጣት ነው፤ ሆኖም ሰላምን የሚያመጣው ግን እውነትንና የትክክለኛ ደቀ መዝሙርነት መርሆን በመሠዋት አይደለም::

[37]ከእኔ ይልቅ እናቱን ወይም አባቱን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባም፤ ከእኔ ይልቅ ወንድ ልጁን ወይም ሴት ልጁን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባም:: [38]መስቀሉን ተሸክሞ [በየዕለቱ[ሉቃ]] የማይከተለኝ የእኔ ሊሆን አይገባውም:: [39]ሕይወቱን ሊያድን የሚፈልግ ያጠፋታል፤ ሕይወቱን ስለ እኔ አሳልፎ የሚሰጥ ግን ያገኛታል::

ማቴ 10÷37-39፤ ሉቃ 9÷23 ጋር ከሉቃ 14÷25-27፤ 17÷33፤ ዮሐ 12÷25፤ ጋር ያነ፤ እንዲሁም ማቴ 16÷24-25፤ ማር 8÷24-35

ድነት በጥረታችን የሚገኝ አይደለም ... ይሁን እንጂ ነጻ አይደለም:: ኢየሱስ ሁሉንም ለእርሱ አሳልፈን እንድንሰጠው ይጠብቃል:: ሙሉ በሙሉ እርሱን እንዳንከተል የሚያሰናክለንን ማንኛውንም ነገር ቤተ ሰብ ቢሆን[170] (ቊ 37)፣ ገንዘብ ቢሆን (ማቴ 19÷21)፣ ደረጃ ቢሆን (ማቴ 19÷30)፣ ሥልጣን ቢሆን (ማቴ 20÷27) ሁሉንም እንድንተው ይፈልጋል::

በአጭር አነጋገር በሕይወታችን ላይ ያለንን የይገባኛል መብት እንኳ አሳልፈን እንድንሰጠው ይጠይቃል (ቊ 38-39):: በኢየሱስ፣ «የመስቀል ነክ ንግግር»[171] ይህ በጣም ግልጽ ነው:: በሮማውያን ባሕል መሠረት መናኛውን መስቀል አንገቱ ላይ እስከሚያጠልቅ ወይም በመኪናው የፊት መስታወት ላይ እስከሚያንጠለጥል ድረስ አእምሮውን የሚስት ሰው አይኖርም:: መስቀል አሰቃቂ ስቃይንና ሞትን ለማስከተል የሚጠቀሙበት መሣሪያ ነበር:: መስቀል የሚሸከም ሰው ጨርሶ

[170] ይህም ምንባብ ኤፌ 6÷1-4 እና 1ጢሞ 5÷8 ከመሳሰለ ምንባቦች ጋር ሚዛናዊ ተደርጐ መታየት እንዳለበት ብሉምበርግ እንደሚገባ አስተውሎታል:: «ለቤተ ሰብ ራስን መስጠት ዋና ክርስቲያናዊ ግዴታ ቢሆንም፣ ይህ ግን ለእግዚአብሔር ያለንን መስጠት እስከምናመቻመች ሊያደርገን አይገባም» (ገጽ 181)::

[171] D.R. Fletcher, "Condemned to Die," *Int* 18 (1964): 156-164. «በእንጨት ላይ የተሰቀለ በእግዚአብሔር ዘንድ የተረገመ ነውና» በሚለው ከዘዳግም 21÷22-23 አንጻር የኢየሱስ አነጋገር በአድማጮቹ ላይ ድንጋጤ ይፈጥራል::



በማይመለስበት አንድ አቅጣጫ ጉዞ እየተጓዘ ነው::[172] መስቀል ላይ ሰዎችን መግደል የሮማውያን እንጂ የአይሁዳውያን አገዳደል ዘዴ እንዳልነበርም እንገነዘባለን (የአይሁድ አገዳደል በድንጋይ መውገር ነበር):: ስለሆነም የኢየሱስ አነጋገር ትንቢታዊና፣ በግል ሕይወቱ የሚፈጸም ጉዳይም ነበር ማለት ነው::[173]

ኢየሱስን ሲከተሉ የነበሩ ብዙ ሰዎች ወደ ሰማዕትነት ነበር የተጓዙት:: ይሁን እንጂ ሌሎች ደግሞ ለእርሱ ከመሞት ይልቅ ይበልጥ አዳጋች ለሆነ ተግባር ማለትም ለእርሱ ወደመኖር ሕይወት ነበር የተጠሩት:: ምንም እንኳ የእነዚህ ሁለት ሕይወት ጥሪ ውጤቶች በጣም የተለያዩ ቢሆንም፣ ሙሉ በሙሉ ለክርስቶስ መስጠትንና ዓለምን መተውን በሚመለከት አንድ ዓይነት ናቸው::

ቊጥር 39 ላይ የምንመለከተው መሳይ ቅራኔ እንደ መዝሙር አዝማች ሁሉ በወንጌሎች ውስጥ በተደጋጋሚ የምንመለከተው ነው:: እንዲያውም በጣም ብዙ ጊዜ የተጠቀሰ የኢየሱስ አባባል ነው:: ለክርስቶስ የመስጠታችን ደም ሥር፣ ስለ ተሻለ የወደፊት ሕይወት የተነገረ ተስፋ ብቻ ሳይሆን፣ በዚህ ሕይወታችንም የተሻለ ሕይወት እንደሚኖረን የሚያስረግጥ ነው:: አንድ ዘር በሕይወት የሚነሣው ምድር ውስጥ ከተቀበረ በኋላ ብቻ ነው:: ቢራቢሮ መብረር የምትችለው የዕጭ ሽፋን ውስጥ ተቀብራ ከቆየች በኋላ ነው:: ክርስቲያንም የተሟላ ሕይወት የሚያገኘው መስቀሉን ከተሸከመ በኋላ ነው (ዮሐ 10÷10)::

[172] መስቀልላይ የሚገደል ማንኛውም ወንጀለኛ መስቀሉን ተሸክሞ ወደ መሰቀያው ቦታ መሄድ ነበረበት (Plutarch, *De Sera Num. Vind.* 9.554B).

[173] J.G.Griffiths, "The Disciple's Cross," *NTS* 16 (1970): 358-364 ላይ እንደሚለው ከዚህ አባባሉ በስተቀር መስቀልን ስለ መሸከም የሚናገሩት ሌሎች የአዲስ ኪዳን ክፍሎች ከኢየሱስ መከራ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ነው የሚያመለክቱት:: ስለሆነም ምንባቡ ከኢየሱስ ሕይወትና ምሳሌውን ከመከተላችን አንጻር መታየት ይኖርበታል::

[40]እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል፤ እኔንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል:: [41]ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ያገኛል፤ ጻድቅንም በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቅን ዋጋ ያገኛል:: [42]ስለዚህ እውነት እላችኋለሁ፣ ማንም ሰው ከእነዚህ ከታናናሾች ለአንዱ ደቀ መዝሙሬ በመሆኑ አንድ ጽዋ ቀዝቃዛ ውሃ ቢሰጠው ዋጋውን አያጣም::

**ማቴ 10÷40-42፤ ከዮሐ 13÷20፤ ሉቃ 10÷16፤ ማር 9÷41 ጋር ያነ**

እዚህ ላይ ሐሳቡ ግልጽ ነው:: «ከእነዚህ አነስተኛ ከሆኑት ወንድሞቼ ለአንዱ ያደረጋችሁት፣ ለእኔ እንዳደረጋችሁት ነው» በማለት ኢየሱስ ይህንኑ በማቴዎስ 25÷40 በድጋሚ ተናግሮታል:: ለሐዋርያትም ሆነ ከዚያም ሰፋ ባለ ሁኔታ ለነቢያት ወይም እንዲያውም ከዚያ ሰፋ ባለ ሁኔታ «ታናናሾች» ለሚላቸው የመርሖው እውነትነት እንደ ተጠበቀ ነው፤ የኢየሱስ ወገኖች ለሆኑ የምናደርገውን ኢየሱስ በግል ለእርሱ እንዳደረግነው ይቀበለዋል::

ሌላው መረዳት ያለብን ጉዳይ ነቢይን የሚባርክ ቤት ወይም ቤተ ሰብ በረከት የሚቀበል መሆኑን ነው:: ነቢያትንና ሐዋርያትን የሚደግፉ ቤተ ሰቦች ከእግዚአብሔር በረከትን ይቀበላሉ (2ነገ 4 ጋር ያነ):: ይህ በዚህ ዘመን ያሉ ክርስቲያን አገልጋዮችንም በተመለከተ እውነት ነው::

[12]እነርሱም ከዚያ ወጥተው፤ ሰዎች ንስሐ እንዲገቡም ሕዝቡን ሰበኩ፤ [13]ብዙ አጋንንት አስወጡ፤ ብዙ ሕመምተኞችንም ዘይት እየቀቡ ፈወሱ::

**§70ሐ**
**የዐሥራ ሁለቱ ስኬት**
**(ማቴ 11÷1፤ ማር 6÷12-13፤ ሉቃ 9÷6)**

ከስብከት በኋላ ዐሥራ ሁለቱ፣ ሁለት ሁለት እየሆኑ በመሄድ ኢየሱስ የሰጣቸውን ሥራ ፈጸሙ:: ማርቆስ



ሕመምተኞችን ስለ ፈወሱበት ሁኔታ ሲናገር ዘይት እየቀቡ ይላል:: ከያዕቆብ 5÷14 አንጻር ይህ ትኩረት የሚያሻው ነው::

**§ 71ሀ**
**ሄሮድስ አንቲጳስ ኢየሱስን በተመለከተ መሳሳቱ**

ዐሥራ ሁለቱ ጉዞ ከመጀመራቸው ጥቂት ቀደም ሲል ኢየሱስ ለመጨረሻ ጊዜ ወዳደገበት የናዝሬት ከተማ ሄዶ ነበር (§69):: ስለ ኢየሱስ የነበራቸውን የተሳሳተ አመለካከትም እናነባለን:: አሁን ግን የምናየው ሄሮድስ የፈጸመውን ስሕተት ነው::

**(ማቴ 14÷1-2፤ ማር 6÷14-16፤ ሉቃ 9÷7-9)**

[[1]በዚያን ጊዜ[ማቴ]] [ማር ፮] [14]የኢየሱስ ስም እየታወቀ በመምጣቱ፣ ንጉሥ ሄሮድስ ይህንኑ ሰማ:: [በሁኔታው ተደናገረ[ሉቃ]] አንዳንዶችም [ባለሟሎቹንም[ማቴ]] የዚህ ዐይነት ታምር በእርሱ የሚሠራው መጥምቁ ዮሐንስ ከሙታን ቢነሣ ነው ይሉ ነበር::

[15]ሌሎቹም፣ «ኤልያስ ነው» አሉ:: አንዳንዶች ደግሞ፣ «ከቀደምት ነቢያት እንደ አንዱ ነቢይ ነው» ይሉ ነበር:: [16]ሄሮድስ ነገሩን ሲሰማ ግን፣ «እኔ ራሱን ያስቈረጥሁት ዮሐንስ ከሙታን ተነሥቶአል! አለ [በዐይኑም ሊያየው ይሻ ነበር[ሉቃ]]::

ፈሪሳውያንን የሚከተሉ አይሁድ በትንሣኤ ሙታን ያምኑ ነበር:: ይሁን እንጂ ነገረ መለኮታዊ አመለካከታቸው ከአጉል እምነት ጋር የተደባለቀ ነበር:: ለምሳሌ ያህል የሞተ ሰው መንፈስ በሌላ ሰው ውስጥ በመሆን ተመልሶ ይመጣል ብለው ያምኑ ነበር (Josephus, *Wars* 1. 599 ጋር ያነ):: በሌላ አነጋገር የሞተው ሰው መንፈስ በሕይወት ባለው ሰው ውስጥ ሊገባና ኃይል ሊሰጠው ይችላል:: የኢየሱስን ተአምራዊ ኃይል ብዙዎች የሚገልጹት በዚህ መልኩ ነበር:: ኤልያስን፣ ኤርምያስን ወይም መጥምቁ ዮሐንስን የመሳሰሉ የአንዳንድ ትልልቅ ነቢያት መንፈስ

ለፍርበታል ብለው ገምተው ነበር (ማቴ 16፥14 ጋር ያነ)። ሄሮድስም ቢሆን ይህን በጣም የተለመደ አጉል እምነት ተቀብሎ ነበር።

የሄሮድስ ቤተ ሰብ በሙሉ በፖለቲካ ሽፍጥ፣ ነውጥን በተሞላ የቤተሰብ ግንኙነት፣ በወሲባዊ ቅሌት በተለይም የሥጋ ዘመድን በማግባትና በመፍታት እንዲሁም የአይሁድ ሃይማኖትን በመቀበል (ዓላማቸውን ለማሳካት እስከ ጠቀመ ድረስ) የሚታወቅ ቤተ ሰብ ነበር። ሄሮድስና ሚስቱ የሰዱቃውያንን ፖለቲካ ሲቀበሉና እምነታቸውን ከፈሪሳውያን ሲያገኙ ሁለቱንም የተቀበሉት አዋጪ ለሆነ ምክንያት ነበር ይህም ተደማጭነታቸውን አስፍቶላቸው ነበር።

«ንጉሥ» በመባል ይጠራ የነበረው የአራተኛው ክፍል ገዥ የነበረው ሄሮድስ፣ ከሳምራዊቷ ሚስቱ ከማልታሴ የተወለደ የታላቁ ሄሮድስ ልጅ ነበር። እንደ ሌሎቹ ሄሮድሶች እርሱም ዕረፍት የሚነሣ የበደለኝነት ስሜት ነበረው፤ ሆኖም ይህ ስሜቱ ቅጥ ያጣ ሥልጣን ናፋቂነቱን ሊገታለት አልቻለም። ሃይማኖትን መጠቀሚያ አድርጐ በማይመች ሁኔታ የያዘ ብልሹ ፖለቲከኛ ነበር። ይኸው የበደለኝነት ስሜቱ የኢየሱስን ማንነት ለማወቅ ገፋፍቶታል። ሆኖም ደቀ መዝሙር ለመሆን ግን ዝግጁ አልነበረም።

**§71**
**የመጥምቁ ዮሐንስ መታሰርና መገደል (ማቴ 14፥3-12፤ማር 6፥17-29 ሉቃ 3፥19-20 ጋር ያነ)[174]**

[ማር6][17]ሄሮድስ ራሱ የወንድሙን የፊልጶስን ሚስት ሄሮድያዳን በማግባቱ ምክንያት፣ ተይዞ እንዲታሰር ትእዛዝ በመስጠት ዮሐንስን ወህኒ ቤት አስገብቶት ነበር፤ [18]ዮሐንስ ሄሮድስን፣ «የወንድምህን ሚስት ታገባት ዘንድ ሕግ ይከለክልሃል» ይለው ነበርና። [ስለ ሌሎች ሥራዎቹ ምክንያት በገሠጸው ጊዜ[ሉቃ]] [19]ሄሮድያዳም በዚህ ቂም ይዛበት ስታስገድለው ፈለገች፤ ነገር ግን አልሆነላትም። [20]ምክንያቱም ዮሐንስ ጻድቅና ቅዱስ ሰው መሆኑን ሄሮድስ በማወቁ ይፈራውና ይጠብቀው ነበር። ዮሐንስ የሚናገረውን ሲሰማ ሄሮድስ ቢታወክም በደስታ ያደምጠው ነበር።

[ማቴ 14][5]«ሄሮድስም ዮሐንስን ሊገድለው ፈልጐ ሕዝቡ እንደ ነቢይ ይመለከተው ስለ ነበር ፈራው»።

---

[174] በዚህ ክፍል የምናያቸው ነገሮች፣ ኢየሱስን አስምልክቶ ሄሮድስ የተሳሳተ አስተሳሰብ ሊኖረው የቻለው ለምን እንደ ሆነ መረዳት የሚያስችል፣ «ትውስታ» ነበር።



መጥምቁ ዮሐንስ የተለሳለሰ ንግግር ይናገራል ተብሎ የሚታማ አልነበረም (ኢሳ 40፥3-5፤ ማቴ 3፥7-12 ጋር ያነ)። ስለ ሕገ - ወጥና ነውረኛ ጋብቻው እንዲሁም ስለ ሌሎች በደሎቹ ሄሮድስን እንኳ ፊት ለፊት የተጋፈጠ ሰው ነበር (ሉቃ 3፥19-20)። ችግሩ ምን እንደ ነበር ጆሴፈስ (ዮሴፍ ወልደ ኩሪዮን) ገልጾታል (Ant 18. 109-115)። የሄሮድስ መጀመሪያ ሚስት የአረቢያው ንጉሥ አሬታስ ልጅ ነበረች። ተጋብተው የተወሰኑ ዓመታት ከኖሩ በኋላ ወደ ሮም ሄደ። እዚያ በነበረ ጊዜ ግማሽ ወንድሙ በነበረው ፊልጶስ ቤት ነበር ያረፈው። ሄሮድስ ከፊልጶስ ሚስት ከሄሮድያዳ ጋር ፍቅር ይይዘዋል፤ የወንድሙን ውለታ የመለሰው ሄሮድያዳ ፊልጶስን ፈትታ እርሱን እንድታገባ በማሳመን ነበር። ወደ አገሩ በተመለሰ ጊዜ የአሬታ ልጅ እየሆነ ያለውን ሤራ ሰማች። ነገሩ እንደ ተነቃበት ሄሮድስ ከማወቁ በፊት በአባቷ አገር ድንበር ላይ ወደሚገኘው ማካሪየስ ወደሚባል ቦታ ደርሳ እንድትመለስ እንዲፈቅድላት ጠየቀችው። ከዚያ በኋላ ወደ አባቷ አገር አምልጣ ሄደች። አሬታስ በጣም ከመናደዱ የተነሣ ሄሮድስ ላይ ጦርነት ዐወጀ፣ በኋላም ሠራዊቱን ደመሰሰበት። ሮማዊው ጄኔራል፣ ቢተለየስ ጣልቃ ባይገባ ኖሮ ሄሮድስን ጨርሶ ያጠፋው ነበር።

በተለያዩ ምክንያቶች ጋብቻቸው ሕገ - ወጥ ነበር። ተቀዳሚው ጉዳይ የሄሮድስ መጀመሪያ ሚስት በሕይወት ነበረች። ሄሮድያዳ የወንድሙ ሚስት ነበረች (ዘሌ 18፥16 ጋር ያነ)። ከዚህም በላይ ሄሮድያዳ በአንድ በኩል የአክስቱ ልጅ (?) ነበረች፤ ስለሆነም ለሁለቱም

ወንድማማቾች ጋብቻቸው በሥጋ ዘመዳሞች መካከል የተደረገ ነበር። ይህ ደግሞ ዮሐንስን አስቆጣው!

ጆሴፈስ ሄሮድስ ዮሐንስን ስላሳሰረበት ሁለተኛ ምክንያት ይነግረናል። የዮሐንስ ዝና እየገነነ በሄደ መጠን፣ በሕዝቡ ውስጥ ነውጥ እያየለ ይሄድ ነበር። ዐመፅ የሚፈጠረው ከእንዲህ ዓይነት ሁኔታዎች ነው። ስለዚህም ሄሮድስ ሕዝባዊ ዐመፅን በመፍራት የተቃውሞው ዋነኛ አንቀሳቃሽ ነው ብሎ ያሰበውን አስወገደው። ሌላው ግምት ውስጥ መግባት ያለበት ጉዳይ ደግሞ ትራኪኒቲስ በሚባል አራተኛው የፊልጶስ ክፍል የነበሩ ብዙዎች ሄሮድስ አንቲጳስን ለመውጋት ከአሬታስ ጋር መሰለፋቸው ነው። ብዙውን ጊዜ ዮሐንስ የስብከት አገልግሎቱን እየፈጸመ የነበረው ለትራኮኒቲስ በጣም ቅርብ በነበሩ በሰሜን ይሁዳና ፔሪያ አካባቢ ነበር። እነዚህ ሰዎች የሰሜኑን ሕዝብ ምሪት ተከትለው እንዳያምጹ ሄሮድስ የአድማ መሪ ነው የሚለውን ማስወገድ ነበረበት።

ሄሮድስ ዮሐንስን ያሳሰረበት ሦስተኛ ምክንያት ሊኖርም ይችላል። በመሠረቱ ሄሮድሶች የሚወግኑት የቤተ መቅደሱን ዙሪያ ከሚቆጣጠሩ ሰዱቃውያን ጋር ነበር። ይሁን እንጂ ፈሪሳውያን በጣም እየተወደዱ ሄደው ነበር። ዮሐንስን ለማሰር የተወሰደው እርምጃ ይጠሉት በነበሩ ፈሪሳውያን ዘንድ መልካም ተቀባይነት ነበረው (ሉቃ 7÷30)። ስለሆነም በአንድ በኩል ሁነኛ ወዳጆችን ለማፍራት ነበር ማለት ነው።

በዮሐንስ ቅር የተሰኘው ሄሮድስ ብቻ ሳይሆን ሄሮድያዳም ጭምር ነበረች። ይህች ሴት በዋዛ የምትታይ አልነበረችም። ሄሮድስ እንዲገድለው ለማሳመን ብትሞክርም ሁለት እንቅፋቶች ገጥመዋት ነበር። በመጀመሪያ፣ ዮሐንስ ጻድቅ ሰው መሆኑን ሄሮድስ ያውቃል። ምንም እንኳ ደካማ ሕሊና የነበረው ቢሆንም እንዲህ ያለውን ጻድቅ ሰው በማይሆን መንገድ ለመግደል ብርታት የሚጐድለው አልነበረም። በተቻለው መጠን ሄሮድስ ጥሪ መሪ ሆኖ መገኘት ይፈልግ ነበር። በጣም



የሚያሳዝነው ግን የሥልጣን ጥማቱ፣ ፍትሕ ከማስፈን ፍላጐቱ ይልቅ አሸንፎ ሲወጣ ይታይ ነበር። በሁለተኛ ደረጃ፣ ሕዝቡ ዮሐንስን እንደ ነቢይ ይመለከቱ ነበር። ዮሐንስን ለማሰር ቀደም ሲል መሣሪያ አንግበዋል። የሕዝቡን ተቃውሞ ላለመቀስቀስ ሄሮድስ የተቻለውን ጥንቃቄ እያደረገ ነበር። በአንድ በኩል ራሱን ከእንዲህ ዓይነቱ ችግር ነጻ ለማድረግ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ትክክለኛ ሰው ሆኖ መገኘት ፈልጓል። በአንድ በኩል ዮሐንስ የሚናገረውን መስማት ይፈልጋል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ዮሐንስ በግል ሕይወቱ እንደሚከነክን ተባይ መሆኑን አይፈልገውም። ዮሐንስን በተመለከተ ሄሮድስ ስለ ሰጠው ምላሽ ማርቆስ ሲናገር፣ «ይታወክ ነበር» ያለው በዚህ ምክንያት ነው።

ጆሴፈስ እንደሚለው (*Ant* 18. 119) ዮሐንስ የታሰረው በ2360 ጫማ ከፍታ ላይ በታነጸችው በጥንካሬዋ ከኢየሩሳሌም ሁለተኛ በሆነችው የተራራ ምሽግ በማካረስ ነበር። የምትገኘው በሙት ባሕር ሰሜናዊ ምሥራቅ ዳርቻ ነበር። ሄሮድስ ከሄሮድያዳ ጋር የነበረበውን ግንኙነት ካወቀች በኋላ የአሬታስ ልጅ ሸሽታ የሄደችው ወደዚህ ምሽግ እንደ ነበር ጆሴፈስም ተናግሯል። በዚያን ወቅት በአሬታስ ምሽግ ቁጥጥር ሥር ነበረች (*Ant* 18. 112)። በመካከላቸው በነበረው መጠነኛ ሽኩቻ ምሽግ ከአሬታስ ወደ ሄሮድስ እጅ ካልተዛወረች ወይም አሬታስ ይህችን ምሽግ ጨርሶ ተቆጣጥሮ ሳይሆን ወዳጃሞች በነበሩ ጊዜ በሄሮድስ ፈቃድ ይጠቀምበት ነበር ካልተባለ በቀር እነዚህ ሁለቱ አቀራረቦች ትክክል ነበሩ ማለት አይቻልም።

የዮሐንስን አገልግሎት አስመልክቶ ማርቆስ በሦስት ቁጥሮች ብቻ ገለጻ ሲሰጥ ሞቱን በተመለከተ ግን ዐሥራ ሦስት ቁጥሮችን መጠቀሙን መረዳት አስፈላጊ ነው። ስለሆነም የዮሐንስ አገልግሎት ለኢየሱስ አገልግሎት በር ከፋች እንደ ነበር ሁሉ፣ የዮሐንስም ሞት የኢየሱስን ሞት አመላካች ማርቆስ ያመለክት ነበር።

21በመጨረሻም አመቺ ቀን መጣ:: ሄሮድስ
በተወለደበት ዕለት ለከፍተኛ ሹማምቱ፣ ለጦር አዛዦችና
በገሊላ ለታወቁ ታላላቅ ሰዎች ግብዣ አደረገ::
22የሄሮድያዳም ልጅ ገብታ በዘፈነች ጊዜ ሄሮድስንና
ተጋባዦቹን ደስ አሰኘቻቸው::

ማር 6÷21-25

ንጉሡም ብላቴናዪቱን፣ «የምትፈልጊውን ሁሉ ጠይቂኝ እሰጥሻለሁ» አላት::
23ደግሞም፣ «እስከ መንግሥቴ እኩሌታ ድረስ እንኳ ቢሆን፣ የምትጠይቂኝን ሁሉ
እሰጥሻለሁ» ሲል በመሐላ ቃል ገባላት::
24እርሷም ወጥታ እናቷን፣ «ምን ልለምነው» አለቻት::
እናቷም፣ «የመጥምቁ የዮሐንስን ራስ» አለቻት:: 25ብላቴናዪቱም ወዲያው
ፈጥና ወደ ንጉሡ በመመለስ፣ «የመጥምቁ የዮሐንስን ራስ አሁን በሳሕን እንድትሰጠኝ
እፈልጋለሁ አለችው::

የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ከኢየሱስ ወደ እርሱ ተመልሰው ከመጡ በርከት ያሉ ሳምንቶች አልፈው ነበር (§57፤ ማቴ 11÷2-19፤ ሉቃ 7÷18-35):: ሄሮድስ በልደት ቀኑ ግብዣ አድርጎ ነበር::[175] በግብዣው ላይ ዝግጅት ከሚያቀርቡት አንዷ የእንጀራ ልጁ ሰሎሜ ነበረች:: ስካር ላይ ለነበሩ ታላላቅ ሹማምት ዳንስ ደነሰችላቸው (ጨፈረች)::[176] የጽሑፉ ዐውድ ዘፈኗ ስሜት የሚያነሣሣ እንደ ነበር ባይናገርም፣ በምሥራቃውያን ባሕል ግን ይህን የሚጠቁም ነበር:: ከዚህም በተረፈ ሄሮድስ የመንግሥቱን እኩሌታ እንኳ እንደሚሰጣት ቃል የገባላት ጥሩ ዘፈን ስለ ዘፈነች ወይም ጥሩ ውዝዋዜ ስላሳየች ብቻ

[175] ኤደርሼይም እንደሚለው ይህ የሄሮድስ ልደት ቀን ሳይሆን ጄኔሲያ (*genesia*) የሚለው ቃል እንደሚያመለክተው ሄሮድስ በአራተኛው ክፍል ላይ ንጉሥ የሆነበትን ያከበረበት ቀን ሊሆን እንደሚችል ያመለክታል::

[176] ቃል በቃል ሲተረጐም በቁጥር 21 በሦስት ምድብ የተጠቀሱት ሰዎች (1) መማክርት - የፖለቲካ መሪዎች፣ (2) አበጋዞች - እያንዳንዱ 1000 ወታደሮች ባሉት ክፍል ላይ ሥልጣን የነበረቻቸው የጦር መሪዎች፣ (3) መኳንንቶች (ተቀዳሚ) የገሊላ ሰዎች - የንግድ፣ የሃይማኖት፣ የፖለቲካ ወዘተ ታላላቅ ሰዎች::



ሊሆን አይችልም:: ይህን በጣም አሳፋሪ የሚያደርገው ደግሞ ሰሎሜ የእንጀራ ልጁ መሆኗ ነበር:: በዚህ ላይ ደግሞ ከዐሥራ ሁለት ዓመት የበለጣት አልነበረችም:: በቁጥር 22 ማርቆስ የተጠቀመበት፣ «ልጅ» (*Korasion*) የሚለው ቃል የዐሥራ ሁለት ዓመት ልጅ ስለነበረችው የኢያኢሮስ ልጅ በማቴዎስ 9÷24 ላይ ተጠቅሷል:: የመንግሥቱን እኩሌታ ሄሮድስ ከሰጣት በመንግሥቱ ከእርሱ ቀጥሎ ሁለተኛ ሰው መሆኗ ነው:: አባባሉ በምሳሌነት የሚጠቀስ ልግስናን የሚያሳይ ቢሆንም፣ ምናልባት ቃል በቃል መውሰድ የሌለበት አባባል ነው::

ያቺን የምታህል ልጅ እንዲህ ያለ ነገር ያደረገችው ለምንድነው? ቁጥር 24 እናቷ ነግራት እንደ ሆነ ፍንጭ ይሰጣል:: ሁኔታው እንደሚታየው ብልግና ቢሆንም የሄሮድስ ቤተ ሰብ ይህን በመሰለ መልኩ ምግባረ ብልሹ ነበር:: መሰሪነታቸው ብልሹነታቸውን ይበልጥ ያጐላዋል:: «ሄሮድስ ከስካሩ ከመንቃቱ በፊት ቶሎ ሥራሽን ፈጽሚ» በሚል አስቸኳይ ትእዛዝ ሄሮድያዳ ሰሎሜን አጣደፈቻት::

26ንጉሡ በነገሩ እጅግ አዘነ፤ በተጋበዙት
እንግዶች ፊት የመሐላ ቃሉን ለማጠፍ አልፈለገም::
27ስለዚህ አንዱን ወታደር በፍጥነት ልኮ፣ የዮሐንስን ራስ
ቈርጦ እንዲያመጣ አዘዘው፤ እርሱም ሄዶ በወህኒ ቤት
ውስጥ ራሱን ቈረጠ፤ 28በሳሕን አምጥቶ ለብላቴናዪቱ ሰጣት፣ ብላቴናዪቱም ለእናትዋ
ሰጠች:: የዮሐንስ ደቀ መዛሙርትም ይህን እንደ ሰሙ መጡ ሬሳውንም ወስደው
ቀበሩት:: [ከዚያም ሄደው የሆነውን ለኢየሱስ ነገሩት[ማቴ]]::

ማር 6÷26-29
ማቴ 14÷12 ጋር

ታዋቂ ፖለቲከኛ ለመሆን ሄሮድስ የነበረው ከፍተኛ ምኞት እዚህም ላይ ሕሊናውን ረታ:: የእርሱ ትልቁ ድክመት ደካማ እንደ ሆነ ተደርጐ እንዳይታሰብ የነበረው ፍርሃት ነበር:: ትዕይንቱ በራሱ አስቃቂ ነበር፤ የዮሐንስ ራስ በብር ሳሕን ቀርቦ ነበር:: ትውፊት እንደሚለው

ከሆነ ደግሞ ሄሮድያዳ የተቆረጠውን ራስ ወደ መኝታ ክፍሏ ከወሰደችው በኋላ ምላሱን ጉልጉላ በማውጣት በእሾክ ጠቅጥቃዋለች:: የክርስቶስን መንገድ ያዘጋጀ ሰው ሕይወት በዚህ መልኩ አበቃ::

ሄሮድያዳ ለሄሮድስ ሞት ምክንያት ሆናለች:: በመጀመሪያ ደረጃ የመጥምቁ ዮሐንስ ሞት ሄሮድስን በግሉ የከነከነው ሲሆን ሕዝቡን ደግሞ አስቆጥቶ ነበር:: ሕሊናው ከአይሁድ አጉል እምነት ጋር ተቀናጅቶ እርሱን ለማወክ ኢየሱስ በዮሐንስ አምሳል እንደ መጣ እንዲያስብ አደረገው::[177] በእርግጥም፣ ዮሐንስን የመሰለ ጻድቅ ሰው በመገደሉ ሕዝቡ ክፉኛ ተናድደው ነበር:: በሁለተኛ ደረጃ፣ ከሄሮድያዳ ጋር የፈጸመው ጋብቻ የመጀመሪያ ሚስቱ ከነበረችው ከአረቢያ ንጉሥ ከአሬታስ ልጅ ጋር የመፋታት ዋጋ አስከፍሎታል:: ቀደም ሲል እንደ ተጠቀሰው አሬታስ በጣም በመቈጣቱ ሄሮድስን በማጥቃት ሠራዊቱን ደምስሶበት ነበር:: ሄሮድስ ራሱ ከሞት ያመለጠው በቬቴሊየስ የሚመራ የሮም ሠራዊት ስለ ደረሰለት ነበር:: ዮሐንስን በመግደሉ ይህ የእግዚአብሔር ፍርድ እንደ መጣ ነበር ሕዝቡ ያሰቡት (Josephus, Ant. 18. 119):: ይህ ጦርነት ሄሮድስ የሮምመንግሥትን ሞገስ እንዲያጣ አድርጉአል:: በመጨረሻም ሄሮድያዳ ከነበራት ከፍተኛ የሥልጣን ጥማት የተነሣ ወደ ሮም እንዲሄድና የበለጠ የፖለቲካ እውቅና ለማግኘት እንዲማፀን ሄሮድስን አባበለችው:: እንደዚያ በማድረጉ የነበረውን ግዛት ተነጥቆ ጉል ውስጥ ወደ ነበረችው ወደ ልዮንስ ግዞተኛ ሆኖ እንዲሄድ ተደርጓል:: ሄሮድያዳ ንጉሡ ያቀረበላትን ስጦታ አልቀበልም በማለት ከባልዋ ጋር ወደ ጉል ሄዳለች (Josephus *Ant.* 18. 254):: በሕይወት ዘመንዋ እንደ መልካም ነገር የሚጠቀስላት ይኸው ብቻ ነው::

የሚሄዱበት ያልነበራቸው የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ከሰማንያ እስከ ዘጠና ኪ.ሜ. ያህል ተጉዘው ይህን አሳዛኝ ታሪክ ለኢየሱስ

[177] «እጅግ አዘነ» *(perilypos v. 26)* ኢየሱስ በአትክልቱ ስፍራ (ጌቴሴማኒ) የነበረውንም ጣር ለመግለጽ ተጠቅሷል (ማር 14፥34)::



ነገሩት:: እስከዚያ ድረስ ከዮሐንስ ጋር የጸኑት ለምን ነበር? ወደ ኢየሱስ እንዲሄዱ ነግሮአቸው ነበር:: ሆኖም አሁን የሚወዱት መሪያቸው ከሞተ በኋላ ከእርሱ ተለይተው ወደ ኢየሱስ ሄዱ::